# ልማታዊነት ወይስ ገበያ?

በኢትዮጵያ ኢሊክትሪክ ኃይል ኢና በኢትዮጵያ ኢሊክትሪክ አገልግሎት




ማቲያስ ገሠሠ

# ልማታዊነት ወይስ ገበያ

## በኢትዮጵያ ኤሌክትሪ ኃይል እና በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

ማቲያስ ገሠሠ

መስከረም 16 2019 ዓም

# ማውጫ


1 መግቢያ ........ 1

2 በኢትዮጵያ አትኩሮት የተነሳው ኢኮኖሚያዊ ኃቅ - የዋጋ ቅዱስነት ........ 4

3 ኤሌክትሪክ በኢትዮጵያ ........ 16

4 በኢትዮጵያ ዘመናዊ የኤሌክትሪክ መስክ ፈተናዎች ........ 20

4.1 የኪሳራ ውርጅብኝ ........ 21

4.2 የኪሳራው ምንጭ ርካሽ እና አቅምን ያገናዘበ ታሪፍ አይደለም ........ 26

4.2.1 በ2025 ከነበረው ሽያጭ 55% የተሸጠው ለውጭ ሐገር ነው ........ 39

4.2.2 የውኃ ግድብ ጥሩ የኢንቨስትመንት አማራጭ አይደለም ........ 48

4.2.3 41% ሎድ ፋክተር ፤ ምክንያት ሊቀርብበት ቢችልም ጥሩ እሚባል አይደለም ........ 55

4.2.4 በኢትዮጵያ ኃይል ማመንጨት እንጂ መሸጥ የእቅዱ አካል አይመስልም ........ 57

4.2.5 የተገነቡ እና በሥራ ላይ ያልዋሉ ማመንጫዎች ........ 66

4.2.6 ኮይሻ - በልማታዊነት ውስጥ ብክነት ስረዓታዊ እንጂ አጋጣሚ አለመሆኑ ሠርቶ ማሳያ .. 74

4.2.7 ነጻ ምሳ የለም ........ 75

5 የተቋማቱ አፈጻጸም ........ 77

5.1 ትርፋማነት ከንብረት አንጻር (Return on Asset – (ROA)) ........ 77

5.2 ትርፋማነት ከአንጡራ ኃብት አንጻር (Return on Equity – (ROE)) ........ 79

5.3 ጠቅላላ ገቢ ከሥራ ማስኬጃ ወጪ አንጻር (Operating Cost per Total Income) ........ 81

5.4 ንብረት በሠራተኛ ( Assets Per Employee) ........ 83

5.5 ትርፍ በሠራተኛ (Profit Per Employee) ........ 86

6 ማጣቃለያ ........ 88

# 1 መግቢያ

ልማታዊነት ወይንስ ገበያ በእሚለው ተከታታይ ጽሑፍ ይኽ አራተኛው ጽሑፍ ነው።

ከእዚኽ በፊት በነበሩት ሦሥት ጽሑፎች ፡-

1. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፥
2. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፥
3. እና ኢትዮ ቴሌኮም (ቴሌ) ፤

በልማታዊነት ወይንስ በገበያ ቢመሩ ይሻላል የእሚል ግምገማ እና ንጽጽር አድርጌያለኹ። የንጽጽሩም ዓላማ ፤ እነ እዚኽ የልማት ተቋማት ፡-

- ለእራሳቸውም እንደ አንድ የንግድ ተቋም ፥
- ለሐገርም አንድ እንደ እነርሱ ያለ የንግድ ተቋም ሊያበረክተው ከእሚገባው አስተዋጾ አንጻር ፥

በልማታዊነት ወይንስ በገበያ ቢመሩ ይሻላል ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነበር።

ይኽንንም ለማድረግ ፤ የሐገራዊ ተቋማቱን ኦዲት የተደረጉ ዓመታዊ ሪፖርቶች እና ለማነጻጸር ደግሞ ለምሳሌ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በምመዝንበት ወቅት የደቡብ አፍሪካውን ስታንዳርድ ባንክን ፣ የኢትዮጵያን አየር መንገድ በምመዝንበት ወቅት የኢምሬትስ አየር መንገድን ፣ ኢትዮ ቴሌኮምን በምመዝንበት ወቅት የሳፋሪኮምን ፤ ዓመታዊ ኦዲት የተደረጉ ሪፖርቶች ፤ በዋና የመረጃ ምንጭነት ተጠቅሜያለኹ።

ይኽ አራተኛው ጽሑፍ ደግሞ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በእሚባሉት እና የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት (Generation) ፣ በማስተላለፍ (Transmission) እና በማከፋፈል (Distribution) ፤ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አቅምን ያገናዘበ ዘመናዊ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የማዳረስ ተልዕኮን የተሸከሙትን ኩባንያዎች ፤ በልማታዊነት ወይንስ በገበያ ቢመሩ ነው ፡-

- ለእራሳቸውም እንደ ተቋም ፥
- ለኢትዮጵያ ሕዝብም ፡- በተወዳዳሪ ዋጋ ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ አገልግሎት በማቅረብ የኑሮ ደረጃውን እና ምርታማነቱን ለማሻሻል ፥

የተሻለ የእሚሆነው ? የእሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እሞክራለኹ።

በኢትዮጵያ ልማታዊነት ወይንስ ገበያ ? የእሚለውን ይኽን ጥያቄ ደግሞ ደጋግሞ ማንሳት ግድ የእሚለው ፤ ኢትዮጵያ በጥቁር አፍሪካ ፤ በኢኮኖሚያዊም ሆነ በፖለቲካው መስክ ፋና ወጊ ልትባል የእምትችል ሐገር ብትሆንም ፤ ዛሬ ላይ በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚ መስክ የእምንገኝበት አቋም ፤ አይደለም ከዓለም

ሐገራት ፤ ከአንድ አንድ የአፍሪካ ሐገራት አንጻር እንኳን እጅግ ኋላ ቀር በመሆኑ እና ይኽን አንጻራዊ የኢትዮጵያ ኋላቀርነትን ችግር መፍታት ካስፈለገ ፤ የእዚኽን አንጻራዊ ኋላ ቀርነት ምክንያት ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

ምክንያቱም ፡- ኢትዮጵያ ዛሬም በብዙ መመዘኛ ኋላ ቀር የእምትባል ሐገር ብትሆንም ፤ ዛሬም ኋላ ቀር የሆነችው ፤ እራሷን ለማዘመን ስለ አልሞከረች ሳይሆን በባለፉት 100 ዓመታት እራሷን ለማዘመን የመረጠቻቸው መንገዶች ፤ ሐገሪቱን ከማዘመን ይልቅ ፤ ባለችበት እንድትረግጥ የእሚያደርጉ በመሆናቸው ነው።

ለምሳሌ ፡- ከአምባገነንነት ወደ ምርታማነት በእሚለው መጽሐፍ ውስጥ ባደረግኹት ጥናት እንደ አየሁት ፤ ሐገራት ከዘመናዊ ኢንደስትራላይዜሽን አንጻር ፤ ትክክለኛውን ፖሊሲ ከተከሉ ፤ እንደ ኢትዮጵያ ካለ ደካማ የኢኮኖሚ ደረጃ ወጥተው ፤ ኢንደስትሪያላይዝድ የሆነ ሐገር ለመሆን ፤ በአማካይ 30 ዓመታት ነው የእሚፈጅባቸው። የላቲን አሜሪካዋ ቺሊ ፣ የትልቋ አሜሪካ ፣ የታላቋ ብሪታንያ ፣ የፖላንድ ፣ የሲንጋፖር ፣ የጃፓን ፣ የቻይና ፣ ወዘተ የኢንደስትሪያላይዜሽን ታሪኮች ለእዚኽ ማሳያ ናቸው።

ከኢትዮጵያ አንጻር ፤ ግዙፍ የእሚባለውን የኃይለ ሥላሴውን ኢትዮጵያን የማዘመን ጥረት ሳንቆጥር ፤ ከደርግ ግዜ አንስቶ የነበረውን እና ልማታዊ በእሚባለው አስተሳሰብ የእሚገለጸውን ኢትዮጵያን የማዘመን ጥረት ብቻ ብንቆጥር ፤ ጥረቱ 52 ዓመት አልፎታል።

ሆኖም የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አይደለም ኢንደስትሪያላይዝድ የሆነች ሐገር ልትባል ይቅርና ፤ ካለባት የተበላሸ ፡- ሕገመንግሥት ፣ የክልል አወቃቀር ፣ የመሬት ፖሊሲ ፣ የገንዘብ ፖሊሲ ፣ የበጀት ፖሊሲ እና የኢንደስትሪ ፖሊሲ የተነሳ ፤ ኢንደስትሪያላይዝድ የመሆን እድሏ እጅግ አደጋ የተዳረገበት ሐገር ሆና ነው የእምትቀርበው።

ምክንያቱም ፤ አኹን ላይ የኢተዮጵያ ማሕበረ ኢኮኖሚ ልማት በእሚከተሉት ነጥቦች የእሚገለጽ ነዉ ፡-

- ኋላ ቀሩ ግብርና ድርሻዉ 33% ሲሆን በአንጻሩ ኢንደስትሪዉ ከገፋ ከ6% አይበልጥም ፥
- ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አንጻር እንኳን ከፍተኛ ገጠሬነት ያለባት ሐገር በመሆኗ ከ75% በላይ የእሚሆነው ኢትዮጵያዊ የገጠር ነዋሪ እና ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ግብርና የእሚኖር ነዉ ፥
- በኼክታር የግብርና ምርታማነት በከዓለም አቀፉ አማካኝ አንጻር እንኳን በጣም ዝቅተኛ የእሚባል ነዉ ፥
- መደበኛ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የእሚያገኘው ሕዝብ ብዛት ከ30% በታች በመሆኑ እና በምሽት በሳተላይት የእሚታዩ የሐገሪቱ ፎቶዎች ሐገሪቱን በጨለማ የተሸፈነች መሆኗን የእሚያሳዩ በመሆናቸው እና ይኽም በእየ ዓመቱ ሲመዘገብ የነበረውን የባለ ኹለት አሀዝ እድገት ምን ውጦት ነው ሐገሪቱን እንደ እዚኽ ጨለማ የወረሳት የእሚያስብሉ መሆናቸው ፥
- ሐገሪቱ አሁን ባላት የዶላር እጥረት ኢንደስትሪ የመገንበት ተስፋዋ በጣም ዝቅተኛ ነዉ ፥ ወዘተ ፤

ኢትዮጵያ ለባለፈው 100 ዓመት (ከኃይለ ሥላሴ ግዜ አንስቶ) ካልሆነ ለባለፉት ከ52 ዓመታት (ከደርግ ግዜ አንስቶ) በላይ የመረጣቸው እና የተከተላቸው የዕድገት ፍኖተ ካርታዎች ፤ ከንቱ መሆናቸውን ያስረዱናል።

ይኸም ማለት ፦ ስተናል ፤ መሳታችንን ግን ሳናውቅ ከ4 አስርት ዓመታት በላይ አልፈዋል። ስለ እዚኸ ፦ መማር እና መቃናት ካለብን ፤ ከየት እንደ ሳትን አውቀን መመለስ አለብን።

ይኸን ዓይነቱ ፤ ሳይታረም ፦ ከደርግ ፣ ወደ ኢሕአዴግ አኹን ደግሞ ወደ ብልጽግና የዞረ ፤ የከሰረ የልማታዊነት መንገድ ፤ ከ52 ዓመታት ሐገር የማዘመን ጥረት በኋላ ፤ ኢትዮጵያን ዛሬም ኋላ ቀር ሐገር በማድረጉ ምክንያት ነው ፤ ልማታዊነት ወይንስ ገበያ የእሚለውን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ በጣም አስፈላጊ የእሚሆነው።

# 2 በኢትዮጵያ አትኩሮት የተነሳው ኢኮኖሚያዊ ኃቅ - የዋጋ ቅዱስነት

በኢትዮጵያ ውስጥ ፤ ከግማሽ ምዕተ ዓመታት በላይ ለቆየው እና ከአብዮቱ ግዜ አንስቶ ሐገሪቱን ለማዘመን የተደረገውን ጥረት ያመከነ አንድ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሳይንስ ግንዛቤ ግድፈት ቢኖር ፤ የኢትዮጵያ ሊህቃን የዋጋን (Price) ምንነት እና ጥቅም የተረዱበት የተሳሳተ ግንዘቤ ነው ማለት ይቻላል።

በኢትዮጵያ በሕዝባዊ መንግሥት አስተሳሰብ ሐገርን የማዘመን ጥረት ከተጀመረ ቢያንስ 52 ዓመት ሆኖታል ፤ በእነ እዚኽ 52 ዓመታት ፤ የተለያየ ዓይነት አመራሮችን ወደ ፊት ያመጡ 3 ወሳኝ የእሚባሉ ለውጦች ፦ የደርግ ፣ የኢሕአዴግ እና የብልጽግና በእሚል ተካኺደዋል።

እነ እዚኽ 3 የተለያዩ አመራሮች ፤ ምንም በእማያጠራጥር መልኩ ፤ አንዱ ከሌላው የእሚለዩበት የእየራሳቸው መለያ ጠባይ ቢኖራቸውም ፤ አንድ የእሚያደርጋቸው ነገር ግን ነበር ወይንም አለ።

እርሱም ፦ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፍተኛ ድህነት ውስጥ ስለ እሚገኝ ፤ መንግሥት የአለውን አቅም እና ስልጣን ተጠቅሞ ፤ መሠረታዊ የእሚባሉ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ፤ የሕዝቡን አቅም ባገናዘበ መልኩ ፍትኃዊ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ፤ እነ እዚኽን አገልግሎቶች ፦ የመደጎም እና የማቅረብ ሥራ መሥራት አለበት የሚለው ነው።

ከእዚኽም የተነሳ ፤ የሕዝብ "ወገንተኝነት" በእሚል ሽፋን ተከልሎ ፤ ለሐገር እና ለሕዝብ ስልታዊ ወይንም ስትራቴጂክ ፋይዳ አላቸው የሚባሉ አገልግሎቶች እና ምርቶች ፤ በመንግሥት ካፒታሊዝም (State Capitalism) ሥር ይገቡና ፤ እነ እዚኽን ስትራቴጂክ አገልግሎቶች እና ምርቶች የእሚያቀርቡ ድርጅቶች ፤ የመንግሥት የልማት ድርጅት ይባላሉ።

እነ እዚኽም የልማት ድርጅቶች ፤ ዋና ተልዕኳቸው የሕብረተሰብን የመግዛት አቅም ያገናዘበ (ርካሽ) እና የስርጭት ፍትኃዊነት ያለው ፤ አገልግሎት እና ምርት ፤ ስትራቴጂክ በተባሉ እንደ ፦ የመብራት (የኤሌክትሪክ) ፣ የቴሌኮምንኬሽን ፣ የባንክ ፣ ወዘተ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ማቅረብ በመሆኑ ፤ ተቋማዊ **ምርታማነት** እና **ትርፋማነት** ፤ ከአቅምን ያገናዘበ ዋጋ እና አገልግሎት/ምርት ከማዳረስ በኋላ በሶሥተኝነት ደረጃ ላይ የእሚያስቀምጡት ግብ ነው።

ቀለል ባለ አነጋገር ፤ የተቋማትን ብሎም የሐገርን ምርታማነት እና ትርፋማነት ከማሳደግ በፊት ፤ የተቋማቱን ምርታማነት እና ትርፋማነት ገድቦ ፤ አገልግሎታቸውን እና ምርቶቻውን በርካሽ ዋጋ ማቅረብ ላይ ያተኩራል ፤ የሕዝቡን የመግዛት አቅም ለማገናዘብ በእሚል።

ከእላይ ሲያዩት ይኸን አካኼድ ፦ የተከበረ ፣ የሕዝብ ወገንተኝነት ያለው እና ስነ ምግባራዊም ይመስላል። በተግባር ግን ፦ ከመሠረታዊ የኢኮኖሚ ሳይንስ መርኽ ጋር ፈጽሞ ተቃራኒ በመሆኑ ፤ ውጤቱ ፦ የታሰበው አቅምን ያገናዘበ ተደራሽ ስትራቴጅካዊ አገልግሎቶች እና ምርቶች አይሆንም።

ምክንያቱም ፦ በአንድ ማሕበረሰብ ውስጥ ፤ መሠረታዊ እና ስትራቴጂክ የእሚባሉ አገልግሎቶች እና ምርቶች ፤ ከአብዛኛው ሕዝብ የመግዛት አቅም በላይ የእሚሆኑት ፤ ያ ማሕበረሰብ ወይንም ሕዝብ በጣም ድኃ ከመሆኑ የተነሳ እሚቀርቡበት ዋጋ ፈጽሞ ከአቅማቸው በላይ ስለ ሆነ ሳይሆን ፤ ይልቁንም የእሚኖሩበት የማሕበረ ኢኮኖሚ ስረዓት በመዋቅራዊ መንገድ ለአገልግሎቶች እና ለምርቶች ዋጋ የእሚወጣበትን ስረዓት በማዛባቱ ፤ ዜጎቹ የእሚያገኙትን ክፍያ በዛም የመግዛት አቅማቸውን ስለ እሚያቀነጭር ነው።

የሕዝቡ ችግር ድህነቱ ሳይሆን የኢኮኖሚ ስረዓቱ የዋጋ ስረዓትን በማዛባት የዜጎችን ገቢ ስለ እሚያሳንስ ነው።

ሰዉ ከሠራ መኖር መቻል አለበት ፤ የኢኮኖሚ ሳይንሱም ፤ ሰዉ ከሠራ በእሚሠራበት ኢኮኖሚ ዉስጥ ራሱን ይችላል።

በእኛ ሐገር ግን ፤ ድህነትን ታሪካዊ አንዳንዴም በሥራ ሳይሆን በመንግሠት ድጎማ ሊፈታ የእሚገባዉ መዋቅራዊ ችግር አድርገን ሰለ እምንቆጥረዉ ፤ በዋጋ ስረዓት ላይ ጣልቃ በመግባት ዋጋ እናዛባለን ።

ይኸ ዋጋ የእሚዛባበት አንዱ መንገድም ፦ ሕዝቡ የመግዛት አቅም ስለ ሌለው እና አገልግሎቱን በተወሰነም ደረጃ ቢሆን የግድ ማግኘት ስለ አለበት መንግሥት የትርፍ ፍላጎቱ ሳይኖረው እና ቢኖረውም እንኳን ተጭኖት ፦ ተቋማትን በባለቤትነት ይዞ ፦ አገልግሎት እና ምርት አቅምን ያገናዘበ እና ተደራሽነት ያለው እንዲሆን ዋጋን መቀነስ አለበት በእሚል ነው።

ትርፍ ሳይፈልጉ ዋጋ አቅምን ያገናዘበ እንዲሆን እና አገልግሎቱ ወይንም ምርቱ ተደራሽነት እንዲኖረው ማድረግ የእሚቻለው ደግሞ ፤ በእዚያ ኺደት የእሚፈጠረውን ፤ በማምረቻ እና በመሸጫ ዋጋ አለመመጣጠን የእሚመጣዉን ክፍተት ወይንም ኪሳራ በአንድም በሌላም መንገድ በመደጎም ነው።

ምክንያቱም ፦ አገልግሎቶችን እና ምርቶችን ፤ ከእሚመረቱበት ዋጋ በታች እየሸጡ መቀጠል እሚቻለው ፤ ገቢ ከወጪ በማነሱ ምክንያት የእሚፈጠረውን ጉድለት ወይንም ክስረት መሙላት ሲቻል ብቻ ነው።

አንዳንዶች እንደ እሚመስላቸው ደግሞ መንግሥት ገንዘብ የማተም ስልጣን ስላለው ገንዘብ እንደ አሻው እያተመ ወይንም እየተበደረ ወይንም ግብር እየሰበሰበ ፣ ወዘተ ጉድለቱን እንደ አሻው መሙላት አይችልም።

የሐገራችን አንዱ ትልቁ ችግርም እርሱ ነው ፤ ምክንያቱም ፦ መንግሥታቱ እንዲኸ ማድረግ ይቻላል የእሚል ደረቅ የመኃይም ዕምነት ስለ አላቸው።

ይኸ ሲባል ፡- መንግሥት አስፈላጊ የሆኑ እንደ መብራት ያሉ አገልግሎት እና ምርቶች በፍጹም መደጎም የለበትም ለማለት አይደለም።

የትኛውም ዓይነት መንግሥት የተለያዩ ዓይነት ያላቸውን ድጎማዎች ያደርጋል ወይንም ማድረግ አለበት።

ሆኖም አንድ መንግሥት ይኸን ሲያደርግ ወይንም ድጎማን ሲያደርግ ግን የዋጋ ስረዓትን እንደ ቅዱስ እና ሊነካ እማይገባው ነገር ቆጥሮ ፤ የዋጋ ስረዓቱን በእማያዛባ መንገድ ነው ማድረግ ያለበት።

የዋጋ ስረዓትን የእማያዛባ ድጎማ ግን ፤ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ማኃይም ፖለቲከኞች ለናኙበት ሐገር ፤ ሲሉት ነው እሚቀለው እንጂ ሲተገብሩት ከድንጋይ ስለ እሚከብዳቸው ፤ ሮጠው ወደ ዋጋ ስረዓት አዛቢ የድጎማ ስረዓት የመዞር አባዜ ይጠናወታቸዋል።

ከእዚኸም የተነሳ ፤ መንግሥታቱ ለመደጎም የእሚሮጡትን ያኸል ሕዝብ መደጎም የእሚችሉበት አቅም ወይንም ኃብት ስለ ሌላቸዉ ፤ የራሱን ድህነት ያላሸነፈ የድኃ ደጓሚ ይሆናሉ። አንድ መንግሥት ግን ፡- ወደ ድጎማ ከመጋባቱ በፊቱ ኢኮኖሚዉ በገበያ ሠርቶ በቂ ግብር እንዲያመነጭ ማድረግ አለበት ።

ይኸ ደግሞ የዋጋን ቅዱስነት ሳይረዱ እና ሳያከብሩ ሊመጣ አይችልም ።

## ዋጋ ፡ ታላቁ አጋፋሪ

አጋፋሪ የእሚለው ቃል ፤ የድግስ ወይንም የንጉሥ እልፍኝ ተቆጣጣሪ (Manager) ዓይነት ሰው ነው። የሥራ ድርሻውም ፡- ምን ይጨመር ፣ ምን ይቀነስ ፣ ምን ያስፈልጋል ፣ ምን ይምጣ ፣ ምን ይከልከል ፣ ማን ወደ ንጉሥ ይግባ ፣ ማን ይቆይ ፣ ወዘተ እያለ ፤ ድግሱ ወይንም የንጉሡ እልፍኝ በስረዓት እንዲኼድ ማድረግ ነው።

ዋጋም ንጉሥ ወይንም ደጋሽ ያልሾመው ፤ ምን አልባት እግዚአብሔር የሾመው ፤ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አጋፋሪ ነው።

**ዋጋ** በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ ከግብታዊ የመንግሥት ስልጣን ጣልቃ ገብነት ነጻ ሲሆን ፡- ምን ይመረት ፣ ምን ዓይነት ሠራተኛ ይቀጠር ፣ የትኛው ምርት ይቀንስ ፣ የቱ ነጋዴ ይክሰር ፣ የቱ ነጋዴ ይደግ ፣ ብድር ለማን ይሰጥ ፣ መሬት ማን ያግኝ ፣ ለእዚኸ የሞያ መስክ የሚከፈለው ደሞዝ ስንት ይኹን ፣ ወዘተ እያለ ፤ ምንም ክፍያ ወይንም ምስጋና ሳይፈልግ ፤ ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴን ያጋፍራል።

**ዋጋ** ግን እንደው የይስሙላ አጋፋሪ አይደለም ፤ ይልቁንም አንድ ጎበዝ አጋፋሪ ፤ የደጋሹ ድግስ ወይንም የንጉሥ እልፍኝ ፤ ምንም መጉላላት ፣ መንዛዛት እና መማረር ሳይኖርበት ፤ ኹሉንም በአግባቡ በማድረግ ፡- ደጋሹን ፣ እድመተኞቹን ፣ ንጉሡን ፣ እንግዶቹን ፣ ወዘተ በጥሩ ኹኔታ እንደ እሚያገለግለው ፤ ዋጋም ያልተሾመ ትራፊክ ሳይሆን ፤ ባግባቡ ሲሠራ ፡- ብድር የእሚያገኙ ሰዎችን በመምረጥ ፣ ጥሩውን ምርት ከደካማው በመለየት ፣ አዋጩን ንግድ ከአክሳሪው በመለየት ፣ ወዘተ ፤ የሐገርን ጠቅላላ ምርታማነት እና ትርፋማነት

በማሳደግ ፤ የዜጎችን የመግዛት አቅም እና የመንግሥትን የድጎማ አቅም በአንድነት በማሳደግ ፤ ብዝዎቹ ዜጎች በገንዘባቸው ጥቂቶች ደግሞ በመንግሥት ድጎማ ፤ ኢኮኖሚያዊ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ፤ በተገቢው ዋጋ ማግኘት የእሚያስችል ዓይነተኛ አጋፋሪ ነው።

ዋጋ የፖለቲካ ውሳኔ ውጤት ሳይሆን በነጻ ገበያ ውስጥ በጥየቃ እና በአቅርቦት (The dynamics of demand and supply ) መካከል በእሚደረግ መሳሳብ እና መገፋፋት የእሚወሰን ሲሆን ፦ በአንድ ሐገር ውስጥ የእሚገኙ የሠራተኛን ጉልበት ጨምሮ ያሉ ኃብቶች ይበልጥ ምርታማ ወደ ሆኑበት መስክ ይደለደላሉ።

ገንዘብ ማን በአግባቡ ይጠቀመኛል ብሎ ወደ እዚያ ሰው ይኼዳል። ባለ ኃብቶች የቱ ጋር ፍላጎት እንደ አለ አውቀው ፤ ምን ማምረት እንደ አለባቸው ያውቃሉ። አምራቾች አፈጻጸማቸውን ሲያሻሽሉ እና አፈጻጸምን እሚያሻሽል ፈጠራ ይዘው ሲመጡ ይሸለማሉ። ሸማቾች ዋጋ በእሚሰጣቸው ምልክት ተመሥረተው የግዢ ኹኔታቸውን ያስተካክላሉ።

ከአጉል የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነጻ የሆነ እና ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ኹኔታዎችን የእሚያንጸባርቅ ፤ ትክክለኛ የዋጋ ስረዓት ሲኖር ፦ ኢኮኖሚው እንደ አንድ ትልቅ የኦርኬስትራ ባንድ ፤ የተለያየ የሙዚቃ መሣሪያ የእሚጫወቱ ሰዎች ፤ በተቀናጀ መልኩ ውብ የሆነ ሙዚቃ እንደ እሚያወጡት ፤ እርሱም ድንቅ ቅንብር ይሆናል ፤ ምንም እንኳን በሚልዮን የእሚቆጠሩ ሰዎች ፤ በአብዛኛው እርስ በእርስ ሳይተዋወቁ እና ሳይገናኙ ፤ የተለያየ ዓይነት ይዘት ያላቸው ፦ የማምረት ፣ የመግዛት ፣ የመሸጥ ፣ የማከፋፈል ፣ ዋጋ የመጨመር ፣ ዋጋ የመቀነስ ፣ ወዘተ ዓይነት በሚልዮን የእሚቆጠሩ ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎችን የእሚወስኑ ቢሆንም።

ይኸ ማለት ፦ ዋጋ የኢኮኖሚያዊ ስረዓት ችግሮች ኹሉ ማርከሻ ወይንም የኢኮኖሚያዊ አሻጥሮች ኹሉ ማምከኛ አስማት ነው ለማለት አይደለም። ዋጋ እየሠራ ፦ የገበያ ክፍተት የእሚባል እና ለምሳሌ ፦ ሞኖፖሊ ፣ ተመጣጣኝ ያልሆነ ዋጋ ፣ የስርጭት መዛባት ፣ ወዘተ ሊፈጠር ይችላል።

ሆኖም ፦ ዋጋ እየሠራም የገበያ ክፍተት ሊኖር ቢችልም ፤ ዋጋ በእሚሠራበት ኹኔታ የእሚፈጠሩ የገበያ ክፍተቶች ፤ አፈንጋጭ (Exceptions) ኹኔታዎች እንጂ መዋቅራዊ እና ገዢ አይሆኑም።

ለምሳሌ ፦ ወረድ ብለን እንደ እምናየው ፤ የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አመነጫጨት እና አከፋፈል ፤ በገበያ ስለ እማይመራ ፤ መንግሥት በብዙ ቢልዮን ዶላሮች በብድር ተዘፍቆ የገነባቸው የኃይል ማመንጫዎች ፤ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም ዝቅተኛ የኤሌክትሪክ ሽፋን ቢኖረውም ፤ የመግዛት አቅሙ ግን ዝቅተኛ ስለ ሆነ የእሚመነጨውን ኃይል በሙሉ መግዛት ስለ እማይችል ፤ የማመንጨት አቅሙ ከፊሉ ተቆልፎ ሲቀመጥ ፤ ከፊሉ ደግሞ መብራት በሌለው ኢትዮጵያዊ አናት ላይ እያለፈ ፤ ከኢትዮጵያ የተሻለ የኤሌክትሪክ ሽፋን ላላቸው እንደ ኬንያ ላሉት ሳይቀር ፤ ለጅቡቲ እና ለደቡብ ሱዳን አሁን በቅርቡ ደግሞ ርካሽ ኤሌክትሪስቲ ለክሪፕቶ ከረንሲ እየተሸጠ ነው።

መንግሥት ግን ሲነሳ እና እነ እዚኽ ትልልቅ ኃይል ማመንጫዎች ሲገነባ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኤሌክትሪክ ሳያገኝ እና ኢንደስትሪው ሳይለማ በፊት ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ቸርቻሪ ለመሆን አልነበረም።

ሆኖም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት እና ማሰራጨቱ በገበያ ስለ አልተመራ ፤ መንግሥት የዋጋ ግሽበት እና የዶላር እጥረት ብሎም የባከኑ እድሎች በእሚፈጥር መንገድ ፤ ከፍተኛ ኢንቨስትመን አድርጎ ኃይል ማመንጫ ይገነባል ፤ በእዚኽ መንገድ ኤሌክትሪክ ኃይል አመንጪ በመሆኑ ግን ፤ ሕዝቡን ፦ በዋጋ ግሽበት ፣ በዶላር እጥረት ፣ በስረ ዓጥነት ፣ በገጠሬነት ፣ ወዘተ ስለ አደከመው ፤ ተበድሮ እና ተለክቶ ያመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል ፤ አይደለም ተራው ኢትዮጵያዊ ባለ ኢንደስትሪውም ከእሚፈልገው በላይ በመሆኑ ፤ የብክነት ክምር ሆኗል።

ይኽ ለምን ትልቅ የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ስህተት እንደ ሆነ ለማስረዳት ልሞክር፦

እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ብናየው ፤ በአምራችነት እና በሸማችነት በኢኮኖሚ ውስጥ ስለ እሚሳተፍ ፤ የዋጋ ስረዓቱ ከአጉል መንግሥታዊ ጣልቃ ገብነት ነጻ በሆነ መንገድ እሚሠራ ከሆነ ፤ አምርቶ የእሚሸጠው አገልግሎት ወይንም ምርት ፤ የእሚሸምተውን አገልግሎት ወይንም ምርት መግዛት የግድ የእሚችል መሆን ይኖርበታል።

የዋጋ ስረዓቱ እራሱ የእራሱን የአጋፋሪነት ሥራ ሠርቶ ፤ ዜጋው ለአገልግሎቱ ወይንም ለምርቱ ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግ ፤ እርሱ ሸማች ሆኖ አገልግሎት ወይንም ምርት ለመግዛት የእሚያስችለውን ክፍያ እንዲያገኝ ያደርገዋል።

ከእዚኽም የተነሳ ፤ ለምሳሌ ፦ አንድ የኢትዮጵያ ገበሬ ፤ በወር 200 ኪሎ ዋት ኤሌክትሪክ እሚጠቀም እና ያም 2000 ብር የእሚያስከፍለው ከሆነ እና ያም 2000 ብር 2 መቶ ኩንታል ጤፍ ለማምረት ከእሚያወጣው ወጪ 10 በመቶ ከሆነ ፤ ገበሬው ያን 200 ኩንታል ጤፍ ከ20 ሺ ብር በታች አይሸጠውም።

ሌላው ገበሬ በ10 ሺ ብር 200 ኩንታሉን ቢሸጥስ እሚባል ነገር የለም ፤ አጋፋሪው **<u>አቶ ዋጋ</u>** ፤ እያንዳንዱ ገበሬ 200 ኩንታል ጤፉን ከ20 ሺ ብር በታች እንደ አይሸጥ ያደርጋል።

ወይንም ደግሞ 200 ኩንታል ጤፍ በ20 ሺ ብር ከተሸጠ ፤ ሕዝቡ የመግዛት አቅም ስለ ሌለው ፤ ገበሬው ምርቱን እሚገዛው አያገኝም አይባልም ፤ በተመሳሳይ መንገድ ፤ ጤፍ እሚገዛው ሰው ፤ ገቢው የግድ 200 ኪሎ ጤፍ መግዛት የእሚችል እንዲሆን ገበያው እሚያስገድድበት መንገድ አለው።

ስለ እዚኽ ፦ የኢትዮጵያው ገበሬ ደኃ ስለ ሆነ አይደለም ፤ የኤሌክትሪክ አገልግሎት በዋጋው ገዝቶ መጠቀም የእሚያቅተው ፤ ይልቁንም ፦ የተበላሸ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ፤ የዋጋ ቅዱስነትን በመዳፈር ፤ የዋጋ ስረዓቱን በማዛባቱ ምክንያት ፤ ገበሬው የልፋቱን ዋጋ እንደ አያገኝ ስለ አደረገው ነው።

ዋጋ ከአጉል ጣልቃ ገብነት ነጻ ሲሆን ፤ ለኹሉም ተገቢውን ዋጋ ይሰጠዋል። የግብዓቶችን ዋጋ በትክክል ያሰላል ፣ እጥረት ካለ ቁጠባን ግድ ይላል ፣ ምርቶች ከተወደዱ ተተኪ ምርት ያመጣል ፣ ኃብትን በጥንቃቄ በተሻለው ቦታ ይደለድላል።

ለምሳሌ ፦ ኢትዮጵያን ዕንመልከት ። በኢትዮጵያ ለመላው ሕዝብ የእሚበቃ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት የእሚያችሉ በቂ ወንዞች ፣ ንፋስ ፣ የጸሐይ ብርኃን ፣ የምድር እንፋሎት ፣ ወዘተ ኃብቶች አሉ። እነ እዚኽንም

የተፈጥሮ ኃብቶች እንዴት አድርጎ ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል መቀየር እንደ እሚቻል በቂ ዕውቀት አለ። ይኽንንም ዕውቀት ወደ ሥራ በመቀየር ለመላው ኢትዮጵያዊያን ኃይል የማመንጨት ሥራ ላይ መሠማራት የእሚችሉ ፤ በቂ ሞያተኞቹ አሉ ፤ ከሌሉም እንኳን ማሰልጠን ይቻላል።

ስለ እዚኽ ፦ ከኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት አንጻር ፤ አኹን በሐገራችን ያለውን የጥየቃ (Demand) እና አቅርቦት (Supply) አለመመጣጠንን የፈጠረው ፤ የተፈጥሮ ኃብት ወይንም የሰው ኃብት እጥረት ወይንም ጉድለት አይደለም።

ይልቁንም ፦ እነ እዚኽን ግብዓቶች ወስደው ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል ለመቀየር የእሚያስፈልገውን ኢንቨስትመንት ለማድረግ የእሚወጣውን ወጪ መሸፈን በእሚችል መልኩ ፤ የኢትዮጵያ ገበሬ የኤሌክትሪክ ኃይል መግዛት አይችልም የእሚለው እሳቤ ፤ ከመንሰራፋቱ የተነሳ ፤ በእምንከተላቸው የተሳሳቱ ፖሊሲዎች ምክንያት ፤ የኢትዮጵያ ገበሬን የመግዛት አቅም ከማሳደግ ይልቅ ፤ ኤሌክትሪክን በርካሽ ዋጋ ልናቀርብለት የእምንፈልግ መሆናችን ነው።

ምክንያቱም ፦ ይኽ ከእላይ ሲታይ የሕዝብ ወገንተኝነት የእሚመስል መፍትኼ ፤ የገበሬው የመግዛት አቅም ከማሳደግ ይልቅ ፤ ይባሱንም ምርታማነቱን በመግደል እና ብዙ ስውር ዋጋዎችን በማስከፍል ፤ የመግዛት አቅሙን የእሚያመናምን በመሆኑ ነው።

ስለ እዚኽ ፦ መፍትሔው የአላዋቂ ሳሚ ሆኖ ፤ ዋጋ ለማርከስ በእሚል የሕዝብን የመግዛት አቅም ማዳካም ሳይሆን ፤ ትክክለኛ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ቀርጾ የዜጋውን የመግዛት አቅም ማሳደግ ነው።

## የመግዛት አቅም እሚያድገው ፤ ምርታማነት ሲያድግ ነው

የመግዛት አቅም እንዴት ያድጋል ከተባለ ፤ መልሱ የዜጋው ምርታማነት ሲያድግ እና ምርታማነቱ የገበያ ዋጋ ሲያገኝ ነው ነው።

አንድ የኢትዮጵያ ገበሬን ብንወስደው ፤ ከአንድ የአሜርካ ገበሬ የበለጠ እንጂ ያነሰ አይሠራም። እንዲያውም ከአንድ አሜርካዊ ገበሬ ለእሚበልጥ ሰዓት ፤ በእማይመች እና በአስቸጋሪ ኹኔታ ውስጥ ሊሠራ ይችላል።

ሆኖም ኢኮኖሚ ምን ያኽል ለፋቹ ወይንም ምን ያኽል ደከማቹ ሳሆን በድካማቹ ልክ ምን ያኽል ዋጋ ወይንም እሴት ፈጠራቹኹ በእሚል ስሌት ነው የእሚሠራው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የመሬት ፖሊሲ ፡ መሬትን የገጠር እና የከተማ ብሎ ከፋፍሎ ፤ የግብርና ምርታመነትን ሊያሳድግ በእማይችል መልኩ ስለ አደላደለ ፣ ብሔራዊ ባንካቻን ከመንግሥት ፖለቲካዊ ጫና ነጻ ሆኖ በገበያ በመሥራት በባንኮች መካከል ጤናማ ውድድር እንዲኖር ፣ የወለድ መጠን ተገቢ እንዲሆን ፣ የመንግሥት በጀት አጓጉል እንዳይሆን ስለ ማያደርግ ፣ እንደ እዚኹም ሐገሪቱ ብሎም መንግሥት በዋነኝነት ተወዳዳሪ አምራች ባልሆኑ የልማት ድርጅቶች ምክንያት ከፍተኛ የብድር ጫና ስለ አለባት ፣ ወዘተ ፤ ገበሬው በተበላሸ የማክሮ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ ታግቶ ምርታማነቱን ማሳደግ አልቻለም።

ምክንያቱም ፡- የመንግሥት የተበላሸ ፖሊሲ ፤ የዋጋ ግሽበትን ስለ አናረው ፤ የዋጋ ግሽበት ያለችውንም ቀሪ ኃብት በእየግዜው ይቦረቡርበታል ፣ ግብርናውን ለማስፋፋት ብድር ለማግኘት ብዙ ችግር አለበት ፤ ብድር ቢያገኝም የወለዱ መጠን እሚቀመስ አይደለም ፤ የውጭ ምንዛሪ ችግር ስለ አለ ማዳበሪያ እና ሌሎች የግብርና ግብዓቶች የእሚገዙበት ዋጋ ትርፋማ እሚያደርገው አይደለም ፤ የመሬት ፖሊሲው ትልቅ እርሻ ይዞ ኮሜርሻል ግብርና በመሥራት ስኬል (Scale) ለማድረግ የእሚፈቅድ ወይንም የእሚጋብዝ አይደለም።

ስለ እዚኽ ፡- ምንም እንኳን አንድ የአሜሪካ ገበሬ ፤ ከኢትዮጵያ ገበሬ የበለጠ ባይተጋም ፤ የመከር ወቅት ላይ ግን ፤ አንድ የአሜርካ ገበሬ ፤ ብዙ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ የእሚያርሰው መሬትም ፤ የእሚያርሰው መሬት ብቻ ሳይሆን ፤ በኼክታር የእሚያመርተው የምርት መጠን ከኢትዮጵያ ገበሬ በብዙ እጥፍ ስለ እሚያድግ ፤ ድካማቸው እኩል ካልሆነም የኢትዮጵያው ገበሬ ድካም የእሚበዛ ቢሆንም ፤ ምርታማነታቸው በብዙ እጥፍ ይለያይና ፤ የአሜርካው ገበሬ ከኢትዮጵያው ገበሬ ብዙ እጥፍ የመግዛት አቅም (Purchasing Power) እንዲኖረዉ ይሆናል።

በአጠቃላይ በሐገሪቱ ያለው የማሕበረ ኢኮኖሚ ስረዓት ፤ የገበሬው ታታሪነት የምርት እመርታ እንደ አያመጣ የእሚገታው እና ፈጠራ የእማያበረታታ ነው።

ልማታውያኑ ፤ ገበሬውን በእዚኽ መልኩ ምርታማ እንደ አይሆን አድርጋችኹት ፤ በመዋቅራዊ መንገድ የመግዛት አቅሙን አዳክማችኹታል ሲባሉ ፤ የመግዛት አቅም ስለ ሌለው ነው የእምንደጉመው የእሚለውን መከራከሪያቸውን በመቀየር ፤ ግብርናው በእዚኽ መልኩ በገበያ በመሥራት ምርታማነቱ ካደገ ፤ በጥቂት ገበሬዎች ብቻ ኢትዮጵያን መመገብ ብሎም ምግብ እህል ኤክስፖርት ማድረግ ያስችልና ፤ አኹን ከእጅ ወደ አፍ ግብርና የተሠማራውን ከ11 ሚልዮን በላይ የሆነውን ገበሬ ፤ ከግብርና በማላቀቅ ፤ ሥራ አጥ አድርግ ወደ ከተማ እንዲጎርፍ ያደርገዋልም ይላሉ።

ገበሬው ደግሞ በእዚኽ መልኩ ፤ በሚልዮኖች ወደ ከተማ ሲጎርፍ ፤ የከተማ ሥራ አጥነት ይበራከታል ፣ በከተማ መሠረተ ልማት ላይ ጫና ይበዛል ፣ ወንጀል እና ውንብድና ይበራከታል ፣ ወዘተ ይላሉ።

ይኽ የልማታዊያኑ አስተሳሰብ የእሚዘነጋው ነገር ግን ፤ **የዋጋ አጋፋሪነት** ፤ በግብርና ብቻ የእማይወሰን እና በሐገር ደረጃ እንዲሠራ ከተለቀቀ ፤ በኹሉም የኢኮኖሚ መስኮች ውስጥ የእሚሠራጭ እና እነርሱንም እንደ ግብርናው ምርታማነታቸውን የእሚያሳድግ መሆኑን ነው።

ዋጋ በግብርና ውስጥ ሠርቶ የግብርናውን ምርታማነት በማሳደግ የገበሬውን የመግዛት አቅም እንደ እሚያሳድገው ፤ የግንባታውን መስክ ምርታማነት በማሳደግ መስኩ ብዙ ሠራተኛ እንዲቀጥር እና ብዙ ከተማ እንዲገነባ ያስችለዋል ፣ በፋብሪካ ሠራተኝነት ፣ በእቃ ማጓጓዝ ፣ በመስተንግዶው ፣ ወዘተ ፤ በአጠቃላይ በኹሉም የኢኮኖሚ መስኮች የእሚኖረው ውጤትም ተመሳሳይ ነው የእሚሆነው።

ስለ እዚኽ ፡- ከግብርናው መስክ ወጥቶ የእሚመጣ ከ11 ሚልዮን በላይ የእሚሆን ቤተሰብ አሳዳሪ ገበሬ ፤ የሚገባበት አጥቶ ፤ ከተማ የሚያጣብብ ምን አልባትም የወንጀል እና የልመና አረንቋ የእሚፈጥር

ሳይሆን ፤ በዋጋው የተመረተ ኤሌክትሪሲትን ጨምሮ ሌሎች እንደ ቤት እና ትራንስፖርት ያሉ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን መሸፈን የእሚያስችል ደሞዝ የእሚከፍላቸውን ሥራ ነው የእሚፈጥርላቸው።

## እማይወጣበት ከድኅማ ወደ ኪሳራ የእሚያስገባው አዙሪት

ቀደም ብለን እንደ አልነው ፤ አንድ መንግሥት ፤ ዋጋዎች ከተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ዕውነታው ውጭ በሆነ መንገድ ፤ ዋጋዎችን በግድ የሕዝብን አቅም ያገናዘቡ እንዲሆን ሲያደርግ ውጤቱ ፤ የኢኮኖሚ ፍትኃዊነት በፍጹም አይሆንም።

ይልቁንም ፦ በከፍተኛ ሐገራዊ የዕዳ ጫና ፣ የእሚጋልቡ የዋጋ ግሽበት ፣ ኢንቨስትመንትን እና እድገትን በእሚገድብ ከፍተኛ የወለድ መጠን እና በእሚባባስ የገበያ ክፍተት ምክንያት ፤ ወውጫ የሌለው ኢኮኖሚያዊ አረንቋ ነው የእሚሆነው።

ልክ አንድ ልማታዊ መንግሥት ፤ ዋጋ የሕዝብን አቅም ያገናዘበ እንዲሆን በማድረግ ፍትኃዊ ስረጭት ያለው ኢኮኖሚ እፈጥራለኹ ብሎ ፤ **<u>በታላቁ አጋፋሪ</u>** ሥራ ውስጥ ጣልቃ በመግባት ዋጋን በእሚፈልገው መልኩ ሊመራው ሲፈልግ የእሚከተለው የኢኮኖሚ ጥፋት እና ውድመት ዑደት ይጀመራል ፦



ኺደቱን በናብራራው ፦

1. **ዋጋ ሲረክስ ግዢ ይጨምራል:** የኤሌክትሪክ ዋጋው ገበያ ይሰጠው ከነበረው ዋጋ ሲያንስ ፤ ይኽ በመንግሥት ጣልቃ ገብነት የተቀነሰ ዋጋ ፤ ለነጋዴዎች እና ለመብራት ተጠቃሚዎች የኤሌክትሪክን ዋጋ ከገበያው በታች አርክሶ ስለ እሚያሳያቸው ፤ ኤሌክትሪክ መጥኖ ከመጠቀም ይልቅ ፤ ከእሚያስፈልጋቸው በላይ ያለ ተገቢ ጥንቃቄ በመጠቀም ፤ ብዙ ይጠቀማሉ።

2. **መንግሥት ዋጋ ለማርከስ ወጪ ይጨምራል:** ይኽን የውሸት የዋጋ መርከስ ለማስቀጠል ፤ መንግሥት ፦ ብድር በመበደር ፣ የሠራተኛ ደሞዝ በመቀነስ ፣ አንድ አንዴም ቀጥታ የበጀት ድጎማ ወደ ማድረግ ማለትም ገንዘብ ወደ ማተም ይገባል።

3. **የመንግሥት ድጎማ ቀዳዳ ኪስ ውስጥ ይገባል:** ይኽን ዓይነት ድጎማ እና እገዛ እየወሰደ ርካሽ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የእሚያቀርበው የመንግሥት ተቋም ፤ በቀጣይነት ገቢው ከወጪው ስለ እሚበልጥ ፤ መንግሥት ፦ በመበደር ፣ የሠራተኛ ደሞዝ በመቀነስ ፣ አንድ አንዴም ቀጥታ የበጀት እገዛ በማድረግ የእሚሰጠው ድጎማ ፤ በቀዳዳ ኪስ ውስጥ እንደ ገባ ገንዘብ ወድቆ ይጠፋል እንጂ ተቋሙን እራሱን ችሎ በእግሩ እንዲቆም አያደርገውም። እንዲያውም የአገልግልት አድማሱ በሰፋ ቁጥር የእሚወድቅበት የዕዳ ረመጥ ጥልቀቱ እየጨመረ ነው የእሚኼደው።

4. **መሰል ልማታዊ አካኼዶች የእሚያስከትሉት የማክሮ ኢኮኖሚ ቀውስ:** ጠቅላላ ሐገራዊ ዕዳ እና ጫናውን ያበዛሉ ፣ በብድር የእሚገዙ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ንብረቶች በእርጅና ምክንያት የእሚያደርሱት ክስረት ይጨምራል (depreciation costs climb) ፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ይባባሳል ፣ የዋጋ ግሽበት ይንራል ፣ የብድር ወለድ መጠን ያድጋል ፣ የሥራ አጥነት ቁጥር ይጨምራ ፣ ሐገራዊ ምርታማነት ይቀንሳል ፣ የመንግሥት ግብር የመሰብሰብ አቅም ይቀንሳል ፣ ወዘተ እነ እዚኽ ኹሉ ተዳምረው ፤ የሕዝቡን የመግዛት አቅም ያዳክማሉ። ያን ግዜ ፤ መንግሥት ዞሮ ፤ የሕዝብ የመግዛት አቅም ዝቅተኛ ስለ ሆነ ፤ አቅምን ያገናዘበ ዋጋ ማቅረብ አለብኝ ብሎ ፤ በተገለጸው መልኩ የሕዝቡን የመግዛት አቅም ይባሱን የእሚያዳክሙ አካኼዶች ውስጥ ይገባል።

ይኽ ባዶ የኢኮኖሚ ጽንሰ‍ኃሳባዊ ትንተና ሳይሆን ፤ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ በተግባር እየታየ ያለ የዕለት ተዕለት ዕውነታ ነው።

ዝርዝሩን ወረድ ብለን በቦታው የዕምናየው ሆኖ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) ፤ በፌደራል ኦዲት ኮርፖሬሽን አስመርምሬዋለው ባለው ዓመታዊ ሪፖርቱ መሠረት ፤ ድርጅቱ ከፈረንጆቹ 2018 ጀምሮ እስከ ሰኔ 2025 ድረስ ባሉት 8 ዓመታት በተከታታይ በቢልዮኖች በእየ ዓመቱ ሲከስር ነው የነበረው።

በ2023 የ24.8 ቢልዮን ብር ኪሳራ ደርሶበታል።

በ2024 ምንም እንኳን ገቢው በ21% ቢያድግም የ10 ቢልዮን ብር ኪሳራ ደርሶበታል።

በ2025 ደግሞ የእሚያስደነግጥ የ122 ቢልዮን ብር ኪሳራ ደርሶበታል።

በእዚያው ዓመት አንጋፋ ከእሚባሉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች መካከል ፦ የኢትዮጵያን ኤሌክትሪክ ኃይልን ጨምሮ ፣ ኢትዮ ቴሌኮም (ቴሌ) ፣ የስኳር ኮርፖሬሽን ፣ የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ፣ ወዘተ ከንግድ ባንክ ተበድረውት የነበረውን በጠቅላላ 900 ቢልዮን ብር ፤ በአግባቡ መክፈል ባለመቻላቸው ፤ ባንኩን ለከፍተኛ አደጋ አጋልጠውት ነበር።

ከእዚኽ 900 ቢልዮን ብር ብድር ውስጥ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዕዳ 217 ቢልዮን ብር ነበር።

በኢትዮጵያ ሐገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በእሚል ፤ የብር ምንዛሪ በገበያ እንዲወሰን ማድረግን ጨምሮ የተለያዩ ዓይነት የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የተደረጉት ፤ አይኤምኤፍ (IMF) በእነ እዚኽ የልማት ፕሮጀክቶች እና በጠቅላላው የመንግሥት የገንዘብ አጠቃቀም ምክንያት በኢትዮጵያ ማክሮኢኮኖሚ ውስጥ የተፈጠረውን የማክሮ ኢኮኖሚ በርካታ ችግሮች ለማስታገስ የእሚረዳውን የብድር እገዛ የእማደርገው ፤ ለምሳሌ ፦ የውጭ ምንዛሪ በገበያ እንዲወሰን ካደረጋችኹ ፣ የመብራት ታሪፍ ከጨመራችኹ ፣ በእነ እዚኽ ፕሮጀክቶች ምክንያት በንግድ ባንክ ላይ አደጋ የጋረጠውን 900 ቢልዮን ብር እዳ ከዘጋችኹ ፣ ከብሔራዊ ባንክ እና ከጡረታ ፈንድ ያለ ምንም ወለድ እና ግዴታ ዘግናችኹ የወሰዳችሁትን ገንዘብ ወደ በንድ በመለወጥ በእዳ ከያዛችኹ ፣ ወዘተ በማለቱ ነበር።

በእዚኽ ኺደትም ፦ ንግድ ባንክን ለአደጋ ያጋለጠው እና መንግሥት በሐገር በቀሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ምክንያት (Because of the homegrown economic reform ) እንዲከፍለው ከተጠየቀው 900 ቢልዮን ብር ውስጥ 217ቱ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) የተሰጠ ብድር ነበር።

ስለ እዚኽ ፦ ለምሳሌ ፦ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) ፤ በእየ ዓመቱ 20 እና 30 ቢልዮን ብቻ አይደለም የእሚከስረው ፤ ይልቁንም ከንግድ ባንክ የተበደረውን ወደ 217 ቢልዮን ብር የእሚጠጋ ብድርም ባግባቡ መክፈል ስለ አልቻለ ፤ ይኽንን ብድር መንግሥት መክፈል ነበረበት።

መንግሥት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን 217 ቢልዮን ብር ጨምሮ በጠቅላላው 900 ቢልዮን የንግድ ባንክ እዳ በመክፈል ፤ እንደ ቴሌ እና የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ባሉ የልማት ድርጅቶች ምክንያት በንግድ ባንክ ላይ ተደቅኖ የነበረውን አደጋ አነሳ ማለት ግን ምን ማለት ነው ?

መልሱ ፦ መንግሥት እዳውን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) ወደ እራሱ አዙሮ ፤ በእየ ሶስት ፣ አምስት ፣ ወዘተ ዓመቱ በግብር ከእምሰበስበው እና ከውጭ ከእማገኘው እርዳታ ወይንም ብድር ፤ ከእነ ወለዱ እከፍላለኹ ማለት ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ፤ ሕዝቡ አቅም የለውም እና በርካሽ አገልግሎት ላቀርብለት ይገባል በእሚል የገባበት ቀውስ ፤ በእዳ እየተዘፈቁ እዳቸውን ወደ እርሱ የእሚያስተላልፉ የልማት ድርጅቶች ብቻ አይደሉም ችግሩ።

ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፤ መልሳለኹ በእሚል ፤ ምንም ወለድ የእማይከፍልበት በብዙ ቢልዮን የእሚቆጠሩ ገንዘቦችም ይወስዳል ። በእዚኽ መልክ በጠቅላላው ወደ 670 ቢልዮን ብር ወስዷል ከብሔራዊ ባንክ።

አብሮም ከግል እና ከመንግሥት ሠራተኞች የማሕበራዊ ዋስትና ድርጅት ፤ የሠራተኞቹን ጡረታ ያለ ምንም ወለድ እየወሰደ ይጠቀም ነበር። በእዚኽ መልኩ ከተቋማቱ ከማሕበራዊ ዋስትና ድርጅቶቹ የወሰደው ጠቅላላ ገንዘብ ወደ 395 ቢልዮን ገደማ ነው።

የአይኤምኤፍን(IMF – International Monetary Fund) ብድር ያስገኘው ፤ ሐገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ የእሚባለው ማሻሻያ ከሠራው ሥራ አንዱም ፤ እነ እዚኽን በጠቅላላው ከ1 ትሪልዮን በላይ የእሚሆኑ ፤ ከብሔራዊ ባንክ እና ከኢትዮጵያ ሠራተኞች የጡረታ ቁጠባ ፤ ያለ ምንም ወለድ በመንግሥት እየተወሰዱ ፤ መንግሥት ለተለያዩ የልማት ሥራዎች ያውላቸው የነበሩ ገንዘቦችን ፤ መንግሥት ወለድ የእሚከፍልባቸው ዕዳዎች እንዲያደርጋቸው ማስገደድ ነበር።

የአይኤምኤፍን(IMF – International Monetary Fund) ድጋፍ እና ብድር ያስገኘው ማሻሻያ ፤ መንግሥት እነ እዚኽን ስልጣኑን ተጠቅሞ ያለ ምንም ወለድ የእሚወስዳቸውን ብሮች ፤ በወለድ እንዲወስዳቸው ማስገደድ ያስፈለገውም ፤ መንግሥት ያለ ዋጋ የእሚያገኛቸውን መሰል ገንዘቦች ወስዶ ፤ ርካሽ አገልግሎት አቀርባለኹ በእሚል ፤ አክሳሪ ፕሮጀክት ላይ እያዋላቸው ፤ የዋጋ ግሽበት እና የወለድ መጠን እያሳደገ ፤ ማክሮ ኢኮኖሚውን የበለጠ በማበላሸት የሕዝቡን የመግዛት አቅም የባሳ እንደ አያዳክም ነው።

ለምሳሌ ፦ ወደ 395 ቢልዮን የእሚጠጋውን የጡረታ ገንዘብ ወስዶ ፤ በ13 ዓመት በ9% ወለድ ተከፍሎ የእሚያልቅ ቦንድ ወይንም የጡረታ ፈንዱ ለመንግሥት ያበደረው ብድር አድርጎ ሲቀይረው ፤ የጡረታ ፈንዱ የመንግሥት ታጋች ስለ ሆነ ነው እንጂ ፤ ይኽን ገንዘብ ገበያ ይዞት ቢወጣ ፤ ከ9% በላይ ወለድ የእሚያገኝበት ነው።

በእዚያ ላይ ፤ የሐገሪቱ የዋጋ ግሽበት ከ9% በላይ በሆነበት ኹኔታ ፤ በ9% ወለድ ይኽን ያኽል ገንዘብ ለመንግሥት ማበደር ፤ የጡረታ ፈንዱን ገንዘብ አቅም ከዓመት ዓመት እያዳከመበት ነው እሚኼደው።

እንበል እና በእየ ዓመቱ ያለው የዋጋ ግሽበት 10% ከሆነ ፤ ያ 395 ቢልዮን ብር ፤ የመግዛት አቅሙ በእየ ዓመቱ በ1% እየቀነሰ ነው ፤ የመንግሥትን ቦንድ ከመግዛት የእሚያገኘው ወለድ 9% ብቻ በመሆኑ።

ይኽም ለጡረተኞች የእሚከፍለው ክፍያ ፤ ከዋጋ ግሽበቱ ጋር የተናበበ እንደ አይሆን በማድረግ ፤ በቀጥታ የጡረተኞቹን የመግዛት አቅም ያዳክማል።

በጠቅላላው ፦ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ የመግዛት አቅሙ ደካማ ነው እና አቅሙን ያገናዘበ የመብራት እና የስልክ የመሳሰሉ አገልግሎት የእሚሰጡት የንግድ ተቋማት ላቋቁምለት ሲል ፤ ተቋማቱ ከወጭያቸው ባነስ መልኩ አገልግሎት እንዲያቀርቡ ስለ እሚያደርጋቸው ፤ ተቋማቱ እየከሰሩ ወይንም እየተመናመኑ በርካሽ የእሚያቀርቡትን አገልግሎት ሕዝብ በስፋት እየተጠቀመ ሲኼድ ፤ የተቋሙ ኪሳራ ከእለት ወደ እለት እየበዛ ነው የእሚኼደው።

እነ እዚኽ ተቋማት እሚከስሩት ክስረት ደግሞ ፤ ከእላይ እንደ ታየው በቢልዮኖች ስለ እሚሆን እና ብዙ ግዜም የዶላር ብድር ስለ እሚኖርባቸው ፤ መንግሥት ይኽን ኪሳራ በአንድም በሌላ መንገድ መሸፈን አለበት።

ከእላይ እንደ አየነው ፤ ይኽን ኪሳራ ለመሸፈን ፦ የተቋማቱን የባንክ እዳ ወደ ራሱ ያዞራል ፣ ገንዘብ ያትማል (ከብሔራዊ ባንክ መበደር ማለት ገንዘብ ማተም ነው) ፣ የግል ባንኮችን አስገድዶ ብር አበድሩኝ ይላል ፣ የጡረታ ቁጠባን ያለ ወለድ ይጠቀማል ፣ ከውጭ ሐገር ይበደራል ፣ አላግባብ ግብር ይጨምራል ፣ ወዘተ ።

በአጠቃላይ የምርት ዋጋ ያልሆነ ፤ ከፍተኛ መጠን ያለው የሐገር ውስጥ እና የውጭ ገንዘብ ኢኮኖሚ ውስጥ በቀጥታ ይረጫል ፤ ይኽም በምርት እና በገንዘብ አቅርቦት መካከል አለመመጣጠን ስለ እሚፈጥር እና ብዙ ገንዘብ ትንሽ ምርት እንዲኖር ስለ እሚያደርግ ፤ ብዙ ገንዘብ ትንሽ ምርትን ማሳደድ ውስጥ ይገባሉ።

ውጤቱም ፦ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ፣ ከፍተኛ የወለድ መጠን ፣ ለነጋዴ እና ለዜጋ የእሚሆን ብድር እጥረት ፣ የግብር መጠን ማሽቆልቆል ፣ የእዳ ጫና መብዛት ፣ የሥራ አጥነት ቁጥር መጨመር ፣ ተደማምረውም የመላ ዜጋውን የማምረት አቅም ማዳከም ይሆናል።

በእነ እዚኽ መዋቅራዊ ችግሮች ምክንያት ፤ የማምረት አቅሙ የተዳከመው ዜጋም ፤ በቀጥታ አብሮ የመግዛት አቅሙ ይዳከማል።

መጽሐፉ ፤ ውሻ ወደ ትፋቱ ፥ አሳማም ከታጠበ በኋላ በጭቃ ይንከባለላል እንደ እሚል ፤ የኢትዮጵያው መንግሥትም ፤ በእራሱ ጥፋት የመግዛት አቅሙን ያዳከመውን ሕዝብ ፤ የመግዛት አቅም ስለ ሌለው ፤ አገልግሎት በርካሽ ላቅርብለት ብሎ ፤ የተበላሸ የ900 ቢልዮን ብር እዳ የእሚፈጥር ዓይነት ፤ አክሳሪ ፕሮጀክቶች ውስጥ በመግባት ፤ በእሚፈጥረው የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ፤ የሕዝቡን የመግዛት አቅም ይባስ በማዳከም ፤ የሕዝብ የመግዛት አቅም መዳከም እና የማክሮ ኢኮኖሚ ቀውስ መውጫ የሌለው አዙሪት ውስጥ ይገባል።

# 3 ኤሌክትሪክ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ግዜ በጀነሬተር የእሚመነጭ ኤሌክትሪሲቲ ማግኘት የተጀመረው ፤ አጼ ምንሊክ በእኛ በ1880ዎቹ (በፈረንጆቹ በ1980 ዎቹ መጨረሻ አከባቢ) ከጀርመን በመጣ ጀነሬተር ኤሌክትሪክ አመንጭተው ፤ ቤተመንግሥታቸውን የዘመናዊ መብራት ተጠቃሚ ሲያደርጉ ነው።

በዓለም ላይ ፤ ኤሌክትሪሲቲ ትርጉም ባለው መልኩ በሥራ ላይ መዋል የጀመረው በፈረንጆቹ 1882 ኒውዮርክ ውስጥ በመሆኑ ፤ አጼ ምንሊክ በፈረንጆቹ በ1890ዎቹ በቤተመንግሥታቸው ኤሌክትሪክ ሲያስገቡ ፤ ከኒዎዮርክ ቢበዛ በ10 ዓመት ብቻ ዘግይተው ነው የነበረው።

ሆኖም ፦ ታሪካዊ የሆነውን የኢትዮጵያዊያን የዘመናዊ ሕዝባዊ መንግሥት አስተሳሰብን ጉድለት በእሚያሳይ መልኩ ፤ ጣልያኖች በኹለተኛው የኢትዮጵያ ወረራቸው ወቅት ፤ ማለትም ፦ ከአርባ ዓመታት ገደማ በኋላ ፤ የመጀመሪያውን ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብ በአቃቂ ወንዝ እስኪ እስኪ ገነቡ እና ኤሌክትሪክን የተሻለ ተደራሽነት እንዲኖረው እስኪያደርጉ ድረስ ፤ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ከቤተመንግሥት ማድመቂያነት አልፎ ፤ ለሕዝብ ለመዋል የወጣበት ኹኔታ አልነበረም።

ጣሊያኖች ከተባረሩ በኋላ ፤ እንደ እሚመስለው ፤ ግድቡን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እያስተዳደረው ቆየና በኋላ ግድቡ ላይ የማስፋፊያ ሥራ በመሥራት ፤ አቅሙ ትንሽ እንዲጨምር ተደረገ እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ብርኃን እና ኃይል ባለሥልጣን (EELPA – Ethiopian Electric Light & Power Authority) የእሚባል እና ኃይል የማመንጨቱን ፣ የማስተላለፍ ፣ የማሰራጨቱን ፣ እንደ እዚኹም የመቆጣጠሩን ሥራ የእሚሠራ ባለስልጣን መሥሪያ ቤት በፈረንጆቹ በ1956 ተቋቋመ።

ከእዚያ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ብርኃን እና ኃይል ባለሥልጣን (EELPA – Ethiopian Electric Light & Power Authority) ለ40 ዓመት ከአገለገለ በኋላ ፤ በዘመነ ኢሕአዴግ ማለትም በፈረንጆቹ 1996 ፤ የመቆጣጠሩን ሥራ እና ኃይል አመንጭቶ የማከፋፈሉን ሥራ የእሚሠራ በእሚል በኹለት ተከፍሎ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ባለስልጣን (Ethiopian Electric Authority) በተቆጣጣሪነት ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን (EEPCO – Ethiopian Electric Power Corporation) በኃይል አመንጭቶ አስተላላፊነት እና አከፋፋይነት ተቋቋመ።

እንደገና በፈረንጆቹ 2014 ፤ ኃይል የማመንጨቱን ሥራ እንዲሠራ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP – Ethiopian Electric Power) ፤ የማከፋፈሉን ሥራ እንዲሠራ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEU – Ethiopian Electric Utility) በእሚል እንደገና እንደ አዲስ ተዋቀረ።

በአጭሩ ተቋሙ ፤ ተቆጣጣሪም ነጋዴም ፤ ከሆነበት ተቆጣጣሪ ለብቻ እና ነጋዴ ለብቻ ወደ ሆነበት ፤ አኹን መጨረሻ ላይ ደግሞ ኃይል አመንጪ እና አገልግሎት ሻጭ በእሚል በኹለት ተከፍሎ እንደ ገና ተዋቅሯል።

ስለ እዚኽ ፡- በኢትዮጵያ ከኢሌክትሪክ ጋር በ1890 የተዋውቅን እና ቢያንስ ከፈረንጆቹ 1956 ጅምሮ እስከ ዛሬ ለ72 ዓመታት የቆየ ፤ ኤሌክትሪሲቲን በተደራጀ መልኩ አመንጭቶ ለሕዝብ የማድረስ ታሪክ አለን።

በቅኝ ግዛት ሥር ሆነው ፤ ከአፍሪካ የደቡብ አፍሪካዋ ኪምበርሊ እና በኋላ ላይ ግብጽ እንደ እዚኹም በዛንዚባር የኦማን ሱልጣኖች ብቻ ናቸው ከኤሌክትሪክ ጋር በመተዋወቅ የእሚቀድሙን። የኤሌክትሪክ አገልግሎት በተደራጀ መልኩ ማመንጨት ብቻ ሳይሆን ተቋም አቋቁመን ስንመራው ደግሞ 72 ዓመታችን ሲሆን ፤ ይኽም ከበርካታ የአፍሪካ ሐገራት ነጻነት በፊት ነው።

ከእዚኽ ኹሉ ግዜ በኋላ ግን ፤ አፈጻጸማችን በፍጹም ታሪካችንን የእሚመጥን ሲሆን አይታይም።

የዓለም ባንክ ፤ NATIONAL ENERGY COMPACT FOR THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA ብሎ ባወጣው ሪፖርት ላይ ፤ በጥር 2025 በተደረገ ጥናት ከተገኙ መረጃዎች መካከል ፤ የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ስርጭት የእሚገኝበትን ኹኔታ ከእዚኽ በታች በቀረበው መስሎ አስቀምጦታል ፡-

- በሐገሪቱ 65% የእሚሆኑት ቤቶች አንድ ዓይነት የኤሌክትሪክ ምንጭ አላቸው።
  - ከእዚኽ ውስጥ 29.3% የእሚሆኑት ከሐገራዊ ግሪድ (National Grid) ወይንም መንግሥት አመንጭቶ ከእሚያከፋፍለው የእሚገኝ ሲሆን ፥
  - 35.7%ቱ ደግሞ ከሐገራዊ ግሪዱ ውጭ በሆነ መልኩ ከጸሐይ ኃይል የእሚገኝ ኤሌክትሪሲቲ ነዉ።
- ሆኖም 44% የሆነው የሐገሪቱ ሕዝብ ብቻ ነው ፤ ከአምፖል ያለፈ ለምሳሌ ፡- ስልክ ቻርጅ የእሚያደርግ ፣ ምግብ የእሚያበስል ፣ ወዘተ ኤሌክትሪክ የእሚያገኘው።
  - ይኽም ማለት 56 በመቶ የእሚሆነው ወይንም ከ60 ሚልዮን በላይ ኢትዮጵያዊ መሠረታዊ የሆነ የኤሌክትሪክ አገልግሎት አያገኝም።
- በእዚያ ላይ 92% የእሚሆነው ኢትዮጵያዊ ፤ በኩበት ፣ በእንጨት ፣ ወዘተ በመሳሰሉት ባዮማስ (Biomass) የእሚባሉትን ነገሮች በማንደድ ነው ምግብ የእሚያበስለው። ይኽም ብዙዎችን ለጤና አደጋ አጋልጧል ፤ አብሮም የደን ጭፍጨፋን አበራክቷል እንደዚኹም ሐገራዊ ምርታመነትን ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጓል።
- ቆጣሪ ኖሯቸው ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር ደንበኛ የሆኑ የጠቅላላ ደንበኞች ቁጥር 3.135 ሚልዮን ነው።

አብሮም ይላል ዓለም ባንክ ፡- ደካማ የማቀድ አቅም ፣ ደካማ የቁጥጥር አሠራር እና ደካማ ተቋማዊ ቁመናዎች ፤ የኤሌክትሪክ መስኩ በኢትዮጵያ ፤ ደካማ የመለወጥ ተስፋ እንዲኖረው የእሚያደርግ በመሆኑ ፤ የ2030 ሐገራዊ የኤሌክትርክ ሽፋንን 75% የማድረስ ህልሙ ፈተና ተዳርጎበታል።

በአንጻሩ ሥራ ብዙው የኢትዮጵያ መንግሥት ፤ ብሔራዊ ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅሜን በጣም ስለ አሳደግኹ ፤ ኤሌክትሪክ ኃይል እየሸጥኹላት ነው የእሚላት ኬንያ ፤ ከኢትዮጵያ በጣም በእሚሻል ደረጃ ላይ ነች።

በእዚኹ የኢትዮጵያን መረጃን ያመጣንበት የዓለም ባንኩ የNATIONAL ENERGY COMPACT ሪፖርት መሠረት ፤ ኬንያ ያላት አፈጻጸም ይኽን ይመስላል ፦

- ኬንያ 2014 ላይ 29% የነበረውን የሐገሯን የኤሌክትሪክ ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ አሳድጋ በ2024 75% አድርሳዋለች (አኹን 76% አልፏል)።
    - ከእዚኽ ውስጥ 65% ከዋናው ግሪድ ኤሌክትሪሲት የእሚያገኝ ነው።
    - 0.84% ከትንንሽ ግሪዶች የእሚያገኝ ነው።
    - 9.2% ብቻ ፤ ከዋናውም ከትንንሾቹም ግሪድ ውጬ ነው።
- ምንም ዓይነት የኤሌክትሪክ ሽፋን የእማያገኘው የኬንያ ሕዝብ 25% የእሚሆነው ብቻ ነው።
- 69% ኬንያዊ እንጨት እና መሰል ነገሮችን በማቃጠል ነው ምግብ እሚያበስለው።
- ትናንሽ የግል ኃይል አከፋፋዮችን ሳንቆጥር ከዋናው የኬንያ ኃይል እና መብራት ኮርፖሬሽን ጋር ቀጥታ ደንበኝነት ያላቸው ደንበኞች ብዛት 10 ሚልዮን ነው።
- በመስኩ የኬንያ ፈተና ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ከውጬ ለመግዛት የእምትከፍለው የውጬ ምንዛሪ እና ከሐገር ውጬ ባለ ኃይል ላይ መደገፍ ነው።

| | ኢትዮጵያ | ኬንያ |
|---|---|---|
| ጠቅላላ ሽፋን | 65% | 76% |
| ከዋናው ግሪድ የእሚገኝ | 29.3% | 65% |
| ከሶላር እና ከሌሎች የእሚገኝ | 35.7% | 10.04% |
| ኤሌክትሪክ እማያገኝ ሕዝብ በፐርሰንት | 35% | 25% |
| በባዮማስ ምግብ የእሚያበስል በፐርሰንት | 92% | 69% |
| ቆጣሪ ያላቸው ደንበኞች | 3.135 ሚልዮን | 10 ሚልዮን |

በኹለቱ ሐገራት መካከል ያለው ልዩነት ፤ 65% እና የ76% በእሚል በተቀመጠው የጠቅላላ ሽፋን ልዩነት የእሚገለጽ አይደለም።

ምክንያቱም ፦ ዝርዝሩን ለበኋላ አቆይተን ፤ እዚኽ መግቢያው ላይ በቀረበው መረጃ ብቻ ፤ የኬንያ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ እና እጅግ በተሻለ መጠን ኤሌክትሪክ እንደ እሚያገኝ ፤ ከዋናው ግሪድ ጋር የተገናኘው ኢትዮጵያዊ 29% ብቻ መሆኑ እና በአንጻሩ የኬንያ 65% መሆኑ ፤ እንደ እዚኹም ከኬንያ የኹለት እጥፍ በላይ ሕዝብ ባላት ኢትዮጵያ ፤ በሐገሪቱ ብቸኛ በሆነው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደንበኛ የሆነው ብዛት 3.135 ሚልዮን ብቻ መሆኑ እና በአንጻሩ በኬንያ የእዚኽ 3 እጥፍ ሆኖ ከ10 ሚልዮን በላይ መሆኑ ፤ የኬንያ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ፥ እጅግ የተሻለ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ እንደ ሆነ ነው የእሚያሳየን።

በእዚያ ላይ ፤ ኢትዮጵያ በ2030 ተስፋዬ የዛሬውን የኬንያ ደረጃ መደረስ ነው ብላ ስትል ፤ ኬንያ ደግሞ ተስፋዬ የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ተደራሽነት 100% ማድረግ ነው ትላለች።

በእዚኽ ላይ ይበልጥ የሚያሳስበው ፤ የኢትዮጵያው አካኼድ ተደራሽነቱን 75% የማድረግ ሕልሙ የመሳካቱ ጉዳይ አጠራጣሪ ሲሆን ፤ የኬንያው ግን ዓለም ዓቀፍ ለጋሾች እና ዕርዳታ ሰጪዎች ይስማሙበታል።

# 4 በኢትዮጵያ ዘመናዊ የኤሌክትሪክ መስክ ፈተናዎች

ካልተሳሳትኩ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ፤ በሐገራችን የኤሌክትሪክ መስኩን ለማዘመን እና ለማሳደግ የእሚደረገው ጥረት ፤ በጣም ከፍተኛ እና ምን አልባትም ከአፍሪካ ተወዳዳሪ የእማይገኝለት ነው ፤ የእሚል ዕምነት ነው ያለው።

በተለይ ደግሞ ፤ የሕዳሴ ግድብ ሲጀመር የፈጠረው ከፍተኛ መነቃቃት እና በኋላ ላይ ደግሞ ያው መነቃቃት ሕወሐት በሙስና አበላሸው እና ብልጽግና መጥቶ አስጨረሰው ፣ ወዘተ መባሉ ፤ በእዚያ ላይ ፤ የሕዳሴው ግድብ ኃይል የማመንጨት አቅሙ እና ጉዳዩ ከግብጽ ፖለቲካ ጋር የተያያዘበት አግባብ ፤ የሕዳሴን ግድብ ፋይዳ በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ አዕምሮ ውስጥ ፤ ከሳውዲ አረብያ የነዳጅ ጉድጓዶች በላይ ፤ እጅግ የከበረ እና ትልቅ ሳያስመስለው አይቀርም።

በእዚያ ላይ ፤ ኢሕአዴግ አዲስ አባባ ከገባ በኋላ ፤ የሕዳሴው ግድብ ፤ በኤሌክትሪክ መስክ ቁንጮው ሥራው ነው እንጂ ፡-

- የተከዜ ግድብ ፥
- የግቤ ተከታታይ ሶሥት ግድቦች ፥
- አሁን ብልጽግና እኔ ባልመጣ ኖሮ ትልቅ አደጋ ይገጥመው ነበር የእሚለው የኮይሻ ግድብ ፥

ለኢትዮጵያዊያን የፈጠሩት ደስታም ቀላል ቦታ እሚሰጠው አይደለም።

ከውኃ ግድቦች አንጻር ድርሻቸው በጣም ትንሽ ቢሆንም ፤ በእየ ግዜው ፤ በእየ ቦታው የእሚተከሉት የንፋስ ኃይል ማመንጫዎች እንደ እዛው በሕዝቡ ዘንድ የራሳቸውን እርካታ ፈጥረዋል።

በእዚያ ላይ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኩባንያ ኤሌክትሪክ ፡- ለደቡብ ሱዳን ፣ ለኬንያ ፣ ለጅቡቲ ፣ ኃይል እየሸጠ መሆኑ እና ወደ ፊትም የተለያዩ የአፍሪካ ሐገራት ኃይል የመሸጥ ዕቅድ ስለ አለው ፤ በመስኩ የአፍሪካ ተስፋ የሆንን ይመስል ይሆናል።

የሐገራችን ፖለቲከኞች የራሳቸውን ፈተና እራሳቸው አርመው ፤ ለራሳቸው ትልቅ ውጤት የእሚሰጡ በመሆኑ ፤ ይኽ ግንዛቤ እና ዕይታ ፤ በሕዝቡ ዘንድ ብቻ ሳይሆን ፤ ምን አልባትም ፡- የኢሕአዴግም ሆነ የብልጽግና ሰዎችም የእሚኩራሩበት ይመስላል።

በእርግጥ በእየ ግዜው የነበረው እና የአለው የመብራት መቆራረጥ ፤ ሕዝቡን አያማርርም አይደለም ፤ በአብዛኛው የኃይል መቆራረጡ ፤ ከአስተዳደር ችግር እና ከኋላ ቀር የስርጭት ገመዶች ወዘተ ጋር እየተያያዘ ስለ እሚታይ ፤ በመስኩ የእሚደረገው ከፍተኛ ኢንቨትመንት የፈጠረውን ፤ ደስታ እና እርካታ ፤ አደብዝዞታል ማለት ይከብዳል።

ለእዚኽ ጽሑፍ ስዘጋጅ እንደ አገኘኹት መረጃ ግን ፤ በጠቅላላው ከኃይለ ሥላሴ ጀምሮ ፤ የኢትዮጵያዊያን በሽታ በሆነው አንድ የአስተሳሰብ ግድፈት ምክንያት ፤ ጥሎብን ምንቸት ጋን የማሳከል ችግር ስለ አለብን እንጂ ፤ በኤሌክትሪክ መስኩ እንደ ሐገር ካሳካነው ስኬት ይልቅ ያጠፋነው ጥፋት በብዙ እጥፍ የእሚበልጥ እና ምን አልባትም አካኼዳችንን ካልቀየርን ፤ ለለውጥ ያለን ተስፋ የተመናመነ መሆኑን የእሚያሳይ ነው።

በጠቅላላው በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መስክ ምን እየሆነ ነው ከተባለ ፦ ጅልነት እንደ ጥበበኝነት ፣ ብክነት እንደ ዕድገት እየተወሰደ ፤ የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መስክም ሆነ ኢትዮጵያ እንደ ሐገር ፤ ተስፋ ያለው ሐገር የመሆን ዕድሏን እየቆመረችበት ነው።

ይኽም እንዴት ነው እየሆነ ያለው ከተባለ ፦

- ኃይል ለማመንጨት ፤ ከእሚያስፈልገው በላይ የብድር ጫና ሐገር ላይ በመፍጠር ፥
- የሐገር ውስጥ የገንዘብ ገበያን በእሚያጠፋ መልኩ የሐገር ውስጥ ገንዘብን በመርኽ አልባ መንገድ ኃይል ለማመንጨት በመጠቀም ፤ የሐገርን ማክሮኢኮኖሚ ከግዜ ወደ ግዜ በማበላሸት ፥
- ከእሚያስፈልግ በላይ ከፍተኛ የሠራተኛ ቁጥር በመያዝ ፥
- በእዚኽ እና ተያያዥ ምክንያት ፤ የሕዝቡን ኤሌክትሪክ የመግዛት አቅም በማዳከም እና የኢንደስትሪ ልማትን በማዳከም ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ሐገር ማዘመኛ ሳይሆን ሐገር ማዝበጫ እና ማጉበጫ እንዲሆን ፤

በማድረግ ነው።

ይኽን ጠቅለል ተደርጎ የተቀመጠ የመስኩን ትችት ፤ በአኹን ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEU – Ethiopian Electric Utility) በመባል ተከፋፍለው ፤ የኤሌክትሪ ኃይል በማመንጨት ፣ በማስተላለፍ እና በማከፋፈል ሥራ ላይ የተሠማሩት የመንግሥት ተቋማት ፤ በፈረንጆቹ ከ2018 ጀምሮ በአወጡት ኦዲት የተደረገ ዓመታዊ ሪፖርታቸው ላይ በመመሥረት እና ለንጽጽር በጎረቤት ኬንያ ፤ ኬንጄን (KENGEN) የእሚባለው እና ኤሌክትሪክ በማመንጨት ብቻ ላይ የተሠማራውን እና ኬፒሊሲ (KPLC – Kenyan Power and Light Corporation) የተባለውን እና ኤሌክትሪክ በማከፋፈል ላይ ብቻ የተሠማራውን ድርጅት የ2024 እና የ2025 ዓመታዊ ሪፖርት በመጠቀም ፤ በዝርዝር እንመልከት።

## 4.1 የኪሳራ ውርጅብኝ

ኹለቱም ፦ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEU – Ethiopian Electric Utility) ፤ የኪሳራ ውርጅብኝ ውስጥ ናቸው።

የተቋማቱን የክስረት መጠን ፤ በእሚቀጥለው ሰንጠረዥ ዕንመልከት (ቁጥሮቹ በቅንፍ ውስጥ ሲቀመጡ ኪሳራ ወይንም ተቀናሽ ማለት ነው)፡-

| የሒሳብ ዓመት (በፈረንጆቹ) | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEU – Ethiopian Electric Utility) |
|---|---|---|
| 2025 | (122,079,764,000.00) | 4,053,504,837.00 |
| 2024 | (10,147,553,000.00) | 3,723,803,193.00 |
| 2023 | (24,838,797,000.00) | 2,322,691,162.00 |
| 2022 | (30,101,938,000.00) | 2,589,890,014.00 |
| 2021 | (22,794,538,000.00) | 1,314,222,306.00 |
| 2020 | (29,651,469,000.00) | 1,505,650,371.00 |
| 2019 | (27,270,677,000.00) | 785,650,113.00 |
| 2018 | (25,036,632,000.00) | (2,503,032,684.00) |

ከሰንጠረዡ እንደ ዕሚታየው ፤ ከፈረንጆቹ 2018 እስከ 2025 ባሉት 8 ዓመታት ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) ትንሹን ኪስራ እርሱም 10 ቢልዮን ብር የከሠረው በ2024 ነው።

በጣም ትልቁን ኪሳራ የከሠረው ደግሞ በ2025 ነው ፤ 122 ቢልዮን ብር በመክሰር።

እንዲያውም በእዚያ ዓመት ለቢትኮይን ማይኒንግ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው እና በመላ ሐገሪቱ ውስጥ ከእሚሸጠው ኤሌክትሪሲቲ ጋር የእሚመጣጠን ሽያጭ ስለ አከናወነ ነው እንጂ ፤ ምን አልባት ኪሳራው 180 ቢልዮን ብር በላይ ሊሆንም ይችል ነበር።

ከእዚያ በተረፈ ግን በስድስቱም ዓመታት ዝቅተኛ ሲባል 22 ቢልዮን ከፍ ሲል ደግሞ 30 ቢልየን ብር ድረስ በእየ ዓመቱ እየከሠረ ነው።

በአንጻሩ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEU - Ethiopian Electric Utility) ፤ በፌደራል ኦዲት ኮርፖሬሽ ኦዲት ተደርጎ የወጣውን የተቋሙ ሪፖርት ስናይ ፤ ከ2018 በስተቀር ባሉት 7 ዓመታት ከ785 ሚዮን ብር እስከ 4 ቢልዮን ብር አትርፏል።

ሆኖም ወደ ትርፉ ሪፖርቱ ዝርዝር ውስጥ ተገብቶ ሲታይ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEU - Ethiopian Electric Utility) ከሰባቱ በአራቱ ማለትም ፡- በ2024 ፣ 2021 ፣ 2020 ፣ እና 2019 ትርፋማ ሆኖ መቆየት የቻለው ፡-

- ተቋሙ የእሚከተለው የሒሳብ አያያዝ ዘዬ ፤ የውጭ አጋዞች ብድር ከገበያ ባነሰ የወለድ መጠን ሲሰጡት ፤ ብድሩን ከገበያ በገበያ ወለድ መጠን ቢበደረው ኖሮ ይከፍል የነበረውን የወለድ መጠን

- ልዩነት ፤ እንደ ገቢው አድርጎ ሪፖርት እንዲያደርግ የሚያዘው በመሆኑ (Concessional Loan Discount – as Income) እና ያንን ፥ የሌለ ነገር ግን ቢኖር ኖሮ ገቢ ተብሎ ሪፖርት የሚደረግ ምናባዊ ገቢ እንደ ትክክለኛ ገቢ ቆጥሮ ገቢ ብሎ ሪፖርት ስለ እሚያደርግ እና
- ለቆርያለው ከሚሸጣቸው ፦ የተቆራረጡ ብረቶች ፣ አሮጌ ዕቃዎች ፣ ወዘተ የሚያገኘውን የተለያየ ገቢ (Miscellaneous which includes income from sales of scrap metals, disposal of assets and others) ፤ ገቢ ብሎ ፤

ሪፖርት በማድረጉ ነው።

ኦዲት አስደርጎ ካወጀው ሪፖርቱ ላይ እነ እዚኽን ኹለት ገቢዎች ስንቀንስ ፤ ድርጅቱ በእነ እዚያ አራት ዓመታት ማለትም ፤ በ2024 ፣ 2021 ፣ 2020 ፣ እና 2019 ፤ በሚከተለው መልኩ ከስሮ ነው የምናገኘው፦

| የሒሳብ ዓመት (በፈረንጆቹ) | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEU – Ethiopian Electric Utility) | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ትርፍ ፤ የድጎማ ገቢዎች ከተቀነሱ በኋላ |
|---|---|---|---|
| 2025 | (122,079,764,000.00) | 4,053,504,837.00 | 2,235,531,865.00 |
| 2024 | (10,147,553,000.00) | 3,723,803,193.00 | (1,931,731,693.00) |
| 2023 | (24,838,797,000.00) | 2,322,691,162.00 | 658,864,681.00 |
| 2022 | (30,101,938,000.00) | 2,589,890,014.00 | 648,729,525.00 |
| 2021 | (22,794,538,000.00) | 1,314,222,306.00 | (705,585,628.00) |
| 2020 | (29,651,469,000.00) | 1,505,650,371.00 | (412,949,892.00) |
| 2019 | (27,270,677,000.00) | 785,650,113.00 | (452,560,845.00) |
| 2018 | (25,036,632,000.00) | (2,503,032,684.00) | (3,055,825,756.00) |

ለንጽጽር ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEU – Ethiopian Electric Utility) ትይዩ የሆኑትን የኬንያ ፤ ኬንጄን (KENGEN) እና ኬፒኤልሲ (KPLC) የ2025 እና የ2024 ዓመታዊ የትርፍ ሪፖርት እንመልከት።

ንጽጽሩን ትክክል ለማድረግ ፤ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) እና በኬንያ ኃይል የማመንጨት ሥራ በሚሠራው ኬንጄን (KENGEN) መካከል ያለውን ልዩነት ማስቀመጥ ተገቢ ነው።

ልዩነቱም ፦ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) ኃይል የማመንጨት ሥራ ብቻ ሳይሆን ከ130KV በላይ የሆኑ የማስተላለፊያ መሥመሮችን በባለቤትነት ይዞ ሲያስተዳድር ፤ የኬንያው ኬንጄን (KENGEN) እነ እዚኽ ከፍተኛ ኃይል የሚያልፍባቸውን ማስተላለፊያዎች በባለቤትነት ይዞ የማስተዳደሩን ሥራ ኬትራኮ (KETRACO) ለተባለ ድርጅት ስለ ሰጠው ፤ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) በይዘቱ ይለያል።

በአጭሩ ፡- በኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) ኃይል የማመንጨት እና ኃይል የማስተላለፉን ሥራ ይሠራል ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEP - Ethiopian Electric Utility) የማከፋፈሉን ሥራ ሲሠራ።

በኬንያ ግን ፡-

- ኃይል የማመንጨቱን ሥራ ኬንጄን (KENGEN) ይሠራል ፣
- ከፍተኛ ቮልቴጅ ያላቸውን የማስተላለፊያ መስመሮች የመገንበት እና የማስተዳደር ሥራ ኬትራኮ (**KETRACO**) ይሠራል ፣
- መንጭቶ የተላለፈውን ኃይል ለደንበኛ የመሸጡን ወይንም የማከፋፈሉን ሥራ ኬፒሌሲ (KPLC) ይሠራል።

በመሆኑም ፡- አወቃቀሩ ይኽን መሠል ልዩነት ስለ አለው ፤ ንጽጽሩ ይኽን ከግምት ማስገባት አለበት።

እንደገናም የኢትዮጵያው በብር ሪፖርት ሲደረግ የኬንያው በሽልንግ ነው ፤ ቢሆንም የኬንያው ሽልንግ የዶላር ምንዛሪ ከ2024 በኋላ ከኢትዮጵያ ብር ጋር ተመጣጣኝ በመሆን ጀምሮ ፤ አኹን ከኢትዮጵያ ብር በላይ የጠነከረ በመሆኑ ፤ ንጽጽሩ የኬንያዎቹን ኩባንያዎች በተሰሰተ ንጽጽር ጠንካራ አድርጎ አያሳያቸውም።

እነ እዚኽን ካልን ፤ በመቀጠል በፈረንጆቹ 2024 እና 2025 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና ኬንጄን ከትርፋማነት አንጻር የነበራቸውን ውጤት እንይ ፡-

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) በ 2025 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Power) በ2024 | ኬንጄን (KENGEN) በ2025 | ኬንጄን (KENGEN) በ2024 |
|---|---|---|---|---|
| የትርፍ መጠን | (122,079,764,000.00) | (10,147,553,000.00) | 10,481,077,000.00 | 6,797,012,000.00 |

በአንጻሩ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪ አገልግሎት እና የኬንያው አቻው KPLC ንጽጽር ይኸን ይመስላል፡-

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEP - Ethiopian Electric Utility) በ 2025 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP - Ethiopian Electric Utility) በ2024 | ኬፒኤልሲ (KPLC – Kenyan Power and Light Company) በ2025 | ኬፒኤልሲ (KPLC – Kenyan Power and Light Company) በ2025 |
|---|---|---|---|---|
| የትርፍ መጠን | 4,053,504,837.00 | 3,723,803,193.00 | 24,466,525,000.00 | 30,080,370,000.00 |

የአፍሪካ የውኃ ማማ ነኝ በእምትለው እና ከራሴ ተርፌ ለአከባቢዬ ሐገራት ኤሌክትሪክ ኃይል በመሸጥ ላይ ነኝ የእምትለው ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል አመንጪ ኩባንያ ብላ ያቋቋመችው ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) ኩባንያ ፤ ከዓመት ዓመት ለስምንት ዓመታት ፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያውቀው ቀርቶ ሊረዳው የእሚያስቸግረውን ዓይነት ፣ አንድ ግዜ 10 ቢልዮን ፣ በሌላ ግዜ ደግሞ 30 ቢልዮን ፣ ሲከፋበት ደግሞ 122 ቢልዮን ብር በዓመት ሲከስር ፤ የጎረቤት ኬንያው ኃይል አመንጪ ኬንጄን (KENGEN) በእየ ዓመቱ 10 እና 7 ቢልዮን ሽልንጎች ያተርፋል።

በእዚያ ላይ ፤ የኬንያው ኃይል አመንጪ ኬንጄን (KENGEN) በዓመት በቢልዮኖች የእሚያተርፈው ፤ በኬንያ ገበያ ውስጥ ያለው ኃይል የማመንጬት ድርሻ 56% ብቻ ሆኖ ነው። እንደ እምናውቀው በኢትዮጵያ ውስጥ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) ብቸኛው የኃይል አመንጪ ነው።

ስለ እዚኽ ፤ የኢትዮጵያው ኤሌክትሪክ አመንጪ ኩባንያ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪ ኃይል (Ethiopian Electric Power) ሙሉ ገበያውን ተቆጣጥሮ እና ብቸኛ ሞኖፖሊ ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል የእሚያቀርብላቸው ደንበኞች ብዛት ፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ግማሽ የእሚሆን ጠቅላላ ሕዝብ ባላት ኬንያ አንጻር ፤ ከእርሱ ከግማሽ በላይ የመደበኛ ደንበኛ እያገለገለ ፤ በቢልዮኖች በእዚክ መልኩ እየከሰረ መሆኑ ፤ ንጽጽሩን ያጎላዋል።

በአንጻሩ ፤ የኬንያ ኹለት እጥፍ ሕዝብ ባላት ኢትዮጵያ የእሚገኘው እና እራሱን የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለደንበኛ አከፋፋይ ነኝ የእሚለው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (Ethiopian Electric Utility) ፤ ትርፍ አተረፍኩ ብሎ የእሚለውን እራሱ ሳንከራከር እንደ ትርፍ ብንወስድለት ፤ ከኬንያው ኬፒኤልሲ (KPLC) ከ6 እስከ 10 እጥፍ ያነሰ ትርፍ ነው የእሚያተርፈው ፤ ምንም እንኳን የኬንያ ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግማሽ ቢሆንም።

በ2025 የኬንያው ኬፒኤልሲ (KPLC) 24 ቢልዮን ሽልንግ ሲያተርፍ ፤ የእኛው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት 4 ቢልዮን አትርፏል ፤ በ2024 ኬፒኤልሲ (KPLC) 30 ቢልዮን ሲያተርፍ የእኛው 3.7 ቢልዮን ብር አትርፏል።

በእርግጥ የኬንያው የኤሌክትሪክ ኃይል አከፋፋይ ኬፒኤልሲ (KPLC) ፤ እስከ ቅርብ ግዜ ልክ እንደ ኢትዮጵያው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (Ethiopian Electric Utility) ብቸኛው አከፋፋይ ነበር ፤ ምንም እንኳን አኹን አዲስ ሕግ ወጥቶ ፤ በቅርቡ ከኹለት በላይ አዳዲስ ኩባንያዎች በተወዳዳሪነት ሊገቡ ቢሆንም።

በጠቅላላው ፡- አገልግሎት አቅራቢ ኬፒኤልሲ (KPLC) ፤ በኬንያ ገበያ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ቢኖራቸውም ፤ በኬንያ የኤሌክትሪክ ገበያ ውስጥ እንደ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና አገልግሎት ፤ ብቸኛ ኩባንያዎች አይደሉም።

## 4.2 የኪሳራው ምንጬ ርካሽ እና አቅምን ያገናዘበ ታሪፍ አይደለም

"የኪሳራ ውርጅብኝ" በእሚለው ክፍል 4.1 ላይ እንደ ዓየነው ፤ ተቋማቱ በከፍተኛ ክስረት ላይ ናቸው። ካልሆነም የእሚያተርፉት ትርፍ ከኢንቨስትመንታቸው አንጻር በጣም ዝቅተኛ ነው።

እንደ አይኤምኤፍ (IMF) ያሉትን አጋር እና የእርዳታ ድርጅቶች ጨምሮ አብዛኛው የጉዳዩ ተንታኝ የሰማን እንደ ሆን ደግሞ ፤ ለእዚኽ ዓይነቱ የተቋማቱ ክስረት እና ከፍተኛ የእዳ ጫና ምክንያቱ :- የሕዝቡን አቅም ለማገናዘብ በእሚል ፤ ተቋማቱ ማለትም ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ በከፍተኛ ኪሳራ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለበርካታ ሕዝብ ስለ እሚሸጡ ነው።

ይኽ ዓይነቱ ግምገማ ግን ፤ የመንግሥትን ሰማዕትነት በማግነን የችግሩ ዋንኛ ምንጬ የሆነውን የመንግሥትን የፖሊሲ ጉዳዮች መኃይምነት የእሚጋርድ ነው።

ምክንያቱም ፡- ጥሩ የመነሾ እና የውጤት ትንተና ካደረግን ፤ የችግሩ ምንጬ የመንግሥት ድኅማ ብለን አናቆምም።

በትክክል ዑደቱን እናስቀምጠው ካልን እንደ እሚከተለው ነው እሚሆነው ፡-




ስለ እዚኽ ፡- ልማዳዊው የችግሩ ምንጬ ትንተና ፤ የሕዝቡ የመግዛት አቅም መዳከምን ፤ የችግሩ መነሻ አድርጎ ነው የእሚያቀርበው ።

የሕዝቡ መግዛት አቅም ግን በተፈጥሯዊ ወይንም ታሪካዊ ምክንያት አይደለም የተዳከመው ፤ ምክንያቱም ፡- በአፍሪካ እንኳን በጣም ዝቅተኛ የእሚባለውን የኤሌክትሪክ ዋጋ መክፈል እስኪያቅተው ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ከሌላው የአፍሪካ ሕዝብ እንኳን ባነሰ መልኩ የመግዛት አቅሙ እንዲዳከም የእሚያደርገው ምንም ዓይነት ተፈጥሯዊ ወይንም ታሪካዊ ምክንያት ማግኘት አይቻልም።

ይልቁንም ፡- ባሕሪያዊ ወይንም ልማዳዊ በሆነው የሐገራችን የዘመናዊ መንግሥት እሳቤ ጉድለት የተነሳ ፤ የሐገራችን መንግሥታት በተከታታይ በተከተሉት የተበላሸ ፖሊሲ ምክንያት ፤ የሕዝቡ የመግዛት አቅም ፤ አይደለም በዓለም ላይ ፤ በአፍሪካ እንኳን ርካሽ የእሚባለውን ኤሌክትሪክ ያለ ድኅማ መግዛት እንደ አይችል ስለ አደረገው ነው።

ከእዚያም ከእላይ እንደ አያችሁት ነገሩ አዙሪት ይሆንና ፤ የተበላሸ የመንግሥት ፖሊሲ የመግዛት አቅሙ የተዳከመ ሕዝባዊ ኹኔታ ይፈጥራል ፤ ያንን ክፍተት ለመሸፈን መንግሥት የድኅማ ረመጥ ውስጥ ይገባል ፤ የመንግሥት ድኅማ ተቋማቱን ማክሰር ብቻ ሳይሆን የሕዝቡን የመግዛት አቅም የበለጠ ያደክማል ፤ በእዚኽ መልኩ የተፈጠረው የሕዝቡ የመግዛት አቅም መዳከም ደግሞ መንግሥት ሕዝቡ የመግዛት አቅሙ ደካማ ነውና ይደጎምን ያስከትላል ፤ ይኽም አዙሪት እራሱን እያሽከረረ ይደግማል።

የእዚኽ ዓይነቱ ግምገማ ወይንም ትንተና ችግር ደግሞ ዋነኛ የችግሩ ምንጬ የመንግሥት ፖሊሲ ሳይሆን ዋንኛ የችግሩ ምንጬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪካዊ ወይንም አንዳች ዓይነት አስገዳጅ ድህነት እንደ ሆነ ማስመሰል ነው።

ዕውነታው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ እንደ ኬንያ እንኳን ካሉ የአፍሪካ ሐገራት አንጻር በልዩ ኹኔታ ድኃ እሚያደርገው ፤ ታሪካዊ ወይንም አስገዳጅ ኹኔታ የሌለ በመሆኑ ፤ ችግሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድህነት ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግሥታት ፍልስፍና ነው ማለት ይቻላል።

ይኽን ከአጼ ምንሊክ ዘመን ጀምረን ለማየት እንሞክር፡-

ቀደም ባለው ክፍል ላይ ለማሳየት እንደ ሞከርኩት ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ኤሌክትሪሲቲ ፤ ልክ ዓለም ላይ ኤሌክትሪሲቲ መስፋፋት በጀመረበት ግዜ ገብቷል ማለት ይቻላል ፤ ምክንያቱም ፡- ኒዎርክ ውስጥ ኤሌክትሪሲቲ ከገባ ከ10 ዓመታት በኋላ ፤ የአጼ ምንሊክ ቤተመንግሥትም ከጀኔረተር በእሚመነጬ ኤሌክትሪስቲ ደምቋል።

ይኸው ኤሌክትሪሲቲ ግን ከቤተመንግሥት ወጥቶ ሕዝብ ጋር እስኪደርስ ከ40 ዓመታት ያላነሰ ግዜ ወስዷል። በእዚያ 40 ማለትም ከ1877 እስከ 1917 ባለው እና በአሜሪካ ታሪክ ጊልድድ ኤጅ (Gilded Age) ወይንም ወርቃማው ዘመን በእሚባለው ዘመን አሜርካ ፤ ከኋላ ቀር ኢኮኖሚ ወጥታ በኢንደስትሪያላይዜሽን አማካኝነት ታላቅ ብልጽግና ውስጥ የገባችበት ነበር።

ምን አልባትም የጣሊያን ወረራ ባይመጣ እና ወራሪው ጣሊያን በቃሊቲ ወንዝ ላይ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ የነበረውን አባ ሳሙኤል የእምንለውን የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድብ ባይገነባ ኖሮ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ማስፋፊያ ከእዚያም ሊዘገይ ይችል ይሆናል።

በአንጻሩ ፤ ኢትዮጵያን ከአሜሪካ ሳይሆን ፤ ከጎረቤታችን ኬንያ ስናስተያይ ፤ ኤሌክትሪስቲ ቤተመንግሥት ማድመቂያ ሳይሆን የሕዝብ መጠቀሚያ ሲሆን እናያለን።

እንደ እሚታወቀው ፡- ኬንያ ብሎም መላው ምስራቅ አፍሪካ ፤ እንደ ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የራስ ገዝ ወይንም የሉዓላዊነት ፖለቲካዊ ታሪክ የሌለው እና በልማዳዊ የነገዳዊ ጥርቅምነት ሲኖር ካልሆነም በተለያዩ ቀኝ ገዢዎች ሥር በመቆየቱ ፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይለያል።

ሆኖም ፡- ኢትዮጵያዊያን ረጅም የመንግሥትነት ታሪክ ያላቸው መሆኑ እና የረጅም ዘመን የመንግሥትነት ፍልስፍናቸው ዘመናዊነትን መላበስ ስላቃተው ፤ ከዘመናዊነት አንጻር የእሚጠቅማቸው ሳይሆን ፤ የእሚጎዳቸው ነው የሆነው።

ምክንያቱም ፡- አጼ ምንሊክ እና የእርሳቸውን ዘመን የኢትዮጵያን ፖለቲከኞች የእሚገዛው እሳቤ ፤ በታሪካዊ ፖለቲካዊ ማዕበል ምክንያት ፤ የተቀነጣጠበባቸውን እና ከእጃቸው የወጣውን ፤ የአባቶቻቸውን ዳር ድንበር ማስመለስ እንጂ ፤ በኢትዮጵያ ዘመናዊ መንግሥትን ማቆም አይመስልም።

የማዘመን ጥረት አያደርጉም አይደለም ፤ ይልቁንም "ፈጣን" ዘመናዊነትን ፖለቲካዊ ግዴታ የእሚያደርግባቸው ፖለቲካ የለም ወይንም የሐገሪቱን ፖለቲካ እንደ እዚያ አድርገው አይገነቡም።

ትልቅ ሐገራዊ የፖለቲካ አቅም ገንብተው ፤ መላ የሐገሪቱን አቅም እራስን ለመከላከል እና ግዛታዊ አንድነትን ማስጠበቅ ላይ ያውሉትና ፤ በእዚያ ኺደት የፈጠሩት አስፈሪ የመንግሥት አቅም ፤ እጃቸው ላይ ቢያንኳርፉ እንኳን ፤ ዘመናዊነት አምጡ ብሎ ሊያስገድዳቸው ይቅርና ቀና ብሎ ሊያያቸውም እማይችል ይሆናል።

ከእዚኽም የተነሳ ፤ አይደለም የአፍሪካ ሐገራት ፤ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ፤ አይደለም ሊያስበው ሊመኘው የእማይችለው ፤ ግዛታዊ አንድነት እና አስተዳደራዊ ነጻነት አስከብሮ መኖር የእሚችል መንግሥት ቢኖርም ፤ ይኸ መንግሥት ግን ፤ አይደለም ከሌላው የዓለም ሕዝብ ፤ ከአጎራባቹ እንደ ኬንያ ካሉ ሕዝብ አንጻር እንኳን በኋላ ቀር የልማት ደረጃ ላይ የእሚገኝ ሕዝብን ያስከትላል።

ባጭሩ የመንግሥት ስልጣን ጥንካሬ ልማት ማምጣትን ግዴታ አያደርግበትም ። ልማት የመንግሥት ቸርነት እንጂ አስገዳጅ ፖለቲካዊ ኹኔታ አይሆንም ፤ ምክንያቱም ፦ የኢትዮጵያ መንግሥት በታሪክ ፤ ማንም አያስገድደውም።

ከልማት አንጻር ፤ በኢትዮጵያ ፦ የመንግሥት ጥንካሬ እድል ሳይሆን እዳ ነው የሆነው።

በአንጻሩ ፦ በምስራቅ አፍሪካ ፤ ምንም እንኳን እንደ ኢትዮጵያ የሐገራዊነት ታሪክ ባይኖርም እና የፖለቲካ ስልጣኑ ፤ በቀኝ ገዢ ኃይሎች በአርጩሜ የእሚቀጣ ባሕላዊ የነገድ መንግሥት ስለ ነበር እና ቀኝ ገዢዎች ደግሞ በባሕሪ ደረጃ ቀዳሚ ግባቸው ኃብት መሰብሰብ በመሆኑ ፤ ምንም እንኳን ኤሌክትሪሲቲ አጼ ምንሊክ በገባበት ግዜ አከባቢ የቀኝ ገዢዎች ቤተመንግሥታቸው ውስጥ ኤሌክትሪሲቲ ቢገባም ፤ ከሉዓላዊቷ ኢትዮጵያ ቀድሞ ለምሳሌ ፦ የናይሮቢ ከተማ መንገዶች በመብራት አሸብረቀው ነበር።

የኬንያን የኤሌትርፊኬሽን ታሪክ ስናይ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ታሪክ ፤ ዛሬ ከየመን በስትመስራቅ ፤ ከኢምሬት እና ከየመን መካከል የእሚገኙት የኦማን ሱልጣኖች ፤ የፖርቹጋል ካቶሊኮች የምስራቅ አፍሪካ የባሕር ጠረፍ አከባቢ ነዋሪዎችን ከእስልምና ወደ ክርስትና ካለተለወጣችኹ በእሚል እና በተለያየ ጭቆና ምክንያት በማስመረራቸው ፤ በተደረገላቸው ግብዣ መጥተው ፤ ፖርቹጋሎችን አባረው ፤ ዛሬ ኬንያ እና ታንዛኒያ ድንበር ላይ የእሚገኙት የዛንዚባር ደሴቶች ላይ ቤተመንግሥት ከመመሥረታቸው ጋር ይገናኛል ፦




http://www.globalsecurity.org/military/world/gulf/images/map-oman-1856.jpg

በኋላም ላይ የዛንዚባር ውበት እና የቅመም ንግድ አመቺነት ከባሪያ ጉልበት ወዘተ ጋር ተዳምሮ ፤ ሱልጣኔቱ መናገሻውን ወደ ዛንዚባር እንዲያዞር ፤ በኋላም ከኦማን ተነጥሎ የዛንዚባር ሱልጣኔት እንዲሆንም አድርጎት ነበር።

ይኸም የዛንዚባር ሱልጣን ፤ ሱልጣን ሰይድ ባርጋሽ በ1875 እንግሊዝን ከጎበኘ በኋላ ፤ በእንግሊዝ ያየውን ቴክኖሎጂ ወደ ዛንዚባር ለማምጣት ጉጉት ስለ አሳደረበት ፤ ከሞላ ጎደል አጼ ምንሊክ ቤተመንግሥት ውስጥ የመጀመሪያው ጀኔርተር በገባበት ማለትም በ1890ዎቹ አከባቢ ፤ ሱልጣን ሰይድም ኤሌክትሪሲቲ እና ሊፍት ስለ አለው ፤ የተዓምር (የአጃይብ) ቤት (*Bait al-Ajaib* or House of Wonders) ተብሎ በተሰየመው ቤተመንግስቱ በ1880ዎቹ መጨረሻ ወይንም በ1890ዎቹ መጀመሪያ አከባቢ ኤሌክትሪሲቲ አስገባ።

በአጭሩ ፦ እንደ ሞምባሳ እና ላሙ ያሉ የዛሬዋን ኬንያ ወደቦች እንደ ሞቃድሾ ካሉ የሶማሊያ ከተማዎች ጋር ጨምሮ የሚቆጣጠረው የዛንዚባር ሱልጣኔት ፤ ምን አልባት አስር በማይሞሉ ዓመታት ከአጼ

ምንሊክ ቀድም ብሎ ወይንም ከአፄ ምንሊክ ጋር ተቀራራቢ በሆነ ግዜ አሌክትሪክን ፤ በምስራቅ አፍሪካ አስገብቷል።

ወቅቱን ከታሪክ አንፃር ከአየነው ፤ እነ ራስ መኮንን ሐረር የገቡበት ፤ አውሮፓን የጎበኙበት ፤ የአደዋ ጦርነት የተደረገበት ወዘተ አከባቢ በመሆኑ ፤ የኢትዮጵያ ሊህቃን ከኦማን ሱልጣኖች ያነሰ ንቃት ነበራቸው ማለት አይቻልም።

በእዚያ ላይ ፤ ኢትዮጵያ የአደዋ ጦርነትን ለማሸነፍ ያሳያቸው የፖለቲካ ልቀት ፤ በአውሮፕ ሰላዮች እስከ ማሰማራት እና በተለያየ መንገድ የጦር መሰሪያ አቅም ለመገንበት ፥ ወዘተ የኼድችበት መንገድ ፤ አይደለም የእዚያን ዘመን የእዚኸኛውን ዘመንምም ፖለቲካ የእሚወዳደር ነው።

እንዲኸ ዓይነት ሐገር የመከላከል እና ነፃነቱን የማስጠበቅ ታላቅ የሴራ ፖለቲካ ብቃት ያለው የኢትዮጵያ መንግስት ግን ፤ ይኸን አቅሙን ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማምጣት ሲጠቀምበት አይታይም።

ምክንያቱም ፦ በተመሳሳይ ግዜ ኤሌክትሪክ በምስራቅ አፍሪካ ፤ ማለትም ፦ በኢትዮጵያ እና በዛንዚባር[1] ቢገባም ፤ ምንም እንኳን በኦማን ሱልጣኔት እና በእንግሊዝ ነጋዴዎች አማካኝነት ቢሆንም ፤ ይኸን የጀኔረተር ኤሌክትሪሲቲ ፤ ነጋዴዎቹ ከቤተመንግስት አውጥተው ፤ እስከ 1908 መጀመሪያ ሞምባሳን በኋላም ናይሮቢን እንደ ከተማ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ማድረግ ችለዋል።

እንደ እኔ ግምት ይኸ የሆነው ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ፤ በጥንካሬው ምክንያት ፤ አንድ የዓለም አካል እንደ ሆነ ሳይሆን የእራሱ ዓለም እንደ ሆነ ያኸል ፤ እራሱን ከቅርብ ጎረቤቶቹ እንኳን ተወዳዳሪ ሳያደርግ ስልጣኑን አስጠብቆ መኖር የእሚችል በመሆኑ ይመስለኛል።

ወደ ዘመናዊ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ስንመጣ ደግሞ ፤ ይኸ አይበገሬው የኢትዮጵያ መንግሥት ተጠያቂነት ልፍጠር ብሎ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ሲፈቅድ ፖለቲካው ፦

ኑሮን ከማሸነፍ ሙግት ማሸነፍ እና ጥገኝነት የተጠናወተው ይመስላል።

ለምሳሌ ፦ በኬንያ ፦ ኬንያ የ3 ሺ ዓመት ታሪክ ነው ያላት ወይንስ 150 ዓመት በእሚል ዓይነት የሞኝ ክርክር ሳይጠመድ ፤ ቀኝ ግዛት በፈጠራት ኬንያ ፤ እንዴት ኤሌክትሪክ ከመሸጥ ገንዘብ ማግኘት እንችላለን በእሚል እሳቤ ተንቀሳቅሶ ፤ ከኤሌክትሪፊኬሽን አንጻር የተሻለ ውጤት ሲያዝመዘግብ ፤ በኢትዮጵያ ግን ፤ ምንሊክ ነው ኢትዮጵያን የፈጠራት ወይንስ ኢትዮጵያ የ3 ሺ ዓመት ታሪክ ነው ያላት የእሚለውን ጥያቄ ሰማይ ቤት ኼዶ ማስመለስ ወይንም የፖለቲካ ስልጣኑን ይዞ ዕውነቱ ኢትዮጵያ የ150 ዓመት ብቻ ታሪክ ነው ያላት ወይንም የ3 ሺ ዓመት ታሪክ ነው ያላት ማለት ዋንኛ የፖለቲካ አጀንዳ ሆኖ ፤ ኤሌክትሪፊኬሽን ሶስተኛ እና አራተኛ ጉዳይ ይሆናል።

ለኢትዮጵያዊው ፖለቲከኛ በሙግት ማሸነፍ ፤ ኑሮን ከማሸነፍ እሚበልጥበት ይመስላል።

[1] ዛንዚባር የእሚባሉት በዋናነት ኹለት ትላልቅ ከሞምባሳ በታች ያሉ ደሴዮች እና ተጓዳኝ ሌሎች የደሴት ስብዝቦች ናቸው ፤ አሁን ቀድሞ ታንጋኒካ ከእምትባለው ግዛት ጋር በመቀላቀል የታንዛንያ አካል ሆነዋል።

በሙግት ከተሸነፈ ፤ ድሎት ሰቀቀን እሚሆንበት ፤ ካሸነፈ ደግሞ ቆሎ ቆርጥሞም ደስ ብሎት እሚኖር ይመስላል የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባሕል።

በእርግጥ ፤ ለምሳሌ ፦ የልማታዊ መንግሥት እሳቤ ወይንም የደርግን የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ወዘተ አንድ ሰው ሲሰማ ፤ ፖለቲካው አፈሙዙን ወደ ልማት ያዞረ ሊመስል ይችላል።

እንደ እኔ ዕይታ ግን ፤ እነ እዚኽ መስመሮች በአግባቡ ከተመረመሩ ፤ ቅድሚያ እሚሰጡት ፖለቲካዊ በቀልን እና የታሪክ ሒሳብ ማወራረድን እንጂ ፤ ከእጼዬ ወጥቶ ወደ ፊት መኼድን ወይንም ኢትዮጵያን ምንሊክ ፈጠራት አልፈጠራት ወይንም የቱ አከባቢ ተወላጅ ከፍ አለ አላለ ሳይሆን ፤ ዋነኛ የፖለቲካ ማጠንጠኛው ሆኖ ነው።

የየትኛውም ሐገር ፖለቲካ እንደ እዚኽ ዓይነት እኔ እሻል እኔ እሻል አለው ፤ ሆኖም እንደ ኢትዮጵያ ግን ፤ እኔ እሻል እኔ እሻሉ ፤ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ከሆነ እና እኔ ለማሸነፍ እርሱ በኹሉም መስክ መሸነፍ አለበት ፤ ማለትም ፦ የፖለቲካ ስልጣን ይዤ እርሱን ካላስራብኩት ወይንም ካላሰርኩት ወይንም በጦርነት ካልጠበስኩት የፖለቲካ ስልጣን የያዝኩ እማይመስለን ነገር ካልተፈታ ፤ ልማታዊነት ልበጣ እንጂ ልማት አይሆንም።

ለእዚያም ነው ፦ ኢትዮጵያ ውስጥ ፤ የፖለቲካ ስልጣን መያዝ ማለት የፖለቲካ ባላንጣ ፦ ስደት ፣ ውርደት እና እንግልት ወይንም የፖለቲካ ስልጣን ማጣት ማለት ከሞት የከፋ ነገር እንደ አይሆን ለማድረግ እና እራሳችንን ከዜሮ ድምር ፖለቲካ አዙሪት ለማውጣት ብቸኛው መንገድ ፤ የነጻነት ዴሞክራሲ እና ነጻ ገበያ ነው ብዬ እማስበው።

ኢሕአዴግን ብትሰሙት ልማታዊ ነኝ ይላል ፤ የጠባብ ብሔርተኝነት ፖለቲካ እና የአንድ አናሳ ንዑስ ፖርቲ የበላይነት ባለበት ግን ፤ ኢሕአዴግ የእሚለው ዓይነት አምባገነናዊ ልማታዊ መንግሥት እንኳን አይሠራም።

ብልጽግናም ብልጽግና ህልሜ ነው ይላል ፤ በእዚኽ የጠባብ ብሔርተኝነት የሕግ እና የክልል መዋቅር እና የድግስ አብዮት ግን ብሔራዊ ብልጽግና ግን የእሚታሰብ አይደለም።

ስለ እዚኽ ፦ ወሬያቸውን ትተን በተግባራቸው ከመዘናቸው ፤ የዘመናዊ ኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ፤ ፊንፍኔ እቴጌ ጣይቱ ፤ የፍል ውኃን ፊን ፊን ለማለት ያወጡት የእራሳቸው ስያሜ እንጂ የአዲስ አበባ ስም አይደለም ቢባል ፤ ይኽን ለመደበቅ ፤ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ፤ የስድድብ አውደ ርዕይ ፣ ወዘተ ሊያደርጉ ይችላሉ።

በአጭሩ የመንግሥት ስልጣን ሕዝብ ማገልገያ ከመሆኑ በፊት ሙግት ማሸነፊያ ነው ፤ ብዙውን ግዜ ፤ ምን ያለበት ምን አቅልም እንደ እሚባል ፤ ሙግት ለማሸነፍ የእሚታገሉት ሰዎችም ዕውነት የላቸውም።

ከእዚኽ የተነሳ ፦ ከአለም ቀድመን ጀምረን ፤ አይደለም ከአለም ከኬንያ እንኳን ኋላ ኋላ እየተከተልን ያለነው።

ኬንያዊያን ምንም እንኳን እንደ ኢትዮጵያ የኮራ እና የደራ ታሪክ ባይኖራቸውም ፤ በቀኝ ግዛት ወረራ ተፅዕኖ ስር ለረጅም ዘመን በመቆየት ፤ ለዓለም ዓቀፍ ፖለቲካ እና የንግድ ልምድ በመጋለጣቸው ፤ ያ

የኮርፖሬት ማኔጅመንት ችሎታቸውን ከፍ እንዲያደርጉ አድርጎ ፤ ከመሰል የኢትዮጵያ ተቋማት የተሻለ ዘመናዊ የንግድ አስተዳደር ጥበብ አዳብረዋል።

ይኸንም ለምሳሌ ፦ የኢትዮጵያን የኤሌክትሪ ኃይል ማመንጨት እና ማከፋፈል መስክ ከኬንያው ተመሳሳይ ኢንደስትሪ ጋር በማነፃፀር በግልፅ ማየት ይቻላል።

እኔ እንደ እምረዳው ፦ የኬንያ ሕዝብ ፤ በታሪክ ሆነ በሐገራዊ ተፍጥሮ ኃብት ወይንም በዜጎቹ ስልጣኔ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቢያንስ እንጂ የእሚሻል አይደለም ፤ ሆኖም ፦ የኬንያ ሕዝብ ለኤሌክትሪክም ሆነ ለምሳሌ ፦ ለቴሌኮም አገልግሎት ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሻለ የመክፈል አቅም አለው።

ስለ እዚኽ ፦ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ከኬንያ ሕዝብ አንፃር እንኳን ፤ ኤሌክትሪክ የመግዛት አቅሙ እንደ እዚኽ የተዳከመው ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከኬንያ ሕዝብ አንፃር ፤ ድኃ የእሚያደርገው ተፈጥሯዊ ምክንያት በመኖሩ ሳይሆን ፤ ኋላ ቀር የሆነ የሐገራችን የማሕበረ ኢኮኖሚ እሳቤ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመግዛት አቅም ከማሳደግ ይልቅ ፤ ከእላይ ለማስቀመጥ በተሞከረው መልኩ ፤ መንግስት ለራሱም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የኢኮኖሚ ቀውስ ረመጥ የእሚፈጥር ፤ ያልዘመነ የፖለቲካ አስተሳሰብ ስለ እሚዘውረው ነው።

ንፅፅሩን ለመረዳት እንዲያቀል ያኽል ፤ ስለ ኤሌክትሪክ ፍጆታ ፣ ስለ ምንዛሪ ለውጥ እና ስለ ኤሌክትሪክ ዋጋ ትመና ፤ አጭር ማብራሪያ እናስቀምጥ፦

ከኤ አይ በተገኘ መረጃ መሰረት ፤ በወር 50 ኪሎዋት አወር ኤሌክትሪሲቲ የእሚጠቀም አንድ ቤት ፦ አንድ አራት አምፖሎች ፣ መለስተኛ ፍሪጅ ፣ ቴሌቭዥን እና እንደ ስልክ እና ላፕቶፕ ያሉ መጠቀምያ ዕቃዎችን ቻርጅ ማድረግ ይችላል።

እንደ እዚኹም ፤ የብር የምንዛሪ አቅም በመዳከሙም ፤ በ2025 እና ከእዚያ በኋላ ፤ የኬንያው ሽልንግ ከኢትዮጵያው ብር አንፃር ጠንካራ ገንዘብ በመሆኑ ፤ የኬንያ ክፍያ በሽልንግ ቢጠቀሰም ፤ ዋጋው ከምንዛሪ አንፃር ፤ ከኢትዮጵያ ጋር ተወዳዳሪ ካልሆነም የበለጠ ነው።

እንደ እዚኹም ኹለቱም ፦ ማለትም ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና የኬንያው KPLC ወይንም ኤሌክትሪክ ከአመንጪዎቹ ገዝተው ለደንበኞቻቸው የእሚቸረችሩት ፤ አንዱን ኪሎዋት በእሚሸጡበት ዋጋ ብቻ ሳይሆን ፤ በእሚያስከፍሏቸውተጨማሪ ክፍያም ይለያያሉ። በእዚኽም መሰረት ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ ፍላት ሬት (Flat Rate) ወይንም ወጥነት ያለው መጠን በመጠቀም ፤ ለምሳሌ ፦ በእየ መደቡ ፤ 10 ፣ 15 ወይንም መሰል ክፍያ ብቻ ሲያስከፍል ፤ የኬንያው ግን ፦

- የነዳጅ ዋጋ ፥
- የዶላር ምንዛሪ ለውጥ ዋጋ ፥
- የዋጋ ግሽበት ዋጋ ፥
- ቫት
- የገጠር ኤሌክትሪፍኬሽን ቀረጥ ፥

ወዘተ ፤ በእሚል ፤ አንድ ቋሚ ሬት ሳይሆን ፤ ተለዋጭነት ያለው እና በጠቅላላ 8 ዓይነት ክፍያዎችን በማካተት ፤ ተጨማሪ ክፍያው ፤ መደበኛ ኪሎ ዋት አወሩን ከእሚሽጥበት በጣም ከፍ ያለ ነው።

እነ እዚኽን ከግምት አስገብተን ፤ ኹለቱም ተቋማት ፦ ማለትም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና የኬንያው ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ በእየ ታሪፉ መደብ የእሚያስከፍሉትን ክፍያ እናነፃጽር ፦

| ኬንያ ከሐምሌ 2025 ጀምሮ | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |
| የታሪፍ መደብ | የKWh ዋጋ በሽልንግ | የአገልግሎት ክፍያ ጭማሪ ሲካተት የKWh ዋጋ በሽልንግ | የመደቡ ጣራ ወርኃዊ የሽያጭ ዋጋ በሽልንግ |
| 30Kwh በታች | 12.14 | 20.17 | 605.10 |
| 31 Kwh - 100 Kwh | 16.50 | 25.27 | 2, 527 |
| 100 Kwh በላይ | 18.57 | 28.46 | ከ 2, 527 ሽልንግ በላይ |

ምንጭ ፦ Understanding Your Bill: Cost of Electricity in Kenya - MEP Engineering

| | ኢትዮጵያ በ2018 ዓም (2025/2026 በፈረንጆቹ) | | |
|---|---|---|---|
| የታሪፍ መደብ | የKWh ዋጋ በብር | የአገልግሎት ክፍያ ጭማሪ ሲካተት የKWh ዋጋ በብር | ከፍተኛ መጠን ክፍያ በብር |
| 50Kwh በታች | 0.92 | 11.90 | 46 + 11.90 = 57.90 ብር |
| 51 Kwh - 100 Kwh | 2.21 | 49.60 | 221 + 49.60 = 270.60 ብር |
| 101 Kwh - 200 Kwh | 3.72 | 49.60 | 744 + 49.60 = 793.60 ብር |
| 201 Kwh - 300 Kwh | 5.68 | 49.60 | 1,704 + 49.60 = 1,753.60 ብር |
| 301 Kwh - 400 Kwh | 5.86 | 49.60 | 2,344 + 49.60 = 2,393.60 ብር |
| 401 Kwh - 500 Kwh | 5.94 | 49.60 | 2,970 + 49.60 = 3,019.60 ብር |
| ከ500 በላይ | 5.97 | 49.60 | ከ 3, 019.60 ብር በላይ |

ምንጭ ፦ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፖርታል

እንደገናም ፦ በኢትዮጵያ ፤ ምንም እንኳን ፋይዳው ይኽን ያኽል ባይሆንም ፤ ቅድመ ክፍያ የእሚከፍሉ ወይንም ዘመናዊ ቆጣሪ በመጠቀም ፤ ቆጣሪ አንባቢ ቤታቸው እንዲመጣ የእማያደርጉ ደንበኞች ፤ ዝቅተኛ የአገልግሎት ክፍያ ነው እሚከፍሉት።

በእዚኽም መሰረት ፦ ቋሚ 11.90 ብር የአገልግሎት ፤ ማለትም ፦ የቆጣሪ ማንበቢያ ፤ የእሚከፍሉት የድህረ ክፍያ የእሚከፍሉት ሲሆን ፤ ዘመናዊ ቆጣሪ ገጥመው ፤ ቅድመ ክፍያ የእሚያደርጉ ከሆነ ፤ ክፍያው 4.87 ሳንቲም በመሆን ሲቀንስ ፤ ከ50 ኪሎ ዋት አወር የእሚጠቀሙት ደግሞ ፤ ቋሚ የአገልግሎት ክፍያቸው ፤ ከ49.60 ወደ 15.02 ይቀንስላቸዋል።

ስለ እዚኽ ፡- በ2018 ከ50KWh በታች ወርኃዊ ፍጆታ ያላቸው ደንበኞች ፤ ቆጣሪ አንባቢ የእሚፈልግ አሮጌ ቆጣሪ እሚጠቀሙ ከሆነ ፤ የወርኃዊ ክፍያቸው ጣሪያ 57.90 ብር ከመሆን ይልቅ 50.87 ብር በመሆን ፤ በወር የሰባት ብር ቅናሽ ያገኛሉ።

እንደ አያቸኹት ፤ በእዚኽ ወቅት ፤ በ57.90 እና በ50.87 መካከል ጉሉኽ ልዩነት ባይኖም ፤ ልዩነቱ ከ10% በላይ መሆኑ እና ዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍልን ለመደጎም የእሚሰራ በመሆኑ ፤ ልዩነቱን የተለየ ትርጉም ይሰጠዋል ። ምክንያቱም ፡- በሐገር የዶላር እጥረት እና በተቋሙ ችግር እንዲኹም በተደጓሚው የሕብረተሰብ ክፍል የመግዛት አቅም ምክንያት ፡- 85% የእሚሆነው የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ አሮጌውን ቆጣሪ የእሚጠቀም ነው ተብሎ ስለ እሚገመት ፤ መንግስት ሊደጉመው ጠብ እርግፍ የእሚልለት ይኽ ሕብረተሰብ ክፍል ፤ ለተጨማሪ የ10 በመቶ ዋጋ ይዳረጋል።

በተለይ ደግሞ ድኃው በወር 50KWh ሙሉ ኤሌክትሪሲቲ ከመጠቀም ይልቅ ግማሽ ቢጠቀም ፤ የአገልግሎት ክፍያው ቋሚ 11.90 በመሆኑ ፤ ምንም እንኳን የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያው 23 ብር ብቻ ቢሆንም በጠቅላላ 34.90 ሳንቲም ይከፍልና ፤ ከክፍያዋ ሲሶው የአገልግሎት ክፍያ ይሆንበታል።

ለማነፃፀር ባደረኩት ሙከራ ፤ እንደ AI መረጃ ከሆነ ፤ በኬንያ ደግሞ አሮጌ ቆጣሪ የእሚጠቀመው የሕብረተሰብ ክፍል 15% በመሆኑ ፤ ከተጨማሪ የአገልግሎት ክፍያ ይድናል።

ይኽን ካልን ፤ የንፅፅሩን ሌላ መልክ ዕንመልከት ፡-

እኔ መረጃ ለማሰባሰብ ባደረኹት ጥረት ፤ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ ምን ያኽሉ የሕብረተሰብ ክፍል የትኛውን የኤሌክትሪክ መጠን ይጠቀማል የእሚል መረጃ ባይሰጥም ፤ የኬንያውን ታሪፍ እና የኤአይን እገዛ ተጠቅሜ ያደረግኹት ግምት ፤ ከግማሽ በላይ የእሚሆነው ተጠቃሚ የእሚገዛው የኤሌክትሪክ ፍጆታ ፤ እስከ 100 Kwh ያለውን እንደ ሆነ ነው መገመት የእሚቻለው።

በእዚኽም መሠረት ፤ ለምሳሌ ጂምናይ ያስቀመጠው ግምት ፡-

| **ወርኃዊ ፍጆታ በኪሎዋት አወር (Kwh)** | **ግምታዊ ተጠቃሚ የሕብረተሰብ ክፍል** | **በእዚኽ ፍጆታ ሊገኝ የእሚችል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ዓይነት** |
|---|---|---|
| 0 – 50 kWh *(የነፍስ አድን ተጠቃሚዎች)* | ~25% – 29% | የገጠር እና የመለስተኛ ከተማ ቤቶች ወይንም አንድ ክፍል የቀበሌ ቤቶች ሆነው ፡- መብራት ፣ ስልክ ቻርጅ እና ቴሌቭዥን እንዲኹም አነስተኛ ፍሪጅም ሊኖራቸው የእሚችል። |
| 51 – 100 kWh | ~29% – 35% | ይኽን ያኽል የእሚጠቀሙት ፤ በኢትዮጵያ ደረጃ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው እና ከመብራት ፥ ቴሌቭዥን እና ስልክ ቻርጅ ባሻገር ፤ እንደ ካውያ ያሉ በኤሌክትሪክ የእሚሰሩ የተወሰነ ቁሳቁሶች እና ውስን በኤሌክትሪክ የማብሰል ሥራ የእሚሠሩ ናቸው። |

ይኽንም የጂምናይ ግምት ፤ ከኬንያው የታሪፍ መደብ ጋር ስናስተያየው ፤ የኬንያዊ ታሪፍ ፤ ዝቅተኛ እና እገዛ እሚደረግላቸው ተጠቃሚዎች ፤ በቤተሰብ ደረጃ ዝቅተኛው ወርኃዊ ፍጆታ 30 KWh ነው ማለቱ እና ከፍ ካለም 100 KWh ድረስ ነው ማለቱ ፤ አንድ አፍሪካዊ መለስተኛ ቤተሰብ እስከ 100 ኪሎዋትአወር ባለው ፍጆታ ፤ መሠረታዊ ፍላጎቱን እንደ እሚያሞላ ያሳያል ከእሚል ጋር ስናገናዝበው ፤ ከ55% እስከ 65% የእሚሆነው ኢትዮጵያዊ የኤሌክትሪክ ፍጆታው በእዚኽ መደብ ውስጥ ነው ሊሆን የእሚችለው እንድንል ያደርገናል።

ስለ እዚኽ ፡- ከሞላ ጎደል ፤ ከግማሽ በላይ የእሚሆነው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ደንበኛ ፤ በወር እስከ 100 ኪዋት አወር (KWh) ነው የእሚጠቀመው በእሚል እሳቤ ካየነው ፡-

- እስከ 50 KWh የእሚጠቀመው ከእነ አገልግሎት ክፍያው በአማካይ በ KWh 1.158 ብር ሲከፍል
- እስክ 100 KWh የእሚጠቀመው ከእነ አገልግሎት ከፍያው በአማካይ በ KWh 2.706 ብር ይከፍላሉ ተብሎ ስለ እሚገመት

የኹለቱን አማካኝ ፤ ከግማሽ በላይ የሆነው ኢትዮጵያዊ ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ፤ በ KWh የእሚከፍለው ነው ብለን ብንወስድ ፤ ከግማሽ በላይ የእሚሆነው ኢትዮጵያዊ ለኤሌክትሪክ በአማካይ በ KWh 1.932 ብር ወይንም ወደ 2 ብር ገደማ ይከፍላል ማለት ነው።

በአንፃሩ ፤ የዝቅተኛውን መደብ ታሪፍ ብንወስድ እንኳን ፤ ኬንያዊያን በ KWh 20.17 ሲከፍሉ ፤ ልክ እንደ ኢትዮጵያ እስከ 100 KWh የእሚጠቀሙትን ከወሰድን በአማካይ በ KWh 22.87 ሽልንግ ይከፍላሉ።

ኢትዮጵያዊያዊ በኪሎዋትአወር 1.565 ብር ሲከፍል አንድ የኬንያ ዜጋ ደግሞ ለተመሳሳይ ፍጆታ በአማካይ 14.32 ሽልንግ ይከፍላል።

ይኸም ማለት ፦ አብዛኛው እና በወር እስክ 100 KWh ፍጆታ ያለው ኬንያዊ ፤ ከኢትዮጵያዊው ከ10 ወይንም 9 እጥፍ በላይ ይከፍላል።

ይኽ እንዲኽ ሲሆን ፤ እንደ እራሱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት መረጃ (የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፖርታል) ፤ በፈረንጆቹ መስከረም 2024 የዋጋ ስሌት ፤ አንድ ኪሎዋት አወር ኤሌክትሪሲቲ አምሮቶ ለማቅረብ በዓመት 6.01 ብር ይፈጃል ።

ይኽም ማለት ፦ የኢትዮጵያ መንግስት ከግማሽ በላይ ለእሚሆነው ፤ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ተጠቃሚ ፤ መንግስት በኪሎዋት 4.445 ብር ወይንም ከ73% በላይ በእያንዳንዱ ኪሎዋት ይደጉማል።

ይኽም የአሁን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ጠቅላላ መኖሪያ ቤት 5 ሚልዮን ነው ብለን ብናስብ (እንደ እዚያ ደርሰናል ስለ እሚሉ) ፤ ከእዚኽ 5 ሚልዮን ደንበኛ ውስጥ እስከ ግማሽ የእሚሆነው ፤ ከ73% በላይ የኤሌክትሪክ ድጎማ ስለ እሚያገኝ ፤ ተቋሙ በእየ ወሩ እስከ 403, 325, 000 (አራት መቶ ሚልዮን ሶስት መቶ ኃያ አምስት ሺ ) የእሚጠጋ ብር በእየወሩ ይደጉማል።

በእዚኽ ላይ ፤ በሐገሪቱ ውስጥ ካለው ፤ የገንዘብ የመግዛት አቅም መዳከም አንፃር ስናየው ፤ በድጎማው ምክንያት ወርኃዊ የኤሌክትሪክ ፍጆታው እንኳን 100 ኪሎ ዋት አወር የሆነውን ሰው ክፍያ መጠን ብናየው 221 የኢትዮጵያ ብሮ ሆኖ የእምናገኝ መሆናችን እና አንድ ደረቅ እንጀራ 30 ብር የእሚሸጥ መሆኑን ስናገናዝብ ፤ ለእዚያውም የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ የሆነ ፤ ስለ እዚኽም የተሻለው የእሚባለው የሐገሪቱ ሕዝብ ፤ 300 ብር የእማይበልጥ ብር ፦ ፍሪጅ ፣ ስልክ ፣ ቴሌቪዥንና መብራት መሰል አገልግሎት ለእሚሰጠው ኤሌክትሪክ በወር 300 ብር በላይ ወይንም በማምረቻ እና በማከፋፈያ ዋጋ እንኳን ማለትም እስከ 700 ብር ከፍሎ ቢገዛ ፤ በከፍተኛ ኹኔታ ኢኮኖሚውን ያዛባዋል እና መንግስት እስከ 73% ይደጉመው ብሎ ማለት ፤ የተበላሸ የሐገራችን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ፤ የሕዝቡን ኢኮኖሚ እንዴት አድርጎ እንደ ጎዳ እንጂ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ ኹኔታ እንዴት የደከመ የመግዛት አቅም እንደ አለው አያሳይም።

ምክንያቱም ፦ በዘመናዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ የኢትዮጵያዊውን የመግዛት አቅም በእዚኽ መልኩ እንዲዳከም ፤ ከኢትዮጵያ መንግስታት የተበላሸ ሕገመንግስት እና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ውጭ ፤ ይኽ እና ያ የእሚባል ፤ “ተፈጥሯዊ” ምክንያት ማቅረብ ስለ እማይቻል።

በተፈጥሮ ኃብት ፣ በፖለቲካዊ ነጻነት ፣ በሕዝብ የሥራ ባሕል እና ስነ ምግባር ፣ ወዘተ ብናይ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኬንያ ሕዝብ ቢሻል እንጂ በምንም አያንስም ፤ ታዲያ እንዴት የኬንያ ሕዝብ ከኢትዮጵያ የተሻለ አቅም የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደኃ ስለ ሆነ ነው ሊባል ይችላል ?

ይልቁንም በመቀጠል እንደ እምናየው ፤ ዋነኛው ችግሩ ፤ መንግስታችን በእሚከተለው ባሕሪያዊ የተበላሸ የማሕበረ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ምክንያት ፡- ከፍተኛ አስተዳደራዊ እና የፖሊሲ ጉድለት ያለባቸውን ፤ እንደ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ያሉ ፤ የልማት ተቋማት ተብዬዎች በመኮልኮል ፤ ሕዝብን በመደጎም ፍትኃዊ ዕድገት አመጣለኹ በእሚል የሞኝ ተረት ፤ የሕዝብ እና የሐገር ኃብት በማባከን እና የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት በመፍጠር ፤ የሕዝብን የመግዛት እና ተቋማት የመምራት አቅም በማዳከሙ ምክንያት እንደ ሆነ ግልፅ ይሆናል።

በእዚያ ላይ ፤ እስከ 2025 ከኢንደስትሪ በስተቀር ፤ በወር እንኳን እስከ 500 ኪሎዋት አወር (Kwh) ማለትም ፡- በርካታ ክፍል ባላቸው ቤቶች ፤ በእየቀኑ በኤሌክትሪክ ከማብሰል አልፈው ፤ በርካታ የገላ መታጠቢያ ውኃ ማሞቂያ እና ሌሎች ብዙ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች የእሚጠቀሙ እንደ እዚኹም የንገድ ቤቶች እንኳን ፤ የድጉማ ተጠቃሚ ነበሩ።

ምክንያቱም ፡- እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር እስከ 2017 ዓም በወር ከ400 እስከ 500 ኪሎዋት አወር የእሚጠቀሙ መኖሪያ ቤቶች እና ማንኛውም የንግድ ቤት ፤ ከወቅቱ አንድ ኪሎዋት አወር ኤሌክትሪስቲ አምርቶ ከማከፋፋያ ዋጋ ፤ ማለትም ከ6.01 በታች 5.97 እና 5.98 ነበር የእሚከፍሉት።

ይኽም የእሚበቃ አይመስል ፤ አባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል የእሚለው ተረት ሰርቶበት ፤ ገለፈት የሆነው የሐገራችን መንግስት ፤ ከ60 ዓመት የኢንደስትሪያላይዜሽን ጥረት በኋላ ፤ በአፍሪካ ደረጃ እንኳን ይኽ ነው የእሚባል የኢንደስትሪ ልማት ማምጣት ባይችልም ፤ ይኽን የሐገር እና የሕዝብ ንብረት እያባከነ የእሚያመነጨውን ኃይል ፤ እና በእዚኽም ምክንያት ፡- በእየ ዓመቱ በቢልዮን ብሮች እየከሰረ ፤ ለአነሥተኛ እና መካከለኛ ኢንደስትሪዎች እንኳን ፤ የማምረቻ እና የማከፋፈያ ዋጋው 6.01 ብር ቢሆንም እንኳን ኤሌክትሪሲ በKWh በ3.62 እና በ2.94 ብር በመሸጥ ፤ ከግማሽ በላይ ይደጉማቸዋል።

በእዚያ ላይ ለመንገድ መብራት በ KWh የእሚሸጥበት ዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል በእሚደጎምበት 0.92 ሳንቲም በ KWh ነው።

እስኪ አንድ ፈጣሪ የሰጠው አዕምሮው አንገቱ ላይ ሆኖ ይዞት የእሚዞር አንድ ሰው ፤ በሐገራችን በልማታዊነት ስም ፤ ይኽን የእብደት እና የአሰራር ብልሹነት ጥግ ፤ መንግሥት ለሕዝብ ብሎ የእሚያደርገው ነው ብሎ ያሳምነን ?

በመሆኑም ፤ ቢያንስ እስከ 2017 መንግስት ዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍሉን ብቻ ሳይሆን ፤ የሐገሪቱን ከፍተኛ ገቢ ነዋሪዎችን ፣ ኢንደስትሪዎችን እና የመንገድ መብራትን እንኳን ነበር ሲደጉም የነበረው።

አሁን መንግስት ለእዚኽ ቆሸቆሸ የኮረደር ልማት እና ከተማን በብልጭልጭ አምፖል ለማብረቅረቅ ቅዠት ፤ በዓመት እስከ 122 ቢልዮን ብር እየከሰረ መደጎም ነበረበት ? በየትኛው የልማታዊነት እሳቤ ወይንስ አሠራር ነው ፤ ይኽ ለሕዝብ ተብሎ የእሚደረግ የእሚሆነው።

ማንም ጤነኛ አዕምሮ ያለው ሰው ፤ እንደ ኢትዮጵያ ያለች ድኃ ሐገር መንግሥት እና በአፍሪካ ደረጃ እንኳን በጣም ዝቅተኛ የእሚባለውን ግብር የእሚሰበስብ መንግሥት ፤ ድኃውን ብቻ ሳይሆን የሐገሪቱን

የከፍተኛ ገቢ ባለቤቶች ፣ ነጋዴዎች ፣ ኢንደስትሪዎች እና የመንገድ መብራት (ለእዚያውም የመሸታ ቤት የመሰሉ የኮሪደር ልማት መብራቶች ጨምሮ) ኤሌክትሪክ ካልደነምኳቸው ፤ ኑሮ ይወደዳል ብሎ የእሚል መሆኑ እና ይኸም በሐገር ደረጃ ፡-

- የብድር ዋጋ መወደድ ፣
- የዶላር እጥረት ፣
- የዋጋ ግሽበት ፣
- የግል መስክ መዳከም ፣ ወዘተ

የእሚያስከተል መሆኑን ሲረዳ ፤ በኢትዮጵያ ያለው ችግር ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንዳች ምክንያት ከኬንያ ሕዝብ አስር እጥፍ ያነሰ የማምረት አቅም ስለ አለው ስለ እዚኸም ከኬንያ ሕዝብ 10 እጥፍ ያነሰ የመግዛት አቅም ስላለው ሳይሆን ፤ መንግሥታት ነን ብለው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተጣበቁት የባለፈው 60 ዓመታት በላይ የኢትዮጵያ መንግሥታት ፤ በእሚከተሉት የመኃይም ሕገመንግሥት እና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምክንያት ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፤ በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው ስለ አደቀቁት መሆኑ ግልፅ ይሆናል።

## 4.2.1 በ2025 ከነበረው ሽያጭ 55% የተሸጠው ለውጭ ሐገር ነው

ከኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተለየ :-

- ኢትዮቴሌኮም ፥
- ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና
- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

ላይ አንዱ የእምናየው ጉድለት ቢኖር ፤ ለረጅም ግዜ በመንግሥት ተቋምነት በመቆየታቸው ፤ በጥሩ ኹኔታ የተቀናበረ እና ደረጃውን የጠበቀ ዓመታዊ ሪፖርት አለማውጣት ነው።

በኦዲተሮች የተመረመረ ዓመታዊ የሒሳብ ሪፖርት ያቀርባሉ ፤ ሆኖም ፡- ዓለም ዓቀፍ ልማዱን የተከተለ ዓመታዊ የትልቅ የንግድ ኮርፖሬሽን ዓመታዊ ሪፖርት ግን የላቸውም ፤ ካላቸውም እንደ ንግድ ባንክ እና እንደ አየር መንገድ ለሕዝብ አላቀረቡትም።

በእርግጥ የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፤ የእሚያወጡት ዓመታዊ ሪፖርት ፤ ከሌሎች ተመሳሳይ ሐገራት ፤ የመንግሥት ተቋማት አንጻር እንኳን ፤ ተወዳዳሪ ነው ማለት ባይቻልም ፤ ልማዱ እና አሠራሩ በመኖሩ ፤ በሒሳብ መዝገብ ብቻ የእማይገኙ ፤ የተቋሞቹን ቁመና የእሚያሳዩ ብዙ መረጃዎች ፤ በእየ ዓመቱ ከእሚያወጡት ሪፖርት ማየት ይቻላል።

ሆኖም ፦ የሩብ ዓመት እና የዓመት ትናንሽ መጽሔቶች ስለ እሚያሳትሙ ያንን ኦዲት ተደርጎ ከእሚቀርበው ዓመታዊ የኢዶት ሪፖርት ጋር አዛምደን ስለ ሽያጩ ስብጥሩ መረጃ ማግኘት እንችላለን።

ቁጥሮቹን ከ2025 ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) ኦዲት የተደረገ ዓመታዊ ሪፖርት ላይ አምጥተን እና ሌላውን መረጃ ደግሞ እንደ ብሮሽር አድርገው ከእሚያሳትማቸው መጽሔትች አምጥተን ዕንመልከት ፦

| **ገዢ** | **2025 ሽያጭ በብር** | **ከጠቅላላ ሽያጩ በፐርሰንት** |
|---|---|---|
| የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት | 27,941,909,000.00 | 38.44% |
| ጅቡቲ | 3,669,921,000.00 | 5% |
| ሱዳን | 59,121,000.00 | 0.08% |
| ኬንያ | 10,454,551,000.00 | 14.4% |
| ዴታ ሴንተሮች (ቢትኮይን) | 27,397,560,000.00 | 37.69% |
| ኢንደስትሪዎች | 3,155,818,000.00 | 4.34% |
| ድምር | 72,678,880,000.00 | 100% |

በሰንጠረዡ ላይ በተቀመጠው መረጃ መሠረት ፦ በፈረንጆቹ 2025 በኢትዮጵያ ውስጥ ፦

- ለመኖሪያ ቤቶች እና ለንግድ ተቋማት እንደዚኹም
- ለኢንደስትሪዎች

በተደረገው ሽያጭ (ከእላይ በአረንጓዴ በተቀለሙት መስመሮች ተቀምጦ የእሚታየው ነው) የተገኘው ጠቅላላ ገቢ ፦ 27,941,909,000.00 +3,155,818,000.00 = 31,097,727,000 (ሰላሳ አንድ ቢሊዮን ፤ ዘጠና ሰባት ሚልየን ፤ ሰባት መቶ ኃያ ሰባት ሺ) ወይንም ክጠቅላላው ሽያጭ 42.78% ነው።

የቀረው 57.22% የኤሌክትሪሲቲ ሽያጭ ገቢ ፤ ርካሽ ኤሌክትሪሲቲ በእሚል ማስታወቂያ የተሸጠው ፤ እራሳቸው በከፍተኛ ብድር ተሠርተው ምንም ኢንደስትሪያሊስት መሳብ ባቃታቸው ኢንደስትሪ ፖርኮች ፤ አሜሪካንን ጨምሮ ከሌሎች ሐገራት ፤ ኤሌክትሪክ መጣጭ ተብለው የተባረሩ የቢትኮይንም ማይነሮችን (Bitcoin Miners) በማስገባት ፤ ለእነርሱ ማለትም ለቢትኮይን ዴታማይኒንግ እና ለሰስቱ ጎረቤቶቻችን ፦ ኬንያ ፤ ሱዳን እና ጅቡቲ ነው።

ይኸ ከላይ የተቀመጠው ፤ በእየመደቡ ከተሸጠው የኃይል ሽያጩ የተገኘ ገቢ በመሆኑ እና የተለያዩት መደቦች ደግሞ የእየራሳቸው የተለያየ ታሪፍ ያላቸው በመሆኑ ፤ ለምሳሌ ፡- ለመላው ኢትዮጵያዊ ፡- መኖሪያ ቤቶችን ፣ ንግድ ቤቶችን እና ኢንደስትሪዎችን ጨምሮ የተሸጠው እና በ2017 ዓም ለዴታ ሴንተሮች ብቻ የተሸጠው በገቢ ደረጃ እኩልነት ቢኖራቸውም ፤ በተሸጠ የኃይል መጠን ግን ልዩነት አላቸው።

ምክንያቱም ፡- ለኢትዮጵያዊ የእሚሸጥበት ዋጋ እና ከውጭ ሐገር መጥተው ኤሌክትሪክ ለእሚመጡ ዴታ ሴንተሮች ኤሌክትሪክ ታሪፍ እኩል አይደለም።

በመሆኑም ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል "Facts In Brief" በእሚል በእሚያሳትማት ትንሽ የእንግሊዘኛ መጽሔት ላይ በ2017 ዓም ወይንም በፈረንጆቹ 2025 ባሳተሙ እትሙ ፤ ከዋጋ ባሻገር ፤ ከተመነጨው ጠቅላላ ኃይል ምን ያኽሉ ለማን እንደ ተሸጠ በእዚኽ መልኩ አስቀምጦታል ፡-

> *"በኢትዮጵያ አቆጣጠር 2017 ዓም በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ፤ ዓመታዊ በተቋሙ ለፍጆታ የዋለው የኃይል መጠን 26,193.87 GWh ነው። ከእዚኽ ውስጥ ፡- 93.08% የእሚሆነው ለሐገር ውስጥ ፍጆታ ሲሆን ፤ ቀሪው 6.92% ኤክስፖርት የተደረገ ነበር። ከእዚኽ ለሐገር ውስጥ ፍጆታ ከዋለው ውስጥ ፡- 60.57% የገዛው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሲሆን ፤ በከፍተኛ የኃይል ተሸካሚ ማለትም 132 kV ኃይል ማስተላለፊያ ኃይል የእሚደርሳቸው ደንበኞች 5.66% እና የዴታ ማይኒንግ 26.67% ሲሆኑ ፤ የኢትዮጵያ ምድር ባቡር 0.17% የጠቅላላ ፍጆታው ተጠቃሚ ነው። ኤክስፖርት የተደረገላቸው የውጭ ሐገራት ፡- ሱዳን ፣ ኬንያ እና ጅቡቲ ፤ በቅደም ተከተል ፤ ከጠቅላላ የተቋሙ ፍጆታ ፡- 0.07% ፥ 5.06% እና 1.8% ደርሷቸዋል።"*
>
> *"At the end of the 2017 Ethiopian fiscal year, total energy consumption is 26,193.87 GWh. From those energy around 93.08 percent local and remaining for export customers. EEU is EEP's primary customer that represented 60.57 percent and High voltage customers connected at 132 kV 5.66 percent and Data mining 26.67 percent and Railways at 0.17 percent of total energy consumption. The export customer has Sudan, Kenya and Djibouti with energy consumption of 0.07, 5.06 and 1.8 percent respectively."*

ለንባብ እና ለመረዳት እንዲቀል ፤ ይኽን በጽሑፍ የተቀመጠ መረጃ ፤ በሰንጠረዥ እናስቀምጠው ፡-

| ሸማች | ከጠቅላላው ፍጆታ ድርሻ |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት | 60.57 % |
| ከፍተኛ ኢንደስትሪዎች | 5.66 % |
| ዴታ ማይነሮች | 26.67 % |
| የኢትዮጵያ ምድር ባቡር | 0.17 % |
| ኤክስፖርት ሸማቾች ፡-<br>➢ ሱዳን ፣<br>➢ ኬንያ<br>➢ ጅቡቲ | ኤክስፖርት ሸማቾች ፡-<br>➢ 0.07%<br>➢ 5.06%<br>➢ 1.8% |

እነ እዚኽን ሸማቾች ስንዘረዝራቸው ፡-

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፡- ለኢትዮጵያ መኖሪያ ቤቶች ፣ ንግድ ቤቶች እንደ እዚኹም ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንደስትሪዎች ኤሌክትሪሲቲ የእሚቸረችረው ማለት ነው።
- ከፍተኛ ኢንደስትሪ የእሚባሉት ፡- የመንግሥት የስኳር ፣ የስሚንቶ ፣ የብረት ማቅለጫዎች ፣ ወዘተ ፋብሪካዎች ናቸው እሚሆኑት ።
- ዴታ ማይነሮች ፡- ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆንም የእሚሰሩት ፤ ርካሽ ኤሌክትሪስቲ ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የውጭ ኩባንያዎች ናቸው።
- የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ፡- የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር እና አዲሱ በኤሌክትሪክ የእሚሰራ ከጅቡቲ አዲስ አበባ የተዘረጋው የኤሌክትሪክ ባቡር ነው።
- ኤክስፖርት ፡- እንደ ተዘረዘሩት ፡- ለሱዳን ፣ ኬንያ እና ደቡብ ሱዳን ፤ አንድ አንዴም ክፍያ የእሚያዘገዩ ግን ኤክስፖርት የእሚደረግላቸው ናቸው።

ስለ እዚኽ ፡- ምንም እንኳን ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2017 ዓም ከተፈጀው የኤሌክትሪክ ኃይል ውስጥ 93.08 % ለሐገር ውስጥ ገበያ የቀረበ ነው ቢልም ፤ ከእዚያ ውስጥ ለዴታ ማይኒንግ የቀረበው 26.67% ኤሌክትሪሲቲ ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በመሸጡ እንጂ ተጠቃሚዎቹ ኢትዮጵያዊያን ባለመሆናቸው እና ኢትዮጵያ የመጡትም ፤ በዓለም ላይ እንደ ቻይና እና አሜርካ ባሉ ሐገራት ሳይቀር ፤ ለዴታ ማይነሮች ዴታ መሸጥ ለሕዝብ እና ለኢንደስትሪ የእሚቀርበውን ኃይል ስለ እሚሻማ ፤ ከፍተኛ ቁጥጥር እና እገዳ የእሚደረግባቸው በመሆኑ ፤ ሪፖርቱ የተድበሰበሰ ስዕል ነው እሚሰጠው።

የእዚኽም እንደምታ የእሚኀላው ፡-

አንደኛ ፡- ምንም እንኳን ፤ በእዚያ ዓመት የተፈጀው ጠቅላላ ኤሌክትሪሲቲ 26,193.87 GWh ነው ቢባልም ፤ በእዚያ ዓመት የተመረተው ጠቅላላ ኤሌክትሪሲት 29,467.90 GWh በመሆኑ ፤ ልዩነቱ ማለትም

ከተመረተው ጠቅላላ ኃይል 11.11% የእሚሆነው እና 3,274.03 የእሚሆነው ፤ በአሮጌ ማስተላለፊያ እና በሌሎች ምክንያት ፤ ተመርቶ ግን ያልተሸጠ እና የባከነ ኃይል ነው።

በአንጻሩ ፤ በእዚያው ዓመት ፤ የኬንያው ኬንጄን ፤ ጠቅላላ የአመረተው ኃይል 8,701.13 GWh ሲሆን ፤ ከእዚኽ ምርቱ ተርፎ ለሽያጭ የቀረበው ደግሞ 8,467.97 GWh ነው። ይኸም ማለት ፤ ከተመረተው ኃይል የባከነው ወደ 2.7% ገደማ ብቻ ነው ፤ ከእላይ እንደ ተጠቀሰው የኢትዮጵያ ብክነት 11% ሲሆን።

በሌላ መልኩ እንመልከተው ካልን ፤ በኢትዮጵያ ተመርቶ ለተጠቃሚ ሳይደርስ በተለያየ መንገድ የባከነው ኃይል ፤ ኬንጄን በዓመት ካመረተው 37.63% ሲሆን አምርቶ ከሸጠው ደግሞ 38.66% ነው። ስለ እዚኽ ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤ የኬንያው ኬንጄን ከእሚያመርተው ኃይል አንድ ሶስተኛውን በዓመት በብክነት ምክንያት ያጣዋል።

ኹለተኛ ፡- የባከነውን ጨምሮ በዓመት በጠቅላላ የተመረተው 29, 467.90 GWh ኤሌክትሪሲቲ ፤ በወቅቱ በሥራ ላይ ባሉ እና የኃይል ፍላጎት ካለ ኃይል ማመንጨት ከእሚችሉ ሐገራዊ አቅም ወይንም በእነርሱ ቋንቋ Installed Capacity ውስጥ 41% ብቻ መሆኑ ነው። ምክንያቱም ፡- በእዚያ ፋክትስ ኢን ብሪፍ በእሚለው መጽሔቱ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እንደ ህዳሴ ፣ ግቤ ፣ ተከዜ ፣ ወዘተ ያሉ ግድቦችን ጨምሮ ፤ በ2017 የነበረኝ ኃይል የማመንጨት አቅም ወይንም Installed Capacity 8,115.84 MW ይኸም በዓመቱ ሰዓታት ማለትም 8,760 ሲባዛ ፡-

$$8{,}115.84\ (MW) * 8{,}760\ (hr) = 71{,}094{,}758.40\ MWh\ \text{ወይንም}\ 71{,}095\ GW$$

ነው ብሎ ይነገረናል።

ሆኖም ፡- ይኽን ያኽል ዓመታዊ የማምረት አቅም ያለው የተተከለ የኤሌክትሪክ ማምረቻ ቢኖርም ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤ በዓመቱ በጥቅላላ ያመረተው 29,467.90 GWh ኤሌክትሪክ በመሆኑ እና ይኸም ፡- ለመኖሪያ ቤቶች ፣ ለንግድ ቤቶች ፣ ለትንንሽ እና ከፍተኛ ኢንደስትሪዎች ፣ የዴታ ሴንተሮች ብሎም ኤክስፖርት ያደረገውን የእሚጨምር በመሆኑ ፤ በዓመቱ ያመረተው ኤሌክትሪሲቲ ማምረት ከእሚችለው ወይንም ከገነባው አቅም 41% ብቻ ነው።

በአንጻሩ ፤ የኬንያው ኬንጄን ፤ ከኢትዮጵያው የኤሌክትሪክ ኃይል በተለየ ወይንም በተሻለ ፤ ከ97% በላይ የእሚሆነውን ኃይሉን ከግድብ ውኃ ብቻ ከማድረግ ይልቅ ፤ በተሻለ ኹኔታ ጂኦተርማል በመጠቀሙ ፤ ከኢትዮጵያው የኤሌክትሪክ ኃይል ከ14% በላይ የእሚሻል ሎድ ፋክተር (Load Factor) ኖሮት ነው የእምናገኘው ወይንም የማምረት አቅሙን የመጠቀም አቅም ኖሮት ነው የእምናየው።

ምክንያቱም ፡- በኬንጀን የ2025 ሪፖርት መሠረት በሥራ ላይ ያለው ጠቅላላ የማመንጨት አቅሙ ወይንም Installed Capacity 1,786 MW ሲሆን ፤ ይኽንም ተመሳሳይ ስሌት ተጠቅመን ፤ ጠቅላላ አመታዊ የማምረት አቅሙን ካሰላን ፡-

$$1{,}786\ (MW) * 8{,}760\ (hr) = 15{,}645{,}360\ MWh\ \text{ወይንም}\ 15{,}645\ GWh$$

ሆኖ እናገኘዋለን።

በመሆኑም ፡- ይኸንን በ2025 የባከነውን ጨምሮ ያመረትኩት ብሎ ያስቀመጠውን ፤ ማለትም ፡- 8,701.13 GWhን ለጠቅላላው የማምረት አቅሙ ማለትም ፡- 15,645 GWh ስናካፍል፡-

$$\frac{8{,}701.13\ GWh}{15{,}645\ GWh} * 100 = 55.61\%$$

ሆኖ እናገኘዋለን።

ይኸም ከኢትዮጵያው 41% ሎድ ፋክተር የተሻለ ከ14% በላይ የሆነ አፈጻጸም እናገኛለን።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤ እኔ ካንተ እሻላለኹ ብሎ ኤሌክትሪክ ኤክስፖርት የእሚያደርግለት ኬንጀን ፤ ኤክስፖርት ከእሚያደርግለት ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እጅግ የተሻለ አፈጻጸም ኖሮት እናገኘዋለን።

በመሆኑም ፡- ከጎረቤት ልምድ አንጻር ብናነጻጽር እንኳን ፤ በሐገራችን የእሚተገበረው የልማታዊነት አስተሳሰብ ፤ ቢያንስ የ14% የኢንቨስትመንት ብክነት አለው ማለት ነው።

በመሆኑም ፡- ለምሳሌ ፡- በ100 ቢልዮን ብር ከእሚያወጣ ኤሌክትሪ የማምረት አቅም ውስጥ ፤ ቢያንስ 14 ቢልዮን ብር ወይንም የአንዳንድ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጠቅላላ አመታዊ በጀት በላይ የሆነ ገንዘብ በእየ ዓመቱ በከንቱ ይባክናል።

ሦሥተኛ ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤ ከፍተኛ የማክሮኢኮኖሚ መዛባት አስከትሎ እና ከእላይ በተገለጸው መልኩ ከፍተኛ ሊባል የእሚችል ብክነት አስከትሎ ከእሚያመነጨው ኃይል 33.6% የእሚሆነውን ለዴታ ማይኒንግ እና ለኤክስፖርት ገበያ የእሚያቀርበው ፤ በእዚኽ መልኩ በከፍተኛ ኢንቨስትመንት ከገነባው ኃይል ማመንጫ ኤሌክትሪክ የእሚያገኘው ኢትዮጵያዊ 29% በሆነበት ኹኔታ ነው።

የዓለም ባንክ የእሚከታተለው እና ከሌሎች የልማት አጋሮች ጋር ሆኖ ብድር እና ሌሎች እገዛዎች በማቅረብ የእሚያግዝበት እና ሐገራት የኃይል አቅርቦታቸውን ለማሻሻል ያላቸውን ዕቅድ የእሚያስቀምጡበት ፤ National Energy Compact For the Federal Democratic Republic of Ethiopia የእሚለው ሰነድ ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ አለው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ደረጃ ይኽን ይላል ፦

*"ኢትዮጵያ ፦ በታዳሽ የኃይል ማመንጫ ግንባታ እና የኤሌክትሪክ አገልግሎትን በማስፋፋት ረገድ ፤ ጉልህ የሆነ ዕድገት ዓሳይታለች። በ2025 ከዓለም ባንክ ጋር በተደረገ ትብብር ፤ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ተደራሽነት ደረጃ የማወቅ ዳሰሳዊ ጥናት ፤ በጥር 2025 65% የእሚሆኑት ኢትዮጵያዊያን አንዳች ዓይነት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያገኛሉ። ከእዚኽም ውስጥ 29.3% የእሚሆኑት ከዋናው ሐገራዊ ግሪድ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ ፤ የቀሩት 35.7%[2] የእሚሆኑት ደግሞ ከብሔራዊ ግሪድ ውጭ በሆኑ ፤ ከጸሐይ ኃይል ማመንጫ ኤሌክትሪሲቲ የእሚያገኙ ናቸው። ሆኖም 44% የሆኑት ብቻ ናቸው መሠረታዊ የእሚባለውን እና እርከን አንድ እና ከእዚያ በላይ ያለውን የኤሌክትሪክ አገልግሎት የእሚያገኙት።"*

*"Ethiopia has made notable progress in expanding electricity access and enhancing renewable energy generation. According to the Ethiopian Energy Access Survey 2025, conducted in collaboration with the World Bank, as of January 2025, 65% of households across the country have access to at least one source of electricity. This includes 29.3% connected to the national grid and 35.7% relying on off-grid solar solutions. However, only 44% of the population benefit from a basic level of electricity service (Tier 1 and above). "*

ይኽን ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በመተባበር የተደረገ የዓለም ባንክ ሪፖርት የእሚለውን ትንሽ እናብራራው።

ከእላይ ሲታይ ወደ 65% የእሚሆነው ኢትዮጵያዊ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ነው የእሚለው። ነገር ግን ስንዘረዝረው ፦

1. 65% ከእሚሆኑት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚዎቹ 29% የእሚሆኑት ብቻ ናቸው ፤ በከፍተኛ ኢንቨስትመንት ክተገነቡት እና ኤክስፖርት ከእሚደረጉት እንዲኹም ለዴታ ሴንተር ከእሚሸጡት ውስጥ ፤ ማለትም ከብሔራዊ ግሪድ ውስጥ ኤሌክትሪክ የእሚያገኙት።

[2] ይኽ ቁጥር ፤ ምንም እንኳን በዓለም ባንክ ስም ሪፖርት ቢደረግም ፤ ቁጥሩን አዘጋጅቶ የእሚሰጠው የኢትዮጵያ መንግሥት በመሆኑ ፤ ነገሩ ቢጣራ የእሚል ጥያቄ ፈጥሮብኛል። ምክንቱም ፦ በኢትዮጵያ ውስጥ ፤ ቢያንስ ከ5 ካልሆነ ከ3 ሚሊዮን በላይ የሆኑ መኖሪያ ቤቶች ኤሌክትሪሲቲ ከሶላር ፓናል እያገኙ ነው የእሚለው ነገር ፤ በኢትዮጵያ ከእሚሰማው ነገር ጋር አብሮ እሚኼድ አይመስልም።

2. ያም ብቻ ሳይሆን ፤ በአግባቡ ባይብራራም ፤ እርከን አንድ እና ከእዚያ በላይ ያሉ ተጠቃሚዎች 44% ብቻ ናቸው ስለ እሚል እና እርከን አንድ ማለት በጣም ዝቅተኛው አጠቃቀም በመሆኑ ፤ ምን አልባት ኤሌክትሪክ ያገኛሉ ከተባሉት 65% ኢትዮጵያዊያን ከ21% በላይ የእሚሆኑት ምን አልባት ፤ መብራት ያለበት አከባቢ እየኖሩ ፤ ስልካቸውን ብር ከፍለው ቻርጅ የእሚያስደርጉ ዓይነት የመብራት ተጠቃሚ እንጂ በቤታቸው ኤሌክትሪሲቲ ያላቸው ዓይነት ተጠቃሚ አይመስሉም።

እንግዲኽ እነ እዚኽን ዕውነታዎች ከግምት አስገብተን ፤ የመንግሥት ኪስ እና የሕዝብ ኢኮኖሚ እያራገፈ ትላልቅ ኃይል ማመንጫዎች እየገነባ ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትኃዊ ኃይል ለማቅረብ እሰራለኹ በእሚል የተቋቋመው የልማት ተቋም ፤ በእዚኽ መልኩ በከፍተኛ ኃይል ከገነባው ኃይል ላይ የእሚያገለግለው ጠቅላላ ኢትዮጵያዊ 29% በሆነበት ኹኔታ ነው ፤ ከእሚያመርተው ጠቅላላ ኃይል 32.33% በመቶውን ለውጭ ሐገር ደንበኞች በኤክስፖርት እና ለዴታ ማይነሮች የእሚሸጠው።

ምን ዓይነት የልማት ተቋም ነው ፡-

- ከእሚያመርተው ኃይል 11% እያባከነ ፥
- ከ14% በላይ ጠቅላላ የማምረት አቅሙ ገዢ አጥቶ ወይንም የተበላሸ ኢንቨስትመንት ሆኖ ፥
- የእሚያገለግለው የሕብረተሰብ ክፍል 29% ብቻ ሆኖ ፥

ከእሚያመርተው ኃይል 32.33% በመቶውን ፤ እንደ ደላው ሰው ፤ ገሚሱን ለኢክስፖርት ፤ ገሚሱን ደግሞ ለዴታ ማይነሮች የእሚሸጠው ?

በእርግጥ ይኽ በአንድ በኩል ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከእሚያመነጨው ኃይል 67.67% የእሚሆነውን ኃይል ለሐገር ውስጥ በርካሽ እየሸጠ ፤ የቀረውን ለሌላ አገልግሎት በውድ በመሸጥ ፤ የሐገሩን ገበያ እየደጎመ ነው ሊያስብለው ፤ ይቻላል።

ያን በልበ ሙሉነት ለማለት ግን በጣም አዳጋች ነው ምክንያቱም ፡-

1. ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውጭ ላለው ገበያ በማቅረብ ካገኘው ትልቁ ገቢው የመጣው ፤ ንፋስ አመጣሽ ከሆነው ለዴታ ሴንተር ከተደረገ ሽያጭ ነው። ምክንያቱም ፡- ኢትዮጵያ እነ እዚኽን ትላልቅ የኃይል ማመንጫዎች በብዙ ዋጋ ስትገነባ ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ አደርጋለኹ ፤ ለኢንደስትሪያላይዜሽንም ርካሽ ግባት አመቻቻለኹ በእሚል እንጂ ቢትኮይን ማይኒንግ ጥሩ ገበያ ይሆናል በእሚል ስሌት አይደለም ።ግድቦቹ በእሚገነቡበት ወቅት ፤ ኢሕአዴግ ቢትኮይን መኖሩንም አያውቅም አይደለም የዕቅዱ አካል ሊያደርገው። ስለ እዚኽ ይኽ የዕቅድ ወይንም የስትራቴጂ ውጤት ሳይሆን ፤ የተዛባ ስትራቴጂ የፈጠረውን ትርፍ ኃይል ፤ እግር የጣለው እድለኛ ከማግኘቱ የመጣ ነው።
2. እንደ እዚያም ሆኖ ፤ ማለትም 32.33% በሆነ ሽያጭ የ55% የእሚሆነውን ገቢ ከውጭ ገበያም አግኝቶ በሐገሪቱ በነበረው የውጭ ምንዛሪ ለውጥ ምክንያት እና ታሪካዊ በሆነው

የተቋሙ የኪሳራ ልምድ ምክንያት ፤ በ2025 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሪከርድ የሰበረ 122 ቢልዮን ብር ከስሯል። ንፋስ አመጣሽ በጣም ከፍተኛ ገቢ እንኳን ፤ ተቋሙን ከኪሳራ አለመታደጉ ፤ ተቋሙ መሠረታዊ የንግድ አስተዳደር ጥበብ ጉድለት እንደ አለው ዓይነተኛ ማሳያ ነው።

3. በእዚያ ላይ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤ ይኸን ኃይል የእሚያመነጨው ፦
    a. ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ርካሽ ብድር በመውሰድ እና የብድርን ዋጋ በሐገር ውስጥ በማናር እንዲኹም ለግሉ መስክ የብድር አቅርቦት እጥረት በመፍጠር ፥
    b. ለረጅም ግዜ የጡረታ ፈንድን ገንዘብ ያለወለድ ፤ በኋላ ላይ ደግሞ በርካሽ ወለድ በመውሰድ ስለ እዚኽ የጡረታ ክፍያን በመጉዳት እንደ እዚኹም ሌሎች ተወዳዳሪ መስኮች ያንን ገንዘብ በብድር እንደ አያገኙ በማድረግ ፥
    c. በመንግስት ዋስትና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ብድር በመውሰድ በእዚኽም መንግሥት ለሌሎች ብድሮች ዋስትና የመስጠት አቅሙን በማሟጠጥ እንደ እዚኹም የሐገር ውስጥ የዶላር ገበያን በመሻማት ፥
    d. ሲከፋም ፤ ከሌሎች መሰል ተቋማት ጋር ተመሳሳይ አክሳሪ ብድር በመበደሩ ምክንያት ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ በጋራ እስከ 900 ቢልዮን ብር የእሚደርስ የተበላሸ ብድር በመፍጠሩ ምክንያት ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፤ አይ ኤም ኤፍ ጣልቃ ገብቶ ፤ ለመንግስት እዳ መክፈያውን ብድር ባያበድረው ኖሮ ፤ ከፍተኛ ሐገራዊ ኪሳራ በማስከተል ፥

በአጠቃላይ ፤ 32.33% የእሚሆንን ኃይል ለዴታ ሴንተሮች እና ለውጭ ሐገር ገበያ የእሚሸጠው ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ኤሌክትሪክ ማምረት ርካሽ እና ቀላል በመሆኑ ፤ ያንን ዕድል በመጠቀም እርሱን የገቢ ምንጭ አድርጎ የሐገሩን ተጠቃሚ ለመደጎም ሳይሆን ፦

- ወደ ወንጀለኝነት በእሚጠጋ እንዝህላልነት ከፍተኛ የኃብት ብክነት (Capital Misallocation) በማስከተል ፥
- የገንዘብ ዋጋን እንደ እዚኹም የሸቀጥ ዋጋን በከፍተኛ ደረጃ በማስወደድ እና የዋጋ ግሽበት በመፍጠር ፥
- የግሉ መስክ በቂ ብድር አግኝቶ መስራት እንደ አይችልም የብድር አቅርቦትን በማድረቅ እና የብድር ዋጋን በማናር ፥
- ከፍተኛ የዶላር እጥረት በመፍጠር ፥
- ሐገራዊ ዕዳ በማብዛት ፥
- የመንግስትን የበጀት ጉድለት በማብዛት ፥
- የመንግስትን የግብር ገቢ በማሳነስ ፥ ሥራ ፈጠራን በማዳከም ፥
- በኢኮኖሚ ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግር እንደ አይመጣ ደንቃራ በመሆን ፥

ወይንም በተበላሸ ፖሊሲ ምክንያት ፤ የኢትዮጵያን መንግስት እና ሕዝብ ፤ ከእላይ ለመዘርዘር የተሞከሩትን ዓይነት ከፍተኛ ዋጋ በማስከፈል ነው።

በአጠቃላይ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤ እንደ ተቋም ከስሮ እና ሐገር አክስሮ ፤ አብሮም የማክሮ ኢኮኖሚ አውሎ ንፋስ አስነስቶ ፤ ከሐገር የኃይል ጥየቃ (Demand) በላይ የሆነ ፤ ያለ ዕቅድ የሆነ ኃይል አመንጭቶ ፤ ያን እሚያደርግበት ሲያጣ በመሆኑ ፤ ቀላል የእማይባል ኃይል ለውጭ ገበያ ከዓለም ገበያ በጣም ባነሰ ዋጋ የእሚያቀርበው :-

> *"የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ይኽን ኹሉ የኪሳራ ውርጅብኝ የእሚያስተናግደው ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመግዛት አቅሙ ዝቅተኛ በመሆኑ ፤ ኤሌክትሪክ በድጎማ በርካሽ ስለ እሚሸጥለት ነው ብሎ ማለት"*

የችግሩን ጥልቀት እና የመንግስት የልማታዊነት አካኼድ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብን የመግዛት አቅም ያዳከመበትን መንገድ ያልተረዳ ነው።

ይኽ በሆነበት ኹኔታ ፤ ተቋማቱ እሚከስሩት እና ሲያተርፍም ከኢንቨስትመንት አቅማቸው አንጻር ዝቅተኛ ትርፍ የእሚያተርፉት ፤ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲል ፤ ርካሽ ኤሌክትሪሲቲ ስለ እሚያቀብ ነው እንዴት ሊባል ይችላል ?

ይልቁንም ፡- እጅግ መኃይምነት የእሚነጸባረቅበት የኢትዮጵያ የልማታዊነት መንገድ ፤ የኢትዮጵያ ድኃ የመሸከም ሳይሆን ፤ ኢትዮጵያን የማደህያ ስልት መሆኑን ዓይነተኛ ማሳያ ነው።

### 4.2.2 የውኃ ግድብ ጥሩ የኢንቨስትመንት አማራጭ አይደለም

ኢትዮጵያ ታዳሽ ከእሚባሉት የኃይል ምንጮች በዋናነት ፡- ከውኃ ፣ ከንፋስ እና ከጂኦተርማል ፤ ኃይል ማመንጨት ትችላለች።

ከእያንዳንዱ ታዳሽ መስክም ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኩባንያ ፤ ፋክትስ ኢን ብሪፍ (Facts in Brief) በእሚለው መጽሔቱ ውስጥ ፤ ምን ያኽል ኃይል የማመንጨት ሐገራዊ ዕምቅ አቅም እንደ አለ ፤ ለምሳሌ በ2025 እንደ እሚከተለው ቀርቧል ፡-

| | ተገማጭ የማመንጨት አቅም |
|---|---|
| ከውኃ | 45, 000 MW በላይ |
| ከንፋስ | 1,350, 000 MW በላይ |
| ከጂኦተርማል | 10, 000 MW  በላይ |

ለንፅፅር እንዲረዳ ፤ ኢትዮጵያ ሙሉ የጂኦተርማል አቅሟን ብትጠቀም ፤ 2 የሕዳሴ ግድብ መጠን ያላቸው ግድቦች ማመንጨት የእሚችሉትን የኃይል መጠን ከመሬት ውስጥ በእሚወጣ እንፋሎት ወይንም ከጂኦተርማል ምንጭ ማግኘት ትችላለች።

ትንበያው ትክክል ከሆነ ደግሞ ከንፋስ ኃይል ፤ ከ2 ሺ በላይ የሕዳሴ ግድብ መጠን ያላቸው ግድቦች የእሚያመነጩትን ኃይል ማመንጨት የእሚችል ዕምቅ አቅም አለ ፤ ምንም እንኳን መላ ኢትዮጵያ የንፋስ ማመንጫ ማድረግ የእማይታሰብ ቢሆንም።

ከእላይ ቀደም ብለን እንደ አልነው ፤ ኢትዮጵያ ጠቅላላ ከእምታመነጨው ኃይል 33.60% ለዴታ ሴንተር እና ለውጭ ገበያ እየሸጠች ፤ እንደ እዚያም የተገነቡት እና በሥራ ላይ ያሉት የንፋስ ፣ የውኃ ፣ የባዮማስ (ቆሻሻ ማቃጠል እና መሰል) እና የጂኦተርማል ምንጮች ፤ እንዲያመነጩ ተብሎ ክታሰበላቸው አንጻር ወይንም ሎድ ፋክተራቸው 41% ብቻ በሆነበት ኹኔታ ፤ በ2025 ወይንም በኢትዮጵያ አቆጣጠር 2017 ዓም የነበራት ጠቅላላ የማምረት አቅም 8, 1115.84 MW ነው።

ከእላይ በሰንጠረዡ ለማስቀመጥ እንደ ተሞከረው ፤ ይኽ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ጠቅላላ ኃይል የማንጨት አቅም ወይንም Installed Capacity ኢትዮጵያ በጠቅላላ ከጂኦተርማል ብቻ ማመንጨት ትችላለች ተብሎ ከተቀመጠው አቅም ያነሰ ነው። ምክንያቱም ፡- ወቅታዊ በሥራ ላይ ያለ የማመንጨት አቅም ወይንም Installed Capacity 8,115.84 MW (ስምንት ሺ አንድ መቶ አስራ አምስት MW) ሲሆን ፤ የጂኦተርማል ዕምቅ አቅሙ ግን 10 ሺ MW ነው።

ይኽን ንጽጸር ልዩ ትርጉም የእሚሰጠው ወይንም ይኽን ንጽጽር ማድረግ አስፈላጊ የእሚሆነው ፤ ጂኦተርማል የኃይል ምንጭ ምንም እንኳን ፤ የመጀመሪያ ኢንቨስትመንቱ ከግድግ በላይ ውድ ቢሆንም ፤ አንድ ግዜ ገተገነባ በኋላ ፤ ከግድብ ውኃ የተሻለ አስተማማኝ የኃይል ምንጭ ወይንም የተሻለ Load Factor ያለው በመሆኑ ነው።

በሌላ አገላለጽ ፤ ለምሳሌ ፡- የአባይ ግድብን ለመገንባት 5 ቢልዮን ዶላር ወይንም በወቅቱ ግምታዊ ምንዛሪ መጠን 810 ቢልዮን ወይንም ወደ አንድ ትሪልዮን ብር አውጥታ ገንብታ ፤ በአማካይ የእምታገኘው አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት የእርሱን 41% ወይንም የ332.1 ቢልዮን ብር ነው ፤ የቀረው ወደ ግማሽ ትሪልዮን ብር የእሚጠጋው ኢንቨስትመንት ይባክናል።

በአንጻሩ ግን ፤ በእንፋሎት ኃይል ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ብትሠራ ግን ፤ የጂኦተርማል የኃይል ምንጮች ከ70% እስከ 85% የእሚደርስ አስተማማኝነት ወይንም ሎድ ፋክተር የእሚኖራቸው በመሆኑ ፤ ኢትዮጵያ አንድ የጂኦተርማል ምንጭ ላይ እንደ ህዳሴው ግድብ ዓይነት 810 ቢልዮን ብር ገደማ ኢንቨስት ብታደርግበት ፤ የእሚባክነው ሲበዛ እስከ 243 ቢልዮን (29%) ብር ሲያንስ ደግሞ እስከ 121.5 ቢልዮን ብር (15%) በመሆኑ ፤ የጂኦተርማል ኢነርጂ ምንጭ በጣም ተመራጭ የእሚሆንበት ምክንያት አለ።

ንጽጽሩን እንዲያግዝ ፤ ኤይ አይን እና ኦንላይን የእሚገኙ መረጃዎች በመጠቀም ፡- ውኃ ፣ ንፋስ እና ጂኦተርማል ምንጮች ያላቸውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ለመመልከት እንሞክር፡-

| **Metric / Feature** | **ትላልቅ የውኃ ግድቦች** | **ጂኦተርማል** | **የየብስ ላይ የንፋስ ማመንጫ** |
|---|---|---|---|
| **በአማካይ አንድ ኪሎዋት ለማምረት በዶላር የእሚፈጁት ኢንቨስትመንት** | **$2,000 – $3,500+** | **$3,500 – $5,500** | **$1,200 – $1,800** |
| **ከጠቅላላ አቅም ውስጥ አስተማማኝ አቅም (Load Factor)** | **40% – 50%** | **80% – 90%** | **29% – 45%** |
| **ለግንባታ የእሚፈጁት ግዜ** | **7 – 12+ ዓመታት** | **4 – 6 ዓመታት** | **1 – 3 ዓመታት** |
| **የቅድሚያ ኢንቨትመንት ግዴታ** | **ከፍተኛ** አንድ ሜጋዋት ኤሌክትሪክ እንኳን ለማመንጨት ፤ ግድቡ ሙሉ በሙሉ ተገንብቶ ማለቅ አለበት። | **መካከለኛ ፦** በቂ እንፋሎት መኖሩን ለማረጋገጥ የእሚደረገው ቁፋሮ የተረጋገጠ ወጪ ነው ፤ አንድ ግዜ ግን መኖሩ ከተረጋገጠ ኃይል የማመንጨቱን ጉዳይ እያዩ መጨመር ስለ እሚቻል የቅድሚያ ኢንቨስትመንት ጫናው መካከለኛ የእሚባል ነው። | **ዝቅተኛ.** አንድ ኹለት እያሉ እንደ አስፈላጊነቱ ፤ በተናጠል ማሳደግ ስለ እሚቻል ፤ ቅድመ ኢንቨስትመንቱ ዝቅተኛ ነው። በአንድ ግዜ አስር ተርባይን ትከል የእሚል ግዴታ የለም። |
| **ለአየር ንብረት መለዋወጥ ያለው ተጋላጭነት** | **ከፍተኛ ፦ በድርቅ እና በዝናብ መለዋወጥ ምክንያት በጣም የማምረት አቅሙ ይወሰናል።** | **ምንም ዓይነት የአየር ንብረት ተጋላጭነት የለውም። ቢዘንብ ባይዘንብ ይሠራል።** | **ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ፦ በወቅቱ በንፋስ ፍጥነት ላይ ብቻ ይደገፋል።** |

እንደ እሚታየው ፤ ሶሥቱም የኃይል ምንጬች ፤ የእየራሳቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎን አላቸው።

ለመገንበት ከእሚፈልጉት ዋጋ አንጻር ካየነው ፤ ንፋስ በጣም ይረክሳል ፤ ውኃ መካከለኛ ነው ፤ ጂኦተርማል ግን ውድ ነው።

ሆኖም ከተገነቡ በኋላ ፤ ከአቅማቸው አንጻር የማመንጨት አቅማቸው ካየን ፤ ጂኦተርማሉ ከ80% እስከ 90% ከአቅሙ አንጻር አስተማማኝ አመንጪነት አለው። በእዚኽ ረገድ የንፋስ ኃይል ማመንጫዎች በጣም ዝቅተኛ አስተማማኝነት ነው ያላቸው።

በተለይ ደግሞ ጂኦተርማል ፤ የግድብን ኹለት እጥፍ ሊባል የእሚችል አስተማማኝነት ስለ አለው ፤ ለምሳሌ ፦

- የውኃ ግድብ የ8 ጊጋ ዋት የማመንጨት አቅም ኖሮት በአስተማማኝነት የእሚያመነጨው 3.5 ጊጋ ዋት ሊሆን ይችላል ፥
- የጂኦተርማል ማመንጫ የ4 ጊጋ ዋት የማመንጨት አቅም ኖሮት በአስተማማኝነት የእሚያመነጨው ከ3.2 እስከ 3.6 ጊጋ ዋት ሊሆን ይችላል፤

ምንም እንኳን መገንቢያ ዋጋው ከግድብ አንጻር ውድ ቢሆንም ፤ ኹለት ግድብ በእሚገነባበት ገንዘብ አንድ ጂኦተርማል ማመንጫ ገንብቶ ተመሳሳይ ምን አልባትም የበለጠ አስተማማኝ ኃይል ማግኘት ይቻላል።

ስለ እዚኽ ፦ መስኩ በገበያ ቢመራ እና ተወዳዳሪነት ፣ ተጠያቂነት እንደ እዚኹም ግልጸኝነት ቢኖር ኖሮ ፤ እያንዳንዷ ዶላር እንዴት ተደርጋ ኢንቨስት ብትደርግ ፤ የበለጠ ኃይል ማመንጨት ትችላለች በእሚል ኢንቨስት ትደረግ ስለ ነበር ፤ ከ97% በላይ የሆነው የሐገሪቱ ኃይል ምንጭ ፤ መካከለኛ የእሚባል እና በኢትዮጵያ ኹኔታ 41% ብቻ አስተማማኝነት ያለው የግድብ ውኃ ብቻ አይሆንም ነበር።

ይኽም ማለት ፦ ለምሳሌ ፦ በ2025 ፤ 8,115.84 ሜጋ ዋት የእሚያመነጭ አቅም ገንብተን ፤ የእምናመነጨው ዓመታዊ አማካይ 3, 327.49 ሜጋ ዋት በመሆኑ ፤ የቀረው ወደ 4,788.35 ሜጋ ዋት የእሚሆነው ፤ ኢንቨስት ያደረግንበት ግን የእማንጠቀምበት አይሆንም ነበር።

በተግባር በሪፖርቱ እንደ ታየው ግን ፤ የማመንጨት አቅም (Installed Capacity) ከእሚባለው 8,115.84 ሜጋ ዋት ውስጥ በ2025 ለዴታ ሴንተር እና ለውጭ ሐገር ኤክስፖርት የተደረገውንም ጨምሮ ፤ ከጠቅላላው የማመንጨት አቅም ውስጥ ፤ በዓመቱ በአማካይ የተጠቀምነው 41% ብቻ እርሱም 3, 327.49 ሜጋ ዋት ሲሆን ፤ የቀረው በብዙ ቢልዮን ዶላሮች በብዙ ዓመታት ቢፈስበትም ፤ ገዢ በማጣት ወይንም በአየር ንብረት መቀያየር ምክንያት ፤ የታቀደለትን ኃይል መጠን ማመንጨት ስለ አልተቻለ ፤ ያ ኹሉ ኢንቨስትመንት ቁጭ ብሎ እየበሰበሰ ነው።

ለእዚያም ይመስላል ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አንዱ ከፍተኛ የኪሳራ ምንጭ ፤ ዓመታዊ እርጅና (Depreciation) የሆነው። ያም ፦ ንብረቱ ፤ ኢንቨስትመንቱን የእሚተካ ኃይል አመንጭቶ እና ሸጦ ፤ ወጪውን ከመሸፈን በፊት ፤ በእርጅና ምክንያት ዋጋውን በከፍተኛ ደረጃ እንዲ ቀንስ ያደርገዋል።

የማመንጫ ኢንቨስትመንቱ ፡- በመንግሥት የልማታዊነት እሳቤ እና ለታይታ በእሚደረጉ ፕሮጀክቶች (Prestige Projects) ከእሚሆን ይልቅ ፤ በተገቢው የኮርፖሬት የኢንቨስትመንት አስተቃቀድ መሰረት ቢሆን ይኸ ብክነት ፤ ከእነ ብዙ ተዛማጅ ችግሮቹ በከፍተኛ ደረጃ ይቀንስ ነበር።

ለምሳሌ ፡- እንደ ኤልኒኖ ባለ የተፈጥሮ ክስተት ምክንያት የአየር ጠባይ መዛባት ተፈጥሮ ድርቅ ሲከሰት እና የዝናብ መጠን መቀነስ የግድቦችን የውኃ መጠን ሲቀንስ ፤ ንፋስ ስለ እሚበዛ ፤ መካከለኛ ውዱን ውኃ እና በጣም ርካሹን ንፋስ ማጣመር ፤ ሐገራዊ ግሪድ ሎድ ፋክተር ፤ የተሻለ የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም አቅም እንዲኖረው ያደርጋል።

ለንጽጽር ኬንጄን (KENGEN) የእሚባለውን ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ትዩዩ የሆነውን የኬንያውን የኃይል አመንጪ አፈጻጸም እንመልከት።

አንደኛው እና የኬንያውን ኃይል አመንጪ ከኢትዮጵያ የእሚለየው ፤ ኩባንያው ብቸኛ የኃይል አመንጪ ባለመሆኑ ፤ 46% የእሚሆነው የኬንያ የኃይል ፍላጎት ፡- በግሉ መስክ እና እንደ ኢትዮጵያ ፣ ታንዛንያ እና ዩጋንዳ ካሉ ሐገራት ኢምፖርት የእሚያደርገው መሆኑ ነው።

ተቋሙ ስለ ኃይል አመነጫጨት ስብጥሩ ፤ በጣም ፕሮፌሽናል በሆነ መልኩ በተዘጋጀው የ2025 ዓመታዊ የኮርፖሬት ሪፖርቱ ላይ እንዲኽ በእሚል ተቀምጧል (የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ይኽን የሪፖርት ስረዓት መጀመር አለበት )፦

> *"በእዚኽ ወቅት ፤ በጥቅላላው 1,786 ሜጋዋት የተተከለ የማመንጨት አቅም ይዞ ፤ ኬንጀን የአከባቢው አንዱ ግዙፍ የኃይል አመንጪ ነው። ከእዚኽ ውስጥ ፡- 826 ሜጋዋት ከግድብ ውኃ ፥ 754 ሜጋዋት ከጂኦተርማል ፥ 180 ሜጋ ዋት ከሙቀት እና 26 ሜጋ ዋት ክንፋስ የእምናመነጭ በመሆናችን ፤ እያዳበርን ላለነው የአረንጓዴ ኃይል ባሕል እና ለፈጠራ ችሎታችን ምልክት ነው።"*

> *"Today, with a robust 1,786MW installed capacity and a commanding 54% market share, KenGen is the energy giant of the region. Our power mix Hydro (826MW), Geothermal (754MW), Thermal (180MW), and Wind (26MW) reflects a balance of green heritage and innovation."*

ይኸን የኃይል አመነጫጨት ስብጥር ፤ 97% በላይ ከግድብ ውኃ ከእሚያመነጨው ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር ፤ ስብጥሩን በፐርሰንት አስቀምጠን እናነፃፅር ፡-

| | በሜጋ ዋት የእሚመነጨው | የተናጠል ሎድ ፋክተር |
|---|---|---|
| ከውኃ | 826 | 46.24% |
| ከጂኦተርማል | 754 | 42.21% |
| ከተርማል (ከሙቀት) | 180 | 10.00% |
| ከንፋስ | 26 | 1.4% |
| ድምር | 1,786 | ~100% (weighted Average) |

እንደ እሚታየው ፤ ኢትዮጵያም እንደ ኬንያ ስምጥ ሸለቆ ያለበት አከባቢ ውስጥ ብትሆንም እና ከፍተኛ ኃይል ከጂኦተርማል ማመንጨት ብትችልም ፤ ወረድ ብለን እንደ እምናየው ፤ መስኩ አንድ ግለሰብ የእሚያመነጨው ዓይነት 7ሜጋ ዋት ዓይነት ኃይል ከማመንጨት ውጭ ምንም አልተሠራበትም።

በኬንያ እንደ እሚታየው ፤ ጂኦተርማሉ የውሃ ግድቡን ያኽል እያመነጨ ነው። በእርግጥ ኢትዮጵያ ከኬንያ ይልቅ የተሻለ ከግድብ ውኃ ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅም አላት ሊባል ይችላል ፤ እዚኽ ጋር ግን እያነጻጸርን ያለነው ፤ ኢትዮጵያ ከውኃ ኃይል የማመንጨት አቅሟ እንዴት ከኬንያ ጋር ይወዳደራል ሳይሆን ፤ ኢትዮጵያ የተለያየ የኃይል ምንጮችን በመጠቀም ሊገኝ የእሚችለውን የተሻሻለ አፈጻጸም ምን ያኽል እየተጠቀመችበት ? ነው።

በመሆኑም ፤ ኬንያ ከእላይ በተመለከተው መንገድ ፤ የኃይል ማመንጫ ምንጮቿን እንደ ኢትዮጵያ በአንዱ ላይ ብቻ ከመንጠልጠል ይልቅ ከእየ አይነቱ ቀይጣ ስለ አሰባጠረቻቸው ፤ ከ97% በላይ በግድብ ውኃ ላይ ብቻ ከእምተደገፈው ኢትዮጵያ ይልቅ ሎድ ፋክተሯን ወይንም የኃይል እጥረት የማጋጠም ችግርን ከ14% በላይ አሻሽላ እናያለን።

ኬንጀን በእዚኽ የኃይል ስብጥሩ ምክንያት ሊያገኝ የእሚችለውን ግምታዊ ሎድ ፋክተር ዕንመልከት ፡-

| | በሜጋ ዋት የእሚመነጨው | የተናጠል ሎድ ፋክተር |
|---|---|---|
| ከውኃ | 826 | 48.86% |
| ከጂኦተርማል | 754 | 70.54% |
| ከተርማል (ከሙቀት) | 180 | 33.65% |
| ከንፋስ | 26 | 21.6% |
| ድምር | 1,786 | 56.08% (weighted Average) |

በአንጻሩ ከ93% በላይ በግድብ ውኃ ላይ የእምትደገፈው ኢትዮጵያ ፤ ሎድ ፋክተሯ 41% ሆኖ ነው የእምናገኛት ፤ ምክንያቱም ፡- ከግድብ ውኃ ማመንጨት በአንጻራዊነት ርካሽ ኢንቨስትመንት ቢፈልግም እና በኢትዮጵያም ከፍተኛ ከውኃ ኃይል የማመንጨት ብዙ እምቅ አቅም ቢኖርም ፤ ከውኃ ኃይል ማመንጨት ግን በድርቅ እና በደለል ምክንያት ፤ አስተማማኝነቱ ዝቅተኛ በመሆኑ ፤ ሎድ ፋክተሩን ዝቅ አድርጉታል።

ይኽም ማለት ፡- በምሳሌ እናስቀምጠው ብንል 100 ሚልዮን ብር ኢንቨስት አድርገን የ41 ሚልዮን ብር ጥቅም ነው እምናገኘው ማለት ነው ፤ በአንፃሩ ኬንያዎች 100 ሚልዮን ብር ኢንቨስት አድርገው ከ50 ሚልዮን ብር በላይ ይጠቀማሉ።

እንደገና ይኽም ማለት ፡- ኢትዮጵያ በእያንዳንዱ 100 ሚልዮን ብር ወደ 9 ሚልዮን ትከስራለች ማለት ነው።

ኃይል ማመንጨት ደግሞ በሚልዮኖች ሳይሆን በርካታ ቢልዮኖች የእሚፈጅ በመሆኑ ፤ በተበላሸ ፖሊሲ ምክንያት ፤ ተቃዋሚ እና ተቺ በሌለበት ፤ ኃይል በማመንጨት ታላቅ ስራ እየሰራን ከሐገራችን አልፈን የጎረቤቶች ተስፋ ሆነናል በእሚል ፤ የሞኝ ፕሮፖጋንዳ ብንነዛም ፤ ከላይ በጠቀሰው መልኩ ፡-

- የብድር ገበያውን ትርምስምሱን አውጥተን ፥
- የጡረታ ገንዘብ አግተን ይዘን ፥
- የዶላር እጥረት ፈጥረን ፥
- ኑሮ አስወድደን ፥
- የመንግሥትን ዕዳ ጨምረን ፥
- የመንግሥትን ግብር ቀንሰን ፥

በአጠቃላይ ከፍተኛ የማክሮ ኢኮኖሚ ቀውስ ፈጥረን ፤ በቢልዮኖች አውጥተን ከእምንገነባው ግድብ ፤ የኃይል ምንጮቻችንን ባለመቀየጣችን ምክንያት ብቻ ፤ በቢልዮን ብር እያባከንን ነው።

አኹንም በድጋሚ ፡- ይኽ በሆነበት ኹኔታ ፤ ማለትም በልማታዊነት ስም የጅል ኢንቨስትመንት በማድረግ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መስክ የእሚከስረው ኪሳራ እያለ እንዴት ዋነኛው የተቋሙ የክስረት ምንጭ ድኃውን የኢትዮጵያ ሕዝብ መደጎሙ ነው ሊያስብል እንዴት ይቻላል ?

### 4.2.3 41% ሎድ ፋክተር ፤ ምክንያት ሊቀርብበት ቢችልም ጥሩ እሚባል አይደለም

ከእላይ ያለውን ንጽጽር ፤ ማለትም ፡- ኢትዮጵያ የኃይል ምንጯን በአቅሟ መሠረት ስለ አልቀየጠች ፤ የኃይል ምንጯን አስተማማኝነት ከመቀነስ ባሻገር ከፍተኛ መጠን ያለው የኃብት ብክነት አስከትላለች የእሚለውን ትችት ያቀረብነው ፤ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሪፖርት የተደረገውን 41% ሎድ ፋክተር ፤ ከውኃ ግድቦች የእሚጠበቅ መደበኛ የብክነት መጠን ነው በእሚል ተቀብለን ነው።

በ2025 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) በዓመት ማመንጨት ከእሚችለው 71, 100 GWh የኤሌክትሪክ ኃይል ፤ 33.60 % ለቢትኮይን ማይነሮች እና የቀረውንም ለጎረቤት ሐገራት ፡- ሱዳን ፣ ኬንያ እና ጅቡቲ ሸጦ እንኳን ፤ ያመነጨው 29, 467 GWh ወይንም የማመንጨት አቅሙን 41% ብቻ ነው።

በእርግጥ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) ፤ ከ97% በላይ ኃይሉን የእሚያመነጨ ከውኃ ግድብ በመሆኑ እና የውኃ ግድብ ደግሞ ፡- በድርቅ ፣ በዝናብ ፣ በግድብ ውኃ መጠን ፣ ወዘተ ስለ እሚወሰን ፤ 41% የማመንጨት አቅሙን መጠቀሙ ፤ ከውኃ ግድቦች ባሕሪያት የተነሳ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል።

እንደ እኔ ፤ ይኽ ግን ሶሥት ጥያቄ አዘል ትችቶችን ማስነሳቱ ግን አይቀርም ፡-

1. በኬንያ እስከ 48% የእሚደርስ የግድቦች የሎድ ፋክተር ሪፖርት ተደርጓል ፥
2. የእኛ 41% የደረሰው ፤ ከአመረትነው ኃይል 33.60 % ለውጭ ሸጠን በመሆኑ ፤ ንብረታችንን እና ኢንቨስትመንታችንን በአግባብ መጠቀማችንን አያሳይም ፥
3. እንደ ደኃ ሐገር ፤ ገንዘብ ቆጥበን የስጋት መጨመር እንጂ ገንዘብ እንደ አሻ አፍስሶ ፤ የስጋት መጠን መቀነስ ፤ ብቁ የኃብት አስተዳደር ጥበብን አያሳይም ፥

እነ እዚኽን በዝርዝር ዕንመልከት።

አንደኛ ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) ፤ ማመንጨት ከእምችለው አንጻር 41% ብቻ ያመነጨኹት ፤ እንደ ደኃ ሐገር በአንጻራዊነት ርካሽ እና የተሻለ ኃይል ማመንጨት የእሚችለውን ነገር ግን ሎድ ፋክተሩ 41% አከባቢ የሆነውን የውኃ ግድብ ዋነኛ የኃይል ምንጬ በማድረግ እና ግድብ ደግሞ በድርቅ እና በውኃ መጠን መቀያየር የማመንጨት አቅሙ ስለ እሚወሰን እንጂ ፤ ደካማ ኢንቨስትመንት እና ፍላጎት የማመጣጠን ሥራ ስለ ሠራኹ ወይንም ደካማ የሆነ የማመንጫ አስተዳደር ስለ

ነበረኝ ነው እንደ አይል ፤ ሩቅ ሳንኼድ ጎረቤታችን ኬንያ ፤ የግድብ ውኃን የኢትዮጵያን ያኽል ባይሆንም ከፍተኛው የኤሌክትሪክ ኃይል ምንጫቸው አድርገው ፤ በ2025 ሪፖርት ያደረጉት ሎድ ፋክተር ከኢትዮጵያው በ8% በልጦ 48% ደርሶ እናገኘዋለ።

ስለ እዚኽ ፦ ከሞላ ጎደል ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይ የእሚባል አየር ንብረት እና የማሕበረ ኢኮኖሚ ደረጃ ያላቸው ፤ ኬንያዊያን ግድባቸውን ከኢትዮጵያ በተሻለ ከተጠቀሙበት ፤ እኛ የኢንጂነሪንግም ሆነ የአየር ንብረት ልዩ ባሕሪ በምክንያትነት ልናቀርብ አንችልም።

ለሐገር ውስጥ ከእምንሸጠው በላይ ለውጭ ሐገር ሸጠንም ጭምር ፤ የማመንጨት አቅማችንን 41% ብቻ የእምንጠቀምበት ብቸኛ ምክንያት ፦

- አይደለም ለሐገር ውስጥ ገበያ ፤ ኤክስፖርት እና ለንፋስ አመጣሽ ዴታ ማይነሮች ከተመረው ጠቅላላ ኃይል 33.60% እንኳን ሸጠን ኃይል የማመንጨት አቅማችን በሐገራችንም ሆነ በአከባቢያችን ካለው የኃይል ጥየቃ (Actual Demand) አንጻር ዝቅተኛ ስለ ሆነ ፤ ስለ እዚኽ ፦ በጣም ከፍተኛ የኃብት ብክነት (Capital Misallocation) ስለ አለን ነው ፥
- ካልሆነም ፦ ከንብረት ኹሉ ጠንካራው የመንግሥት ንብረት ነው እንደ እሚባለው ፤ የግድብ አስተዳደራችን ፤ የግድቦችን አቅም በተገቢው መልኩ ሥራ ላይ ማዋል በእሚቻልበት መንገድ አልነበረም ፥

በአጠቃላይ በደካማ አፈጻጸም ምክንያት ነው።

ገበያ ቢሆን በፍጹም እንደ እዚኽ ዓይነት ስህተት አይሠራም።

ኹለተኛ ፦ በእዚኽ መልኩ የአስተዳደር መበላሸት (mismanagement) በእሚታይበት መልኩ ኃይል እያመነጨን እና የሎድ ፋክተራችን 41% በሆነበት ኹኔታ ፤ በሐገራችን ያለው የኤሌክትሪክ ተደራሽነት 29% በሆነበት ኹኔታ ፤ ከእምናመርተው ኃይል 33.60% ለቅንጡተኛ እና ለጎረቤት ሐገር የእምንሸጥ በመሆናችን ፤ 41% ሎድ ፋክተር እንደ አንድ ተፈጥሯዊ ሎድ ፋክተር ተደርጎ የእሚወሰድ አይደለም።

እንደ እዚያ በሆነበት ኹኔታ ፦

- ንግድ ባንክን እያከሰርን ፥
- ገንዘብ እያተምን ፥
- የውጭ ምንዛሪ ዕዳ በሐገር ላይ እየጫንን እና በእነ እዚኽም ምክንያት ፦
    - የዋጋ ግሽበት እያስከተልን ፣
    - የገንዘብ ወለድ መጠን ከፍ እያደረግን ፣
    - በእዚኽም የዜጎችን የማምረት አቅም እየቀነስን እና በእዚኽም የዜጎችን የመግዛት አቅም እየጎዳን ፤ ባለንበት ኹኔታ ፤

ይኸን ኹሉ ዋጋ ሐገርን እና ሕዝብን አስከፍለን በእዚኽ መልኩ ከፍተኛ መጠን ያለው የኃይል ማመንጫ ኢንቨስትመንት እምናደርገው ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አቅምን ያገናዘበ እና ተደራሽ የሆነ ኤሌክትሪክ ለማቅረብ ነው ልንል አንችልም።

ለኢትዮጵያዊ ከእምንሸጠው በላይ ፤ ለውጭ ሐገር ዜጎች እየሸጥን ፤ ለኢትዮጵያዊ ስንል ነው ብሎ ነገር ፤ በፍጹም ሊኖር አይችልም።

ሶሥተኛ ፦ ኢትዮጵያ በጣም ድኃ ሐገር በመሆኗ እና በከፍተኛ ክፍያ ከእሚገኝ ዋስትና በፊት ያላትን ኃብት በአግባቡ መጠቀም በጣም የእሚቀድም በመሆኑ ፤ ይኸን ኹሉ በብዙ መቶ በቢልዮኖች የእሚቆጠሩ ኢንቨስትመንት አድርገን ፤ 41% የእምንጠቀመው ፤ የኃይል መቆራረጥ የሌለበት አስተማማኝ አገልግሎት ለማቅረብ ነው ብንል ፤ በእራሳችን የምናፌዝ አሳዛኝ ሕዝብ እንጂ ስጋት ለመቀነስ የእሚሠራ ሕዝብ ልንሆን አንችልም።

## 4.2.4 በኢትዮጵያ ኃይል ማመንጨት እንጂ መሸጥ የእቅዱ አካል አይመስልም

ኢትዮጵያ ውስጥ በቅርቡ ፤ ማለትም ፦ ባለፈው ሦሥት እና አራት ዓመታት ፤ ለማስተዋል እንደ ቻልኩት ፦ እንደ ኢትዮጵያ ስታቲስትክስ አገልግሎት ፣ ብሔራዊ ባንክ ፣በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ሚንስትር ፣ አሁን ደግሞ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (Ethiopian Electric Utility) ፤ ግልጸኝነት እና ተጠያቂነት በከፍተኛ ደረጃ ተዳክሞ ፤ ከእዚኽ በፊት በእየ ዓመቱ እየተዘጋጁ የእሚቀርቡ መረጃዎችን ማግኘት አዳጋች መሆኑ ነው።

ከእዚኽም የተነሳ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዌብሳይት ላይ ፤ ፋክትስ ኢን ብሪፍ (Facts in Brief) የእምትለው እና በተሰባበረ መልኩም ቢሆን ፤ ስለ ተቋሙ መረጃ እምትሰጠው መጽሔት ከ2021/2022 ማለትም ከኢትዮጵያ 2014 በኋላ ማግኘት አይቻልም።

በመሆኑም ፦ ይኽ ትንተና በእሚሠራበት ፤ በኢትይጵያ አቆጣጠር 2019 ላይ ፤ ከ2014 በኋላ የተሰሩ ሥራዎችን ያካተተ ድምር ሪፖርት ማግኘት ስለ አልተቻለ ፤ በእዚኽ የእማቀርበውን መረጃ ፤ መነሻውን የ2021/2022 ፋክትስ ኢን ብሪፍ እና ፈለገ ብርኃን በእሚል የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የእሚያሳትማቸውን መጽሔቶች በመጠቀም ፤ ስለ እዚኽ ፦ መነሻውን በኢትዮጵያ አቆጣጠር 2014 ዓም አድርጌ ፤ ከእዚያ በኋላ በእየ ግዜው የእሚወጣውን ዓመታዊ ሪፖርት በመጠቀም ፤ አሁን ላይ ስንት ሊደርስ ይችላል በእሚል ግምታዊ ማገጫጨት ነው።

በእዚኽም መሠረት ፤ በኢትዮጵያ አቆጣጠር የ2014ቱ ፋክትስ ኢን ብሪፍ ፤ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (Ethiopian Electric Utility) ሥር ያሉ ፤ የኃይል ማከፋፈያ እና ማሰራጫዎች ርዝመት ፤ በእሚከተለው መልክ ሪፖርት ተደርጓል ፦

| ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች (Power Transmission Lines) | |
|---|---|
| የማስተላለፊያ አቅም በኪሎ ቮልት | ጠቅላላ የአስተላላፊ ርዝመት በኪሎ ሜትር |
| 132 KV and above[3] | 21, 335 KM |
| ድምር | 21, 335 KM |
| 45 KV | 177 KM |
| 66KV | 1,731 KM |
| ድምር | 1,908 KM |
| | |
| የኃይል ማከፋፈያ መስመሮች (Power Distribution Lines) | |
| የማከፋፈያ አቅም በኪሎ ቮልት | |
| መካከለኛ ፦ 15KV/33KV | 54, 300 KM |
| ዝቅተኛ ፦ o.38KV/0.22KV (380V/220V) | 60, 704 KM |
| ድምር | 115,004 KM |
| ጠቅላላ አስተላላፊ እና አከፋፋይ መስመሮች | 116,912 KM |

ፈለገ ብርኃን በእሚለው መጽሔቱ ፤ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሰኔ 2018 ተቋሙ ፤ በ9 ወር በመካከለኛ እና ዝቅተኛ የማከፋፈያ መሥመሮች ላይ በሠራኹት ሥራ በጠቅላላው የ9, 568 ኪሜ ጭማሪ አድርጌያለኹ ስለ እሚል ፦

> *"የኢትየጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ባለፉት ዘጠኝ ወራት አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር ባከናወነው ስራ 9 ሺህ 588 ኪሎ ሜትር አዳዲስ የዲስትሪቢዩሽን መስመሮች ማስፋፊያ/ዝርጋታ አከናውኗል። ከዚህ ውስጥ 3 ሺህ 518 ኪ.ሜ የመካከለኛ መስመር፣ 6 ሺህ 69 ኪ.ሜ ደግሞ የዝቅተኛ መስመር ዝርጋታ የተከናወነበት ነው። በተጨማሪም የኃይል አቅርቦቱን የሚያሳድጉ 3 ሺህ 683 የተለያዩ ዓቅም ያላቸው አዲስ የዲስትሪቡዩሽን ትራንስፎርመሮች ተከላ ተከናውኗል።"*

ተቋሙ በአማካይ በአመት 10 ሺ ኪሜ ርቀት የእሚሸፍን የማስፋፊያ ሥራ ይሠራል ብለን ብንል ፤ ከ2015 እስከ 2018 በነበሩት አራት ዓመታት ፤ በጠቅላላ በመካከለኛ እና በዝቅተኛ የማከፋፈያ መስመሮች

[3] ይኽ ቁጥር የመጣው ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) የ2025/2026 ወይንም የኢትዮጳይ 2017 ዓም ላይ በቀረበ ፤ ተቋሙ ፋክትስ (Facts) በእሚል ከእሚያሳትመው መጽሔት ነው። ለመረጃ ያኽል 132KV and ከእዚያ በላይ ያሉ አስተላላፊዎችን የእሚያስተዳድረው የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ሲሆን ፤ 66KV እና ከእዚያ በታች ያሉትን ደግሞ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ነው የእሚያስተዳድረው ፤ ለእዚያ ነው ለእየ ብቻ ሪፖርት የእሚደረጉት።

ላይ የ40ሺ ኪሜ ማስፋፊያ ይሠራል በእሚል ታሳቢነት ፤ በ2018 ዓም ባለቀው የበጀት ዓመት ፤ ጠቅላላ የማከፋፈያ መስመሮች ርዝመት ፤ 156, 912 ኪሜ ገደማ ነው ማለት እንችላለን።

ስለ እዚኽ ፦ እስከ ኢትዮጵያ 2018 ዓም ፤ ኹሉንም ብንደምራቸው ፤ የማስተላለፊያ እና የማከፋፈያ መስመሮች ተደምረው ፤ ከ160 ሺ ኪሎሜትር በላይ አይበልጡም ።

እንደ ኢትዮጵያዊያን የተጠናወተን ፤ እራሳችንን ከእራሳችን ጋር እያነጻጸርን ፤ በባዶ አቅም ፤ እጅግ ተዓምራዊ ዕድገት እያደረግን ነው በእሚል ራሳችንን ማታለል ሱስ ላለብን ፤ እንደ ቁጥር 160 ሺ ኪሎ ሜትር የማስተላለፊያ እና የማከፋፈያ መስመር ርቀት ወይንም በዓመት 10 ሺ ኪሜ የእሚሸፍን የማስፋፊያ ሥራ ሠራን ማለት ፤ ትልቅ ሊመስል ይችላል።

ሆኖም ፦ ብዙም ሩቅ ሳንኼድ ራሳችንን ከኬንያ ጋር ስናነጻጽር ፤ ምን ያኽል ጉድለት እንደ አለብን ግልጥ ብሎ ይታያል።

በኬንያ ኃይል እና ፔትሮሊየም ሚኒስትሪ (Ministry of Energy and Petroleum) ስር የእሚገኘው የኃይል ክፍል (State Department for Energy) ባወጣው የኬንያ ከ2025 – 2034 ብሔራዊ የኃይል ፖሊሲ (National Energy Policy) በ ዲሴምበር 2024 ላይ የእሚገኘው የማስተላለፊያ እና የማከፋፈያ መስመሮች ርዝመት (Length of Transmission and Distribution Lines) ቀርቧል (ገጽ 9 እና 10)።

እዚያ ላይ የቀረበውን መረጃ በሰንጠረዥ መልክ በእሚከተለው መልኩ አስቀምጨዋለኹ ፦

| ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች (Power Transmission Lines) | |
|---|---|
| የማስተላለፊያ አቅም በኪሎ ቮልት | ጠቅላላ የአስተላላፊ ርዝመት በኪሎ ሜትር |
| 132 KV and above | 9,484 KM |
| ድምር | 9,484 KM |
| | |
| የኃይል ማከፋፈያ መስመሮች (Power Distribution Lines) | |
| የማከፋፈያ አቅም በኪሎ ቮልት | |
| 66KV እና ከእዚያ በታች ያሉ (መለስተኛ ማስተላለፊያዎች እና ማከፋፈያዎች ጠቅላላ ድምር) | 302, 256 KM |
| ድምር | 302, 256 KM |
| ጠቅላላ አስተላላፊ እና አከፋፋይ መስመሮች | 311,740 KM |

በኬንያው KPLC and KENGEN የእሚቀርቡት ዓመታዊ ሪፖርቶች ፤ የማስተላለፊያም ሆነ የማሰራጫ መስመር ዓመታዊ ጭማሪያቸው ፤ በመቶ ኪሎ ሜትሮች ብቻ ስለ ሆነ ፤ ከ2024 በኋላ ያለው ጭማሪ ብዙም ለውጥ ስለ እማያመጣ ፤ ከእላይ የተቀመጠውን 311, 740 KM እንደ ኬንያ የማስተላለፊያ እና የማሰራጫ መስመር ርቀት መጠን እንውሰድ።

በእዚኽ ላይ ተመሥርተን ፤ የእሚከተሉትን ንጽጽር እናድርግ ፦

1. የተገላቢጦሽ ተዛምዶ (Inverse Relation)[4]

በኃይል ማስተላለፊያ እና ማከፋፈያ ርቀት ጉዳይ ፤ በኢትዮጵያ እና በኬንያ መካከል የተገላቢጦሽ ተዛምዶ ይስተዋላል።ምክንያቱም ፦ በኃይል ማስተላለፊያ ርቀት አንጻር ስናይ ኢትዮጵያ የኬንያን የኃይል ማስተላለፊያ ርቀት እጥፍ የእሚሸፍን የኃይል አስተላላፊ ርቀት ሲኖራት ፤ በአንጻሩ ወደ ማከፋፈያው ስንመጣ ደግሞ ኬንያ የኢትዮጵያን ጠቅላላ የማከፋፈያ ርቀት ኬንያ ከእጥፍ በላይ የእምትሸፍን መሆኑ ነው።

በኢትዮጵያ 132KV እና ከእዚያ በላይ ያሉ ከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያዎች ጠቅላላ የሰርኪውት ርቀታቸው 21, 335 KM ሲሆን በአንጻሩ የኬንያው ከእዚኽ በግማሽ በላይ በማነስ 9,484 KM ሆኖ እናገኘዋለን።

[4] በነገራችን ላይ ፦ ከእዚኽ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባይኖረውም ፤ ይኽ የተገላቢጦሽ ተዛምዶ ፤ በቅድመ ክፍያ እና በድህረ ክፍያ ደንበኞች መካከልም ይገኛል። ምክንያቱም ፦ በኬንያ የቅድመ ክፍያ ተጠቃሚ ደንበኞች ወደ 85% ሲሆን የድህረ ክፍያ ደንበኞች መጠን ደግሞ ወደ 15% በመቶ ነው። በአንጻሩ በኢትዮጵያ ደግሞ የቅድመ ክፍያ ተጠቃሚ ደንበኞች ወደ 15% ሲሆን የድህረ ክፍያ ተጠቃሚ ደንበኞች ደግሞ ወደ 85% ነው። ከእዚኽ የተነሳ ፤ ከግማሽ በላይ የእሚሆኑት ከፍተኛ ድጎማ የእሚደረግላቸው ደንበኞች ፤ የድህረ ክፍያ ተጠቃሚዎች ፤ በአገልግሎት ክፍያ ምክንያት ፤ በድጎማ ምክንያት የእሚከፍሉትን ክፍያ መጠን ግማሹን ያክል ለአገልግሎት ማለትም ፤ ለቆጣሪ ማንበቢያ እና መሰል አገልግሎቶች ይከፍላሉ። ለእዚኽም ምክንያቱም ፦ ለምሳሌ ፦ የዶላር እጥረት በመኖሩ እና መንግስት የቅድመ ክፍያ ቆጣሪዎችን በበቂ ኹኔታ ማስገባት ስለ እማይችል እንደ ሆነ ይገመታል። ይኸም ፦ የመንግሥት ፖሊሲ ብዙ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት መፍጠሩ ችግሩን ዘርፈ ብዙ አድርጎታል።

ይኸም ማለት ከኃይል ማመንጫዎች ኃይሉን ተሸክሞ ወደ ማከፋፈያዎች በእሚያስገቡ መስመሮች ጉዳይ ፤ ኢትዮጵያ የኬንያን እጥፍ ዝርጋታ አላት።

ከ66KV እና ከእዚያ በታች ባሉት ፦ መለስተኛ ማስተላለፊያዎች እና ማከፋፈያዎች በእሚባሉት እና በዋናናት በኃይል አምራቹ ፤ ለምሳሌ ፦ በኢትዮጵያ ፦ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና በኬንያ በKPLC በእሚተዳደሩት መስመሮች ደግሞ ፤ ኢትዮጵያ በጠቅላላ ርቀት ወደ 145 ሺ ኪሎ ሜትር የእሚረዝም ማሰራጫ መስመሮች ሲኖሯት ፤ ኬንያ በአንጻሩ ከእዚያ ከእጥፍ በላይ የእሚበልጥ ፤ በጠቅላላው የ302, 256 KM ርቀት ሽፍና እናገኛለን።

ምንም እንኳን ፤ በእኔ ዕምነት ፤ ይኸ ልዩነት ፤ ጠለቅ ያለ ሞያዊ ውይይት ቢያስፈልገውም ፦ በኤአይ እርዳታ እና በእራስ ግምገማ ያገኘኹት ማብራሪያ የእሚከተለውን የእሚመስል ነው ፦

- አንደኛ ፦ ኢትዮጵያ የኃይል ማመንጫዎቿን በአንዳች ምክንያት አራምባ እና ቆቦ አድርጋ ስለ ገነባች ፤ ለምሳሌ ፦ ሕዳሴ ግድብ የሐገሪቱ ጫፍ ላይ ፣ የግቤ ግድብ ከተጠቃሚ ገበያዎች በከፍተኛ ርቀት ላይ ፣ ወዘተ የተመረቱትን ኃይሎች ፤ ከማምረቻ ግድቦች አውጥቶ ተጠቀሚዎች ወደ እሚገኙበት ለማድረስ ፤ ርጅም ርቀት ያላቸው የኃይል ማስተላለፊያ (Transmission Lines) መገንባት ግድ ይሆናል። በአንጻሩ ኬንያ የኃይል ማመንጫዎቿን በአንድ አከባቢ ወይንም በአጭር ርቀት ላይ እንዲሆኑ በማድረግ የከፍተኛ ኃይል ተሸካሚ ኃይል ማስተላለፊያዎችን መቀነስ ችላለች። ትልቁ ጥያቄ ፦ እነ እዚኸን የኃይል ማመንጫዎች አራምባ እና ቆቦ አድርጎ እና ከነዋሪ በከፍተኛ ርቀት ላይ የመገንባት ግዴታ ነበር ወይስ የግድብ ቦታ መረጣ ችግር ነው ?የእሚለው ይሆናል። ምክንያቱም ፦ ለምሳሌ ፦ የሕዳሴ ግድብን እዚኸ ደብረ ሊባኖስ ጋር መገነባት ይቻል ነበር ስለ እሚባል ፤ ሌሎቹን ግድቦች የተሻለ ቦታ መገንባት ይቻል ነበር ወይ እና ያም መንግስት ፤ ከፍተኛ የኃይል አስተላላፊዎችን ረጅም ርቀት ለመሸፈን የእሚያወጣውን በቢልዮን ዶላር የእሚቆጠር ገንዘብ መቀነስ ይችል ነበር ? ምክንያቱም ፦ ለምሳሌ ከሕዳሴ ግድብ ኃይል ለማውጣት ፤ ኢትዮጵያ ከቻይና የ1.2 ቢልዮን ዶላር ብድር ተበድራለች።
- በእዚኸ ላይ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤ የሐገሩን ገበያ አንድ ሶስተኛ እንኳን በአግባቡ ሳያገለግል ፤ ኃይል ኤክስፖርት አደርጋለኹ በእሚል እና እንደ ዴታ ሴንተር ላሉ የከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚዎች ኃይል ለማቅረብ ከፍተኛ መጠን ያለው የኃይል አስተላላፊ መገንባቱም ፤ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ የእምታገለግለው የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ከኬንያው በግማሽ በላይ ያነሰ ቢሆንም ፤ ከፍተኛ የኃይል አስተላላፊዎቿ ርቀት በእጥፍ የእሚጨምሩ ሆነዋል።
- እንደ ገናም ፤ በመካከለኛ ማለትም 33KV/15KV ተሸካሚ የሆኑት ማሰራጫ መስመሮች ርቀት (54,300 ኪሎሜትር) እና ዝቅተኛ ወይንም ወደ እየቤት ኃይል ከእሚያስገቡ ማሰራጫ መስመሮች ማለትም 0.38KV/0.22KV መስመሮች (60, 704KM) መካከል ተቀራራቢ የሆነ ሽፋን ነው የእምናየው። ይኸም ማለት ፦ ሰብስቴሽን ከእሚባሉት ኃይል አውጥቶ ፤ በእየ ስልክ እንጨቱ ላይ ወደ እሚሰቀሉ ትራንስፎርመሮች ኃይል ለማድረስ እና ኃይሉን ደግሞ ስልክ እንጨት ላይ ከእሚተከሉ ትራንስፎርመሮች አውጥቶ ወደ ግለሰቦች ቤት ለማስገባት የተዘረጉት መስመሮች

በመላ ኢትዮጵያ ደረጃ ተቀራራቢ ርቀት የእሚሸፍኑ ሆነው ነው እምናገኛቸው። ይኸም ማለት ፦ በተተከሉ ትራንስፎርመሮች 600 ሜትር ራዲየስ ውስጥ ፤ በቂ የመግዛት አቅም ያላቸው ኢትዮጵያዊያን የሉም ወይንም ደግሞ በሐገራችን ባለው ዝቅተኛ የከተሜነት ደረጃ ምክንያት ፤ ትራንስፎርመር ባለባቸው በታዎች የእሚገኙ ነዋሪዎች ቁጥር በጣም ዝቅተኛ ነው ማለት ነው።

2. በማከፋፈያ መስመሮች እድገት እና በደንበኛ እድገት መካከል ያለው ንጽጽም ከፍተኛ ልዩነት አለው

ቀደም ብለን እንደ አልነው ፤ አኹንም ወቅታዊ ሪፖርት ማግኘት ቢያስቸግርም ፤ የ2021/2022 ወይንም በኢትዮጵያ 2014 ዓም የቀረበውን ሪፖርት መሰረት አድርገን እና እዚያ ላይ ግምት ጨምረንበት ፤ በ2025 ወይንም በ2017 ዓም በኢትዮጵያ የተደረገውን የኃይል ማከፋፈያ ጭማሪ ከደንበኛ ጭማሪ ጋር ያለውን ቁርኝት ፤ ከተመሳሳይ የኬንያ ኹኔታ ጋር ብናነጻጽረው ፤ ኬንያዎች ጥቂት የማከፋፈያ መስመር ቢጨምሩም በእየ ዓመቱ ከኢትዮጵያ በሺዎች የእሚበልጡ አዳዲስ ደንበኞች ሲጨምሩ ነው እምናየው።

መረጃዎቹን በሰንጠረዥ አስቀመጠን እናነጻጽር።

የ2014ቱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፋክትስ ኢን ብሪፍ ፤ ከ2014 (2021/2022) በፊት በነበሩት 8 ዓመታት የነበሩትን የደንበኞች እድገት በእዚኽ መልኩ ሪፖርት አድርጓል ፦

| ዓመት | አዲስ የተጨመሩ ደንበኞች |
|---|---|
| 2014/2015 (2007 ዓም) | 131,028 |
| 2015/2016 (2008 ዓም) | 180,028 |
| 2016/2017 (2009 ዓም) | 215, 442 |
| 2017/2018 (2010 ዓም) | 231,781 |
| 2018/2019 (2011 ዓም) | 195,264 |
| 2019/2020 (2012 ዓም) | 168,751 |
| 2020/2021 (2013 ዓም) | 387,864 |
| 2021/2022 (2014 ዓም) | 364,764 |

ለእኔ በግሌ መጀመሪያ ትኩረቴን የሳበው ፤ በ2022 ወይንም በኢትዮጵያ 2014 ዓም ሪፖርቱ ከመቋረጡ በፊት ፤ አዳዲስ የእሚጨመሩ ደንበኞች ከነበረው ልማድ የ150 ሺ በላይ ባሳየ መልኩ ጭማሪ በማሳየት በዓመት የአዲስ ደንበኞች ቁጥር ፤ 387 ሺ እና 364 ሺ መድረሱ ነው።

ይኽ ከፍተኛ የደንበኛ እድገት ፤ ምን አልባት ፦ የብልጽግናው በስንዴ ምርት ከአፍሪካ አንደኛ ሆንን ዓይነት ፋሽን ይሆን ወይንስ በእውነትም የደንበኛ ቁጥር እድገት በእዚኽ ደረጃ ዓመታዊ ጭማሪ እያሳየ ነው ?

ሆኖም ፦ ይኽ ከጥርጣሬ ስለ እማያልፍ ፤ የቀረበውን መረጃ እንደ ተዓማኒ መረጃ ወስደን ፤ ከነበረውን ልምድ ተነስተን ፤ የ2025 ወይንም የ2017 ዓም የአዲስ ደንበኞች ቁጥር ስንት ሊሆን ይችላል ብለን ከገመትን ፤ ቁጥሩ ከ376 ሺ እስከ 565 ሺ ሊሆን ይችላል።

ፍትኃዊ ለመሆን መካከለኛ ቁጥር እንውሰድ ካልን ፤ የ2025 ወይንም የ2017 ዓም አዲስ ደንበኞች ቁጥር ወደ 465 ሺ ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል።

ስለ እዚኽ ፦ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በ2017 ዓም በጠቅላላው 465 ሺ አዲስ ደንበኞች ጨምሯል ካልን ፤ ይኽን ያክል ደንበኛ በጨመረበት ወቅት ፤ ፈለገ ብርኃን በእሚለው መጽሔቱ ላይ ባወጣው ሪፖርቱ መሠረት ፤ በእዚያ ዓመት በ9 ወር ብቻ በጠቅላላው አዲስ የ9, 587 ኪሎሜትር የማከፋፈያ መስመሮች ከጨመረ በኋላ ነው፦

> *"የኢትየጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ባለፉት ዘጠኝ ወራት አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር ባከናወነው ስራ 9 ሺህ 588 ኪሎ ሜትር አዳዲስ የዲስትሪቢዩሽን መስመሮች ማስፋፊያ/ዝርጋታ አከናውኗል። ከዚህ ውስጥ 3 ሺህ 518 ኪ.ሜ የመካከለኛ መስመር፣ 6 ሺህ 69 ኪ.ሜ ደግሞ የዝቅተኛ መስመር ዝርጋታ የተከናወነበት ነው። በተጨማሪም የኃይል አቅርቦቱን የሚያሳድጉ 3 ሺህ 683 የተለያዩ ዓቅም ያላቸው አዲስ የዲስትሪቡዩሽን ትራንስፎርመሮች ተከላ ተከናውኗል።"*

በአንጻሩ የኬንያው KPLC በ2025 ባወጣው ዓመታዊ ኦዲት የተደረገ ሪፖርቱ ላይ እንደ አስቀመጠው ፦

> *"አዲስ የተጨመሩት ደንበኞች ፦*
>
> *i. 163, 092 በእርዳታ ሰጪዎች እና በመንግስት ድጎማ በአብዛኛው በገጠር እና ደካማ አከባቢ ያሉ ኤሌክትሪክ ያገኙ ደንበኞች።*
>
> *j. 238, 757 በእራሳቸው ከፍለው ኃይል ያገኙ።*
>
> *"The composition of the new customers connections is as follows:-*
>
> *i. 163,092 Last mile customers*
>
> *ii. 238,757 paid up customers"*

ይኽን በጠቅላላው ስትደምሩት 401,849 ሺ ይመጣል። የኬንያው ኤሌክትሪክ አቅራቢ ፤ ይኽን ያኽል ደንበኛ ሲጨምር ግን ፤ አይደለም 10 ሺ ኪሎሜትር የእሚሸፍን የማከፋፈያ አዲስ መስመር ሊገነባ ፤ 1 ሺ ኪሎሜትር የእሚሸፍን አዲስ የማከፋፈያ መስመርም አልገነባም።

ይኽም ሊሆን የእሚችለው ፦

- በሐገራችን ኢትዮጵያ ፤ ከሰሐራ በታች ካሉ ሐገራት አንጻር እንኳን ፤ በጣም ዝቅተኛ ከተሜነት ስለ አለ ፤ ዜጎች በጣም ተዘርዝረው ስለ እሚኖሩ ፤ ከፍተኛ ርቀት ተሸፍኖ ኃይል ከተዳረሰ በኋላ

የተጠቃሚ ሠፋሪው ቁጥር ትንሽ ስለ ሆነ ፤ ማስተላለፊያ መስመሩ ከማከፋፈያ መስመሩ ጋር ተቀራራቢ ርዝማኔ እንዲኖረው አድርጓል።

- ወይንም ኃይል በደረሰበት ቦታ ኹሉ በቂ ሠፋሪ ቢኖርም ፤ የሕዝቡ የመግዛት አቅም በጣም ዝቅተኛ ስለ ሆነ ፤ ደንበኛ ማግኘት አልተቻለም።

ምክንያቱ ምንም ሆነ ምንም ግን ፤ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ማመንጨት እንጂ ማከፋፈል ፤ በበቂ ኹኔታ ትኩረት ተሰጥቶት የተሠራ ነገር እንደ አልሆነ እና ይኽም ከፍተኛ የአስተዳደር እና የኢንቨስትመንት ክፍተት ለመሆኑ ግን ምንም ጥያቄ የለውም።

3. ኢትዮጵያ ከኬንያ በእጥፍ የበለጠ ኃይል ብታመነጭም የእምታገለግለው ደንበኛ ግን በግማሽ ያነሰ ነው

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በቆዳ ስፋቷም ሆነ በሕዝብ ቁጥር ብዛቷ የኬንያን 2 እጥፍ መሆኗ ግልጽ ቢሆንም ፤ ከእምናመነጨው ጠቅላላ ኃይል አንጻር የእምንፈጥረው ተጠቃሚ (Total Customers) አንጻር ፤ የኬንያ ግማሽ የያዝን መሆናችን ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ኃይል ማመንጨት እንጂ ኃይልን ለተጠቃሚ ማድረስ ወይንም የሕዝብን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የእቅዳችን አካል አይመስልም ለእሚለው ጉዳይ መቅረብ የእሚችል ሌላው ማሳያ ነው።

ለምሳሌ ፦ የኬንያን ጠቅላላ ሐገራዊ ኃይል የማመንጨት አቅም ብናይ 3, 307 ሜጋ ዋት ሆኖ እናገኘዋለን። ሆኖም ኬንያ በሐገር ውስጥ የእምታመረው ኤሌክትሪሲቲ ስለ እማይበቃት ፤ ተጨማሪ 11% የኃይል መጠን ከኢትዮጵያ ፣ ከዩጋንዳ እና ከታንዛንያ ገዝታ ታስገባለች ፤ በመሆኑም በ2025 የኬንያ ጠቅላላ የኃይል አቅርቦት ወይንም ፍጆታ 3,307 ሜጋ ዋት ይሆናል።

በአንፃሩ የእሚያስፈልጋትን ኃይል በሙሉ ራሷ የእምታመርተው ኢትዮጵያ ደግሞ ፤ ዓመታዊ የኃይል ምርት አቅሟ 8, 115.84 ሜጋ ዋት ፤ ይኽም ከኬንያው ጠቅላላ የኃይል ምርት አቅም እጥፉ ሆኖ እናገኘዋለን።

ሆኖም ደጋግሜ እንደ አልኹት ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ ዓመታዊ ሪፖርት በጥሩ ኹኔታ አዘጋጅቶ ተደራሽ በሆነ መልኩ ለሕዝብ የማቅረብ ችግር ያለበት በመሆኑ ፤ ቀጥታ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ወይንም ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የጠቅላላ ደንበኞችን ቁጥር ማግኘት ቢያስቸግርም ፤ ብርሜትሪክስ የእሚል ሐገራዊ የዜና ምንጭ ፤ በኦገስት 2025 ባወጣው በእዚኽ [EEU Delivers Nearly Full Electricity Supply to 5.2 Million Customers, Posts 63 Billion Birr Revenue - Birr Metrics] ዜና መሠረት ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጠቅላላ ደንበኞች 5.2 ሚልዮን እንደ ሆኑ ይነግረናል፦

> *"የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎ ከ5.2 ሚልዮን በላይ ደንበኞችን አገልግሏል ፤ 81.4% በድህረ ክፍያ ፣ 17.4 በቅድመ ክፍያ እና 1% የእሚሆኑትን ደግሞ በስማርት ሜትሮች።"*
>
> *"The utility served more than 5.2 million customers, including 81.4 percent postpaid, 17.4 percent prepaid, and 1 percent on smart meters."*

በአንፃሩ የተሻለ የሪፖርቲንግ እና የመረጃ ማጋራት ልማድ ያለው ፤ የኢትዮጵያው ኤሌክትሪክ አገልግሎት አቻ የሆነው የኬንያው KPLC በዓመታዊ ሪፖርቱ ላይ ፤ በ2025 ባለቀው የበጀት ዓመት ወደ 401 ሺ በላይ አዲስ ደንበኞች በመጨመር ፤ የጠቅላላ ደንበኞቹን ቁጥር 10 ሚልዮን እንደ አደረሰ ይነገረናል ፦

> *"በዓመቱ በጠቅላላው አዲስ የ203 ጊጋዋት አወር መጠን ያለው ተጨማሪ ሽያጭ ማድረግ ያስቻሉን ፤ የ401, 848 አዲስ ደንበኞችን በመጨመር ፤ ጠቅላላ የደንበኞቻችንን ቁጥር ከ10 ሚልዮን በላይ ማድረግ ችለናል። በአዲስ ደንበኞች ምክንያት ከተመዘገበው የኃይል ሽያጭ ውስጥ ፤ ከግማሽ በላይ የሆነው የተሸጠው ፤ ለኢንደስትሪ ደንበኞች ነው።"*
>
> *"We crossed the 10 million customer mark with 401 ,848 new connections, which contributed approximately 203 GWh in new sales, With Industrial customers accounting for more than half of the incremental unit sales."*

ከእዚኽ ንፅፅራዊ መረጃ ልትመለከቱ እንደ ምትችሉት ፤ ምንም እንኳን ኬንያዊያን ከኢትዮጵያ ፣ ከዩጋንዳ እንዲኹም ከታንዛንያ ወደ 11% የእሚሆነውን የኃይል አቅራቦት አስገብተውም ፤ ጠቅላላ ሐገራዊ ኃይል የማምረት አቅማቸው ፤ 3,307 ሜጋ ዋት ፤ ስለ እዚኽም ፦ የኢትዮጵያ የተመሳሳይ ወቅት ኃይል የማምረት አቅም ከግማሽ በታች ቢሆንም ፤ የኢትዮጵያን ከፍተኛ ክፍተት በእሚያሳይ መንገድ ፤ የጠቅላላ ደንበኛ ቁጥራቸው ፤ የኢትዮጵያን እጥፍ በላይ ነው።

ኬንያ ከኢትዮጵያ ግማሽ በሆነ ኃይል የማመንጨት አቅም (የሐገር ውስጥ እና ከውጭ ኢምፖርት የተደረገ) ፤ የኢትዮጵያን እጥፍ ተጠቃሚ ማገልገል ችላለች።

ይኽም ፦ በኢትዮጵያ ኃይል ማመንጨት እንጂ የሕዝብን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ወይንም ኃይል ማከፋፈል የእቅድ አካል አይመስልም የእሚለውን በደንብ ያሳያል።

ይኽም ከእላይ ከተዘረዘሩት ሌሎች ምክንያቶች ጋር ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በእዚኽ መልኩ በእየ ዓመቱ በቢልዮኖች ፤ ቢያንስ ለባለፉት 7 እና 8 ዓመታት ሲከስር የነበረው ፤ የመግዛት አቅሙ የተዳከመውን ሕብረተሰብ ለመደጎም ሲል ይኽን ዓይነት ትልቅ ክስረት የእሚከስረው የእሚለውን ሙግት ባዶ ያደርገዋል።

አይደለም ፦ ለሐገር ውስጥ ገበያ ፤ ለኤክስፖርት እና እንደ ቢትኮይን ላሉ የካፒታሊዝም ፕሮጀክቶች ከ33% በላይ የእሚሆነውን ኃይሉን ሸጦ እንኳን ፤ ግማሽ የማምረት አቅሙን መጠቀም ያልቻለ ኃይል አመንጪ ፤ ስለ እዚኽ ከግማሽ በላይ የእሚሆነው የማመንጨት አቅሙ ፤ የእሚባክንበት ኢንቨስትመንት የእሚያደርግ ተቋም ፤ ለእዚያውም ያን የባከነ ኢንቨስትመንት የእሚያመጣው ከድኃው ኢትዮጵያዊ ጉሮሮ ላይ ፦ ርካሽ ብድር በመውሰድ ፣ የጡረታ ገንዘብ አግቶ በማያዝ ፣ የመንግስት ድጎማ በመቀበል ፣ ወዘተ የሆነ ተቋም ፤ የእሚከስረው በእራሱ እንዝህላልነት እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብን ስለ እሚደጉም አይደለም።

እንዲያውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ፤ ይኽኽን የእንከፍ ከነድፍድፉ ተሸካሚ ተቋም የተሸከመው።

### 4.2.5 የተገነቡ እና በሥራ ላይ ያልዋሉ ማመንጫዎች

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (Ethiopian Electric Power) በእየዓመቱ በእሚያሳትመው እና ኃይል የማመንጨት አቅሙን በእሚገልጽበት ቦታ ላይ ፤ በ2017 በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ፤ በማንኛውም ሰዓት ወደ ሥራ ገብተው ፤ ኃይል ማመንጨት የእሚችሉ ማመንጫዎቹን ፤ ከእዚኽ በታች ባለው መልክ ደርድሯቸዋል፡-

| 2017 (2024/2025) ላይ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ፤ በሥራ ላይ ያሉ ማመንጫዎች በአንድ ሰዓት ውስጥ ማመንጨት የእሚችሉት ኃይል በሜጋ ዋት (Mega Watt) | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ኃይል ማመንጫ | ውኃ ግድብ | ጂኦተርማል | ንፋስ | ቆሻሻ ማንደድ | ጠቅላላ | በሥራ ላይ |
| 1. | ቆቃ | 43.2 | | | | | 1960 |
| 2. | ጥስ አባይ 1 | 11.4 | | | | | 1964 |
| 3. | ጢስ አባይ 2 | 73 | | | | | 2001 |
| 4. | አዋሽ 2 | 32 | | | | | 1966 |
| 5. | አዋሽ 3 | 32 | | | | | 1971 |
| 6. | ፊንጫ | 134 | | | | | 1973/2003 |
| 7. | መልካ ዋከና | 153 | | | | | 1988 |
| 8. | ግልገል ግቤ 1 | 184 | | | | | 2004 |
| 9. | ግልገል ግቤ 2 | 420 | | | | | 2010 |
| 1 | ግልገል ግቤ 3 | 1, 870 | | | | | 2015 |
| 1 | ተከዜ | 300 | | | | | 2009 |
| 1 | በለስ | 460 | | | | | 2010 |
| 1 | አመርቲ ነሺ | 97 | | | | | 2011 |
| 1 | ገናሌ ዳዋ | 254 | | | | | 2020 |
| 1 | ሕዳሴ | 3, 550 | | | | | 2022/2024 |
| 1 | አሉቶ ላንጋኖ | | 7.3 | | | | 1999 |
| 1 | አሼጎዳ | | | 120 | | | 2012 |
| 1 | አዳማ 1 | | | 51 | | | 2012 |
| 1 | አዳማ 2 | | | 153 | | | 2014 |
| 2 | አይሻ ንፋስ 2 | | | 80 | | | 2022 |
| 2 | አሰላ ንፋስ | | | 65.84 | | | - |
| 2 | ረጲ ቆሻሻ | | | | 25 | | 2019 |
| | ድምር | 7,613.60 | 7.3 | 469.84 | 25 | 8, 115.84 | |
| | ተዋፅዖ | 93.81 % | 0.09% | 5.79% | 0.31% | 100% | |

ይኽም ማለት እነ እዚኽ ማመንጫዎች ፤ በሙሉ ኃይላቸው ከሠሩ ፤ በዓመት ውስጥ በእሚገኙት በእያንዳንዳቸው 8, 760 ሰዓታት ውስጥ በእየ ሰዓቱ 8,115.84 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ይችላሉ።

ሆኖም በኢትዮጵያ ልማታዊነት በእሚል እሳቤ በድኃ እንደጉማለን ሽፋን ከፍተኛ የሕዝብ እና የሐገር ኃብት ያለአግባብ የማባከኑ አባዜ ፤ ከእሚታይበት መንገድ አንዱ ፤ የኃይል ማመንጫ ህንፀቶች (Edifices) ፤ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ተደርጎ ከተገነቡ በኋላ በሙሉ አቅማቸው ኃይል እንደ አያመርቱ ፤ በጥቃቅን እንደ መለዋወጫ እጥረት ዓይነት ምክንያቶች ፤ በሙሉ አቅማቸው ኃይል ወደ ማምረት የእማይገቡ መሆናቸው ነው[5]።

በእዚኽ ረገድ ፤ የሕዳሴውን ግድብ እና የረጂ ማመንጫዎች ሙሉ አቅማቸው ሲጀምርም በሥራ ላይ እንደ አልዋለ ነው የእሚታየው።

### *4.2.5.1 ሕዳሴው ፡-*

የሕዳሴው ግድብ ፤ እንደ ውኃ እና ኢነርጂ ምኒስተር ባሉ እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልም ሆነ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የበላይ ጠባቂ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መረጃ መሠረት ፤ ጠቅላላ የማመንጨት አቅሙ ፡- 6,450 ሜጋ ዋት ነው።

ይኽም የሕዳሴው ግድብ የማመንጨት አቅም ፤ የኬንያውን ልምድ ምስክር ማድረግ ከተቻለ ፤ ብቻውን ሌላ ምንም የኃይል ማመንጫ እገዛ ሳያስፈልገው ፤ አኹን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ገበያ ፤ በእጥፍ ማገልገል የእሚችል አቅም ነው።

ሆኖም እላይ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዓመታዊ መጽሔት በተገኘ መረጃ መሠረት ፤ በ2017 ዓም በሕዳሴ ግድብ ስም የተጫነ የማመንጨት አቅም (ምን አልባትም ወደ ሥራ የገባ ተርባይን መጠን i.e. Installed capacity) 3, 350 ሜጋ ዋት ማመንጨት የእሚችል ብቻ ነው የነበረው።

ይኽም ማለት ፤ በመጀመሪያው ዋጋው እንኳን ብንኼድ 5 ቢልዮን ዶላር ወጥቶ የተገነባ እና 1 ቢልዮን ዶላር የኃይል ማስተላለፊያ ያሰወጣ ግድብ ፤ በአጠቃላይ ካስከፈለው 6 ቢልዮን ዶላር ውስጥ 3.3 ቢልዮን ዶላሩን ብቻ ነው ወደ ሥራ እያሰማራ ያለው።

ይኽም ማለት ፡- 2.7 ቢልዮን ዶላር ወይንም በአሁኑ ምንዛሪ ወደ 437 ቢልዮን የእሚሆን ብር የወጣበት ኢንቨስትመንት ፤ ለማንም ምንም ሳይጠቅም ፤ 29% ሕዝብ ብቻ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ባለባት ሐገር ተቆልፎ ተቀምጧል ማለት ነው።

በእርግጥ በአንድ ዓመት ብቻ 122 ቢልዮን ብር ለእሚከስር ተቋም ፤ ቁጭ ብሎ የእሚዝግ 437 ቢልዮን ብር ምንድ ነው ሊባል ይችል ይሆናል ፤ እንደ ሐገር በመኃይምነት ምክንያት ፤ **የድኃ እጅግ አባካኝ** መሆናችንን ግን ምንም ጥያቄ የለውም።

---

[5] ምን አልባትም ፤ የተመረተውን መሸጥ ስላቃተ ፤ መለዋወጫችን ሰበብ አድርጎ ፤ ማመንጫዎችን የመገደብ ነገር ሊኖርም ይችላል።

### *4.2.5.2 ረጺ ፡-*

የረጺው ከቆሻሻ ኃይል የማመንጨት ፕሮጀክት ፤ ምንም እንኳን ከግል ባለኃብቶች ጋር በተደረገ ትብብር የተገነባ ቢሆንም ፤ በአንድም በሌላ መንገድ በመንግሥት ፖሊሲ ምክንያት ከሕዝባዊ ኢንቨስትመንት በምንም ተለይቶ አይታይም።

እናም እንደ እሚመስለው ፤ መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ ሆኖበት ፤ እራሱን ብልጽግና ያለው ጉድ ወደ ስልጣን ሲመጣ ፤ ዘመናዊ እና አዲስ አሠራር አመጣለኹ በእሚል ፤ ለአከባቢ ጥበቃ የእሚመች የኃይል ማመንጫ በእሚል ዓይነት እሳቤ ፤ የአዲስ አበባን ቆሻሻ በማቃጠል ፤ በአንድ በኩል የቆሻሻ ችግር ሲፈታ ፤ በአንድ ድንጋይ ኹለት ወፍ ብሎ ፤ ቆሻሻው ሲቃጠል በእሚፈጠር እንፋሎት ኤሌክትሪክ ግሪዱ ውስጥ ተጨማሪ 25 ሜጋ ዋት ኤሌክትሪክ ኃይል ለማስገባት ነበር።

ችግሩ ግን ፤ መንግሥትን ኢንቨስተር ማድረግ ፤ አንድ የውተት ላምን አሰልጥኖ የጦር ፈረስ የማድረግ ያኽል ከባድ በመሆኑ ፤ አዲስ አበባ ቆሻሻን ደረቅ እና በስባሽ ቆሻሻ የእሚል ክፍፍል አድርጋ ቆሻሻ የእምትሰበስብ ከተማ አለመሆኗን ከግምት ያላስገባ ፕሮጀክት ነበር።

እንደ እሚወጡት መረጃዎች ከሆነ ፤ ቆሻሻው በአግባቡ ተለይቶ ስለ እማይመጣ ፤ አንድ አንዴ ከደረቁ ጋር እርጥቡ ቆሻሻ እየተካተተ ማሽኑን እያበላሸው ነው።

ይኽም ማለት ፡- ኃይል ማመንጫው ፤ ከወጣበት ኢንቨትመንት አንጻር ፤ ትርፋማ ሆኖ እንዲቀጥል ፡- የተጣራ በቂ ቆሻሻ ማግኘት እና በእርጥብ ቆሻሻ ምክንያት ቶሎ ቶሎ መበላሸት የለበትም።

በእዚያ ላይ ማሽኑ ሲበላሽ ለማሠራት እና መለዋወጫ ከውጭ ለማስገባት የዶላር ችግር በተደጋጋሚ ይገጥመዋል ነው እሚባለው።

ከእዚኽም የተነሳ ፤ የጢስ አባይን እጥፍ ወይንም አዋሽ 1 እና 2 ከእሚባሉት የውኃ ግድቦች ጋር ተመጣጣኝ ኃይል ማመንጨት የእሚችል ማመንጫ ፤ ከሞላ ጎደል በሥራ ላይ ያዋለው ማመንጫ ፤ የአቅሙን 50% ብቻ ነው።

ምን አልባትም ፡- ዋናው ኃይል ማመንጫ ፤ ያመነጨውን እሚሸጥበት ባጣበት ኹኔታ ፤ ከግል ባለኃብት ጋር ሠርቶ የእሚያመጣን ኃይል አለመፈለግም የራሱን ይኽን የረጺ ኢንቨስትመንት ለማባከን የራሱን ስውር ሚና ሊጫወት ይችላል።

ምን አልባት ፤ ቆሻሻው መቃጠሉ ካልቀረ ፤ የ12.5 ሜጋ ዋት ኤሌክትሪስቲ ማግኘቱ ድል ነው ሊባል ይችላል ፤ ሆኖም ፡-

- አንድ ኢንቨስትመንት ሲደረግ ፤ የተጠበቀው ምርት በ50% ቀንሶ ፤ በትርፋማነት ሊቀጥል የእሚችልበት እድል በጣም ጠባብ በመሆኑ ፤ ለመቀየር ረጅም ግዜ የእሚወስደው የሐገራችን የቆሻሻ አወጋገድ ካልተቀየረ ፤ ተቋሙ የወጣበትን ኢንቨስትመንት አውድሞ እራሱም ከስሮ የእሚጠፋ መሆኑ ብዙም የእማያጠያይቅ ነው።

➢ ኢንቨስት ከተደረገበት እና ከሚጠበቅበት ምርታማነት አንጻር ፤ 50% ብቻ ምላሽ መስጠቱም ፤ 50% የሚሆነው ኢንቨስትመንት እንዲኹ እየባከነ መሆኑ እርግጠኛ በመሆኑ ፤ ግማሽ ብክነት መኖሩ ምንም ጥያቄ የለውም።

ተቋሙ ፤ ማለትም ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የመረጃ ሞኖፖሊ ስለ አለው ፤ የገለልተኛ አካል ምርመራ ስለ ሌለ ማወቅ ባይቻልም ፤ ምን አልባትም ፤ በርካታ ብዙ ገንዘብ የፈሰሰባቸው እንደ አዋሽ ፣ ጢስ አባይ ፣ ወዘተ ያሉ ከእላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ያሉ ግድቦች ፤ ልክ እንደ ረጲው እና እንደ ህዳሴው ፤ የአቅማቸውን ዓይነት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ቢደረግባቸው ፤ በተመሳሳይ ምክንያቶች ፤ ማምረት የሚችሉትን ኃይል እንደ አያመነጩ እየተደረጉም ሊሆን ይችላል።

በአጠቃላይ :- ኤክስፖርት የተደረገውን ፣ ለዴታ ሴንተሮች የተሸጠውን ፣ ለሐገር ውስጥ ከፍተኛ ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ኢንደስትሪ የተሸጠውን ፣ ለሐገር ነጋዴ እና ለነዋሪ ሕዝብ የተሸጠውን ጨምሮ ፤ አይደለም በመደበኛ ግዜ ፤ በአንዳች ምክንያት በአንድ ወቅት የሚፈጠር ከፍተኛ የኃይል ጥየቃ (Peak Demand) እንኳን ብናይ ፤ የተገነቡ ኃይል ማመንጫዎች ወይ ኃይል አምርተው ኃይሉ ገዢ አጥቶ እየባከነ ነው ወይንም ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸው የኃይል ማመንጫ ህንጻቾች ፤ ማመንጨት የሚችሉትን ያኽል ኃይል እሚገዛ ደንበኛ ስለ ሌለ ፤ የአቅማቸውን ያኽል ኃይል እንደ አያመነጩ እየተደረጉ ነው።

ለማስረጃ ያኽል ፤ በኢትዮጵያ 2017 ዓም ወቅታዊ ከፍተኛ ጥየቃ (Peak Demand) በሚል በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የቀረበን መረጃ እንመልከት ፡-

| ዓመተ ምህረት | ከፍተኛ የኃይል ጥየቃ (Peak Demand) |
|---|---|
| 2013 | 2,792.95 MW |
| 2014 | 2,781.27 MW |
| 2015 | 3,255.20 MW |
| 2016 | 3,714.15 MW |
| 2017 | 4,916.71 MW |

እዚኽ ጋር ኹለት ነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን ፡-

አንደኛ ፡- በ2017 ከፍተኛ የሚባለው የኃይል ጥየቃ በተደረገበት ዓመት ፤ የከፍተኛ ጥየቃው (Peak Demand) 4, 916.71 የተተከለው የማምረት አቅም (Installed Capacity) 60% ወይንም 8, 115.84 ሜጋ ዋት ሆኖ ነው የምናገኘው።

በአንጻሩ ፤ በKENGEN ወይንም በኬንያው ኃይል አመንጪ ኩባንያ የ2025 ዓመታዊ ሪፖርት መሠረት ፤ በኬንያ የዓመቱ ድንገታዊ ከፍተኛ ጥየቃ (Peak Deman) 2,392 MW ሆኖ ስለ ምናገኝ ፡-

*"በዓመቱ ከፍተኛ ጥየቃ ከባለፈው ዓመት በ9.9% በማደግ 2,392 ሜጋ ዋት ደርሷል ፤ ይኽም ኬንጀን በኬንያ ኢኮኖሚያዊ ሽግግር ውስጥ ያለውን ጉልህ ሚና የእሚያሳይ ነው።"*

*"National peak demand has jumped by 9.9% to 2,392 MW from the previous year, reinforcing KenGen's pivotal role in ensuring reliable and sustainable electricity supply to power Kenya's economic transformation."*

በእዚኽ ሪፖርት ላይ ከቀረበው የኬንጀን ኃይል የማምረት አቅም መረጃ ተነስተን ፤ ጠቅላላ የዓመቱ የኬንያ የማምረት አቅም (ኢምፖርት የእሚደረገውን 11% ጨምሮ) 3,307 ሜጋ ዋት ነው ብለን ማስላት ስለ እምንችል ፤ በኬንያ ከፍተኛ ጥያቃ ለተጨነ የማምረት አቅም 72% መሆኑን ዕናያለን።

ይኽም ፤ ኬንያዊያን ቢያንስ ከኢንቨስትመንታቸውን ከኢትዮጵያ 12% ጥቅም እንደ እሚያገኙ ያሳየናል።

ኹለተኛ ፡- ከእዚኽ በታች ባለው ሠንጠረዥ እና ግራፍ ፤ ዓመታዊ የከፍተኛ የኃይል ጥየቃ (Peak Demand) ዕድገትን ስንመለከት፡-

| ዓመተ ምህረት | ከፍተኛ የኃይል ጥየቃ (Peak Demand) | ዓመታዊ የከፍተኛ ጥየቃ ዕድገት በፐርሰንት | ዕድገቱ በሜጋ ዋት |
|---|---|---|---|
| 2013 | 2,792.95 MW | | |
| 2014 | 2,781.27 MW | (-) 0.4% | (-) 11.68 MW |
| 2015 | 3,255.20 MW | (+) 17.04% | (+) 473.93 MW |
| 2016 | 3,714.15 MW | (+) 14.09% | (+) 458.95 MW |
| 2017 | 4,916.71 MW | (+) 32.38% | (+) 1,202.56 MW |




ከ2014 ዓም እስከ 2016 ዓም ፤ የ17% እና የ14% ፣ ከፍተኛ የኃይል ጥየቃ ዕድገት ስናይ ፤ በ2017 ዓም ደግሞ የከፍተኛ የኃይል ጥየቃ እድገቱ ከእጥፍ በላይ ጨምሮ የ32% ዕድገት ወይንም በቁጥር 1,202.56 ሜጋ ዋት ጭማሪ አሳይቶ እናያለን።

ይኸን ፤ በተለይ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (ምንም እንኳን መረጃው እስከ 2014 ዓም ድረስ ብቻ ቢሆንም) ዓመታዊ የደንበኞች እድገት ብሎ ካስቀመጠው መረጃ ጋር አዛምደን እና እርሱንም መሠረት አድርገን የቀጣይ ዓመታት ግምታዊ የደንበኞች ዕድገት ብንሰራ ፤ የከፍተኛ ጥየቃው ምንጭ ፤ የመደበኛ ደንበኛ መስፋፋት ውጤት ከመሆን ይልቅ ፤ የከፍተኛ ጥየቃ ዕድገት ምንጩ ፤ ከኢንደስትሪዎች እንኳን ሳይሆን ፤ ምን አልባት ፤ ከኤክስፖርት እና ከዴታ ሴንተር የመጣ ሊሆን እንደ እሚችል እንድንገምት ያደርገናል።

ለማንኛውም ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከ2007 ዓም እስከ 2014 ዓም በእሚያቀርበው እና እርሱ ላይ ተመርኩዞን ደግሞ ከ2015 ዓም እስከ  ከ2017 ዓም ሊኖር የእሚችለውን የደንበኛ ዕድገት እንመልከት ፡-

| **ዓመተ ምህረት** | **ዓመታዊ የደንበኛ እድገት** |
|---|---|
| **2007** | 131,028 |
| **2008** | 180,028 |
| **2009** | 215,442 |
| **2010** | 231,781 |
| **2011** | 195,264 |
| **2012** | 168,751 |
| **2013** | 387,864 |
| **2014** | **364,764**[6] |
| **2015*** | በግምት 234,365 (avg growth) |
| **2016*** | በግምት 234,365 |
| **2017*** | በግምት 234,365 |

ይኽ ኹለት ነገር ይነግረናል ፡-

1ኛ. ለየት ያለ የደንበኛ እድገት አለመኖሩን እና ይኽም የከፍተኛ ኃይል ጥየቃው (Peak Demand) ምንጩ ከተለየ የደንበኛ እድገት ሊሆን አይችልም።

2ኛ. ከእላይ የኬንያው KENGEN ባቀረበው መረጃ መሠረት ፤ የከፍተኛ ኃይል ጥየቃ ዕድገቱ በ2025 (በኢትዮጵያ 2017) በ9% ነው ያደገው ሲል ፤ በእዚያው ዓመት KPLC የነበረኝ የደንበኛ ዕድገት ከ401 ሺ በላይ ብሎ ከማለቱ ጋር እና በእዚያ ዓመት በአዲስ ደንበኛ እድገት ምክንያት ከተፈጠረው ጠቅላላ አዲስ የኃይል ሽያጭ ከግማሽ በላዩ ለኢንደስትሪ በተደረገ ሽያጭ ነው ብሎ ስለ አለ ፤ ከግማሽ በላይ ለኢንደስትሪ ሽጦ እንኳን ፤ የከፍተኛ ኃይል ጥየቃው (Its peak demand growth) ዕድገት እንኳን በ9% ብቻ ነው ያደገው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የእሚባሉት ፤ እንደ ሲምንቶ ፋብሪካ ፣ የስኳር ፋብሪካ ፣ ወዘተ ያሉ ትላልቅ ኢንደስትሪዎችን እንኳን ጨምሮ ፤ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሳይሆን በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

[6] ከእዚኽ ማለትም ከ2014 ዓም በኋላ ያለው የደንበኛ ዕድገት ፤ ከ2007 እስከ 2014 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የነበረኝ የደንበኛ ዕድገት ነው በእሚል ፋክትስ ኢን ብሪፍ በእሚለው መጽሔቱ ላይ ያቀረበውን መሰረት አድርጎ ፤ ኮፓይለት ( CoPilot) በእሚባለው ኤአይ የተደረገ ግምታዊ የደንበኛ ዕድገት ነው።

የእሚገለገሉ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ኢንደስትሪዎች ጨምረው ፤ ጠቅላላ ለኢንደስትሪዎች የእሚሸጠው ኃይል ከእሚመረተው ኃይል 6% ብቻ በመሆኑ ፤ በኢትዮጵያ በ2017 እስከ 32% ወይንም በቁጥር የኬንያን ጠቅላላ የኃይል አቅም ሲሶ የእሚሆን እስከ 1,200 ሜጋ ዋት የእሚጠጋ እድገት ፤ ከኢንደስትሪ ወይንም ከደንበኛ ዕድገት ካልመጣ ፤ የመጣው ከኤክስፖርት እና ለዴታ ሴንተሮች ከተደረገ ሽያጭ ነው ማለት ነው።

ይኸ ማለት ደግሞ ፤ በተሳሳተ ፖሊሲ እየተመራን ፤ ማከፋፈልን ባግባቡ ከግምት ሳናስገባ ፤ ኃይል ማመንጨቱ ላይ ስለ አተኮርን ፤ የገነባነውን ኃይል የማምረት አቅም 60% ብቻ እየተጠቀምን እንኳን ፤ የእምናመርተውን ኃይል ሚገዛን ስለ አጣን ፤ የጥየቃ ጫናው እድገት በዋናነት የእሚመጣው ፤ ከኤክስፖርት እና እንደ ዴታ ሴንተር ላሉ መስኮች ከእሚደረግ ሽያጭ እንጂ በኢትዮጵያ ኢንደስትሪዎችን ጨምሮ ከነዋሪዎች ከእሚመጣ ጥየቃ እንደ አልሆነ ያሳየናል።

## 4.2.6 ኮይሻ - በልማታዊነት ውስጥ ብክነት ስረዓታዊ እንጂ አጋጣሚ አለመሆኑ ሠርቶ ማሳያ

ልማታዊነት እራሱን ከእቅዱ ወይንም ከመልካም ምኞት ማሳካቱ አንጻር እንጂ ከአሠራሩ እና ውጤቱ አንጻር ስለ እማይገመግም ፤ ወይንም እራሱን ከውጤት አንጻር ከገመገመ ገበያ መር ስለ እሚሆን ፤ ብክነት በልማታዊ መንግሥታት ውስጥ የሙስና እና የአፈጻጸም ድካም ውጤት ሳይሆን ስረዓታዊ የሆነ እና በአፈጻጸም ብቃት መሻሻል ወይንም በጸረ ሙስና ትግል የእሚሸነፍ ወይንም የእሚፈታ ችግር አይደለም።

ማንም ጤናማ የሆነ ሰው ፦

- አንድ ድኃ እና የኤሌክትሪክ ተደራሽነት (ከመደበኛው ግሪድ) 29% የሆነበት ሐገር እና ለድኃ እሠራለኹ የእሚል መንግሥት ያለበት ሐገር ፤ በብዙ ብድር እና የሕዝብ ኃብት ፤ በከፍተኛ ወጪ ከገነባቻቸው የኃይል ማመንጫዎች የእምታመነጨውን ኃይል ከ33% በላዩን ለውጭ ሐገራት እየሸጠች ፥
- ከአላት ጠቅላላ የማመንጨት አቅም 41% ብቻ በአማካኝ በዓመት እየተጠቀመች ፥
- በአንድም በሌላ ምክንያት እየተጠቀመችበት ያልሆነ ነገር ግን ልትጠቀምበት የእምትችለው በሰዓት ወደ 300 ሜጋ ዋት ማመንጨት የእሚችል ማመንጫ እያላት ፥
- በሐገሪቱ የዶላር ችግር ከአቅም በላይ ሆኖ ፤ የሐገርን ኢንደስትሪላይዜሽን በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳ ፥
- ሐገር በጠቅላላው ፤ በዓለም ላይ ካሉ ከፍተኛ የዕዳ ጫና ካለባቸው ድኃ ሐገራት ጎራ እየተመደበች ፣ ወዘተ

የእዚያች ሐገር መንግሥት ፦ የግቤ 1 ፣ 2 እና 3 ማመንጫዎችን ድምር ኃይል ማመንጨት የእሚችል ፤ በጠቅላላው ወደ 2, 200 ሜጋ ዋት በሰዓት ማመንጨት የእሚችል እና የግምት የግንባታ ወጪው 2.5 ቢልዮን ዶላር የሆነ ግድብ መገንባት አለብኝ በእሚል ፤ ይኽን ግድብ ሳልገድብ እንዴት ተኝቼ አድራለኹ ይላል ብሎ አይጠብቅም።

በኢትዮጵያ ግን በልማታዊነት ስም ፤ በኮይሻ ግድብ እየሆነ ያለው ያ ነው።

ይኼም የልማታዊነት ስረዓታዊ አባካኝነት እና የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ አመራሮች ፤ በልማታዊነት ስም መንግሥትን ያለ መስኩ ነጋዴ ለማድረግ የእሚሞክሩ ፤ ላምን የጦር ፈረስ ማድረግ የእሚያምራቸው ዓይነት ፤ ልዩ ፍጥረት መሆናቸውን ማሳያ ነው።

በእዚያ ላይ ፤ በአግባቡ ቢሠራበት የኮይሻ ግድብ ፤ አኹን ባላቸው ቁመና የኢትዮጵያን እጥፍ ማለት 10 ሚልዮን ደንበኞች የእሚያገለግሉት ኬንያዎች ፤ ከውጭ ኢምፖርት አድርገው እንኳን በሐገር ውስጥ ካላቸው የተተከለ አቅም (Installed Capacity) 66% የእሚሆነውን አገልግሎት መስጠት ይችላል።

በሌላ አነጋገር ፤ የኮይሻ ግድብ ፤ ሌላ ግድብ ሳይፈልግ የአሁኑን የኢትዮጵያ ገበያ ማስተናገድ ይችላል።

## 4.2.7 ነጻ ምሳ የለም

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልም ሆነ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ ሙሉ ለሙሉ የመንግሥት ስለ ሆኑ ፤ ይኽን ኹሉ ብክነት የእሚያስመዘግቡት፡-

- መንግሥት ለማቋቋሚያ እና ለማጠናከሪያ ከሕዝብ ካዝና እና ከውጭ እርዳታ አምጥቶ የእሚሰጣቸውን የኃብት ግብዓት ተጠቅመው ነው ፥
- መሬት በነጻ እያገኙ (ምን አልባትም እንደ ቴሌ የመሬቱን ዋጋ የንብረት ቁጥራቸው ውስጥ በአገባቡ ሳያስገቡ ) ፥
- በኪሳራ ወይንም በሌላ አመካኝተው ግብር ሳይከፍሉ ፥
- ገበያውን ዘግተው ፤ ውድድር አልባ ሞኖፖሊ ፈጥረው ፡-
    - ብድር ፣
    - የሠራተኛ ጉልበት ፣
    - ወዘተ በጣም በርካሽ የወለድ መጠን እና ሌሎች መስኮችን ሊያደክም በእሚችል መንገድ እያገኙ ፣ ወዘተ

በመሆኑ ፤ እንደ እዚኽ የክስረት እና የብክነት ማዕከል ሆነው ፤ እስከ አኹን መቆየት የቻሉት ፤ በአንዳች ዓይነት ጥንቆላ እና ምትኃት ሳይሆን ፤ የማያስተውል ሕዝብ ይገለበጣል እንደ እሚለው ብሒል ፤ የአለማስተዋል ግርዶሽ የጋረደውን ይኽን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ለአንተ ብዬ ነው በእሚል ከንቱ ቅዠት ፤ በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ መንገድ ፤ ኪሱን እያጠቡ ነው።

ስለ እዚኽ ፡- እነ እዚኽን እሚያኽሉ ትላልቅ ክስረቶች የእሚከስሩት ተቋማት ፤ የክስረታቸውን ጉድለት የእሚሞሉት ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት በመፍጠር አደህይተው በመሆኑ ፤ እነርሱ

የኢትዮጵያ ድኃ እየደኸመ ሳይሆን ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በእነርሱ ብክንየት ምክንያት እራሱን እያደኸየ እነርሱን እያስቀጠለ ነው።

# 5 የተቋማቱ አፈጻጸም

በእዚኽ ክፍል ፤ የንግድ ተቋማት ምርታማነት እና ትርፋማነት (Productivity and Profitability) የእሚመዘንባቸውን መለኪያዎች በመጠቀም ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ ትርፋማነት እና ምርታማነት እናነጻጽራለን።

## 5.1 ትርፋማነት ከንብረት አንጻር (Return on Asset – (ROA))

ይኽ መለኪያ ፤ አንድ የንግድ ተቋም ፤ የእራሱን አንጡራ ኃብት እና በብድር ወይንም በተውሶ አግኝቶ በስራ ላይ ካዋለው ኃብት አንጻር በዓመት ምን ያኽል የተጣራ ትርፍ ያገኛል የእሚለውን የእሚለካ እና ኃብቱ በምን ያኽል ደረጃ በአምራች እና ትርፋማ መንገድ ኢንቨስት እንደ ተደረገ የእሚለካ ነው።

አለካኩም ፦ በእየ ዓመቱ የንግድ ተቋሙ የእሚያስመዘግበውን የተጣራ ትርፍ ፤ የተጣራ ትርፉ በተመዘገበት ዓመት በሥራ ላይ በጠቅላላ በዋለው ንብረት ወይንም ኃብት በማካፈል እና የእዚያን ፐርሰንቴጅ በማግኘት ነው።

በእዚኽም ክፍል ፤ የ2024 እና የ2025 ኦዲት የተደረገ ዓመታዊ ሪፖርታቸው በቀረበ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ፦

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን ከኬንያው ኬንጄን ጋር
- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን ከኬንያው KPLC ጋር

ከንብረት አንጻር ያላቸውን ትርፋማነት በማነጻጸር እናያለን[7] ፤ ይኽንንም ንጽጽር በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ እና በኬንጀን መካከል በማድረግ እንጀምር ፦

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል | | ኬንጀን (KENGEN) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| ROA | (-) 14.79% | (-) 1.43% | (+) 2.07 % | (+) 1.38% |

[7] ምንም እንኳን ኹለቱም የንብረት እና የትርፍ መጠናቸውን በብር እና በኬንያ ሽልንግ ቢያስቀምጡም ፤ ከ2024 በኋላ የኢትዮጵያ ምንዛሪ በከፍተኛ ደረጃ በመዳከሙ ፤ የምንዛሪ መጠኑ ተቀራራቢ ካልሆነም የኬንያው ሽልንግ የጠነከረበት ሲሆን ፤ ንፅፅሩ ደግሞ በፐርሰንቴጅ በመሆኑ ፤ ምንዛሪው ብዙም ፋይዳ የለውም።

በሰንጠረዡ ላይ እንደ እሚታየው ፤ በስራ ላይ ከዋለው ጠቅላላ ንብረት ፤ በእያንዳንዱ መቶ ብር የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በ2025 14.79 ብር ሲከስር በ2024 ደግሞ 1.43 ብር ከስሯል።

በአንጻሩ የኬንያው ኬንጄን ፤ በሥራ ላይ ካዋለው ከእያንዳንዱ መቶ የኬንያ ሽልንግ ፤ በ2025 6.29 የኬንያ ሽልንግ የተጣራ ትርፍ ሲያገኝ ፤ በ2024 ደግሞ ከእያንዳንዱ መቶ ሽልንግ 8.40 ሽልንግ አትርፏል።

ይኽም ማለት ፡- በአንዳች መንገድ ይኽ ኪሳራ ካልተተካ ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ንብረት በእየ ዓመቱ በኪሳራው መጠን እያነሰ ነው ማለት ነው። ስለ እዚኽም ፡- ተቋሙን ለማስቀጠል አንዳች ዓይነት ድጎማ ወይንም ብድር ያስፈልገዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከኬንያው አቻው KPLC ጋር ሲንጻጸር ይኽን ዓይነት ውጤት አለው ፡-

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት | | ኬፒሌሲ (KPLC) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| ROA | (+) 2.06% | (+) 3.15% | (+) 6.29 % | (+) 8.40% |

በእዚኽም እንደ እሚታየው ፤ ምንም እንኳን ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እንደ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በኪሳራ ባይሆንም ፤ በሥራ ላይ ካዋለው ኃብት አንጻር ፤ የኬንያው አቻው ግማሽ ትርፋማነት ኖሮት ዕናያለን።

በእዚኽም መሠረት ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በሥራ ላይ ካዋለው እያንዳንዱ 100 ዶላር በ2025 2.06 ዶላር የተጣራ ትርፍ ሲያገኝ ፤ በ2024 ደግሞ 3.14 ዶላር የተጣራ ትርፍ አግኝቷል።

በአንጻሩ የኬንያው KPLC በሥራ ላይ ካዋለው ከእያንዳንዱ የ100 ዶላር ዋጋ ካለው ንብረት ፤ በ2025 6.29 ዶላር ሲያተርፍ በ2024 ደግሞ 8.40 ዶላር አትርፏል።

በእዚኽም የኬንያው KPLC በ2025 እና በ2024 ከንብረት አንጻር የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እጥፍ ትርፋማነት እንደ አለው ይታያል።

## 5.2 ትርፋማነት ከአንጡራ ኃብት አንጻር (Return on Equity – (ROE))

ይኽ መለኪያ ፤ አንድ የንግድ ተቋም ፤ በሥራ ላይ ካሠማራው አንጡራ ኃብት አንጻር በዓመት ምን ያኽል የተጣራ ትርፍ ያገኛል የእሚለውን የእሚለካ እና አንጡራ ኃብቱ በምን ያኽል ደረጃ በአምራች እና ትርፋማ መንገድ ኢንቨስት እንደ ተደረገ የእሚለካ ነው።

አንጡራ ኃብት አንድ ተቋም በብድር ወይንም በተውሶ አግኝቶ ሥራ ላይ ካሰማራው ኃብት ውጭ ያለ ወይንም ከማንኛውም እዳ ውጭ ያለ ኃብት ሲሆን ፤ አንድ ተቋም ዛሬ ቢሸጥ ፤ እዳዎች ወይንም ተውሶዎች በሙሉ ከተመለሱ በኋላ ፤ ለባለቤቱ ወይንም ለባለቤቶቹ የእሚቀረው ኃብት ማለት ነው።

አለካኩም ፦ በእየ ዓመቱ የንግድ ተቋሙ የእሚያስመዘግበውን የተጣራ ትርፍ ፤ የተጣራ ትርፉ በተመዘገበት ዓመት በሥራ ላይ በጠቅላላ በዋለው የተጣራ ኃብት በማካፈል እና የእዚያን ፐርሰንቴጅ በማግኘት ነው።

በእዚኽም ክፍል ፤ የ2024 እና የ2025 ኦዲት የተደረገ ዓመታዊ ሪፖርታቸው በቀረበ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ፦

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን ከኬንያው ኬንጄን ጋር
- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን ከኬንያው KPLC ጋር

ከንብረት አንጻር ያላቸውን ትርፋማነት በማነጻጸር እናያለን[8] ፤ ይኽንንም ንጽጽር በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ እና በኬንጀን መካከል በማድረግ እንጀምር ፦

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል | | ኬንጀን (KENGEN) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| ROE | (-) 25.81% | (-) 1.80% | (+) 15.74 % | (+) 17.02% |

በሰንጠረዡ ላይ እንደ እሚታየው ፤ በስራ ላይ ከዋለው አንጡራ ኃብት ፤ በእያንዳንዱ መቶ ዶላር የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በ2025 25.81 ዶላር ሲከስር በ2024 ደግሞ 1.80 ዶላር ከስሯል።

በአንጻሩ የኬንያው ኬንጄን ፤ በሥራ ላይ ካዋለው ከእያንዳንዱ የተጣራው የራሱ ኃብት መቶ ዶላር ፤ በ2025 15.74 ዶላር የተጣራ ትርፍ ሲያገኝ ፤ በ2024 ደግሞ ከእያንዳንዱ መቶ ዶላር 17.02 ሽልንግ አትርፏል።

ከእዚኽም ማየት እንደ እሚቻለው ፤ የኬንያው ኬንጀን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከ10 እጥፍ በላይ በአንጡራ ኃብቱ ትርፋማ እንደ ሆነ ነው እሚታየው። ምክንያቱም ፦ መክሰሩ ቀርቶ እንኳን ፤ የኢትዮጵያ

[8] ምንም እንኳን ኹለቱም የንብረት እና የትርፍ መጠናቸውን በብር እና በኬንያ ሽልንግ ቢያስቀምጡም ፤ ከ2024 በኋላ የኢትዮጵያ ምንዛሪ በከፍተኛ ደረጃ በመዳከሙ ፤ የምንዛሪ መጠኑ ተቀራራቢ ካልሆነም የኬንያው ሽልንግ የጠነከረበት ሲሆን ፤ ንፅፅሩ ደግሞ በፐርሰንቴጅ በመሆኑ ፤ ምንዛሪው ብዙም ፋይዳ የለውም።

ኤሌክትሪክ ኃይል በ100 ዶላር አንጡራ ኃብት ያለው ትርፋማነት 1 ዶላር ነው ብንል እንኳን ፤ የኬንያው ኬንጀን በአንጡራ ኃብት ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አንጻር ከ15 እጥፍ እና ከ17 እጥፍ በላይ ትርፋማ ሆኖ የሚገኝ በመሆኑ ነው።

በትርፋማነት ከአንጡራ ኃብት አንጻር ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከኬንያው አቻው KPLC ጋር ሲነጻጸር ደግሞ ፤ ይኸን ዓይነት ውጤት ይኖረዋል ፡-

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት | | ኬፒሌሲ (KPLC) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| ROA | (+) 2.77% | (+) 4.85% | (+) 22.38 % | (+) 34.45% |

በእዚኽም እንደ እሚታየው ፤ ምንም እንኳን ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እንደ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በኪሳራ ባይሆንም ፤ በሥራ ላይ ካዋለው የእራሱ አንጡራ ኃብት አንጻር ፤ ከኬንያው አቻው በ2025 በ8 እጥፍ ፤ በ2024 ደግሞ በ7 እጥ ያነሰ ትርፋማነት ኖሮት ዕናያለን።

በእዚኽም መሠረት ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በሥራ ላይ ካዋለው የእራሱ የተጣራ ኃብት ከእያንዳንዱ 100 ዶላር በ2025 2.77 ዶላር የተጣራ ትርፍ ሲያገኝ ፤ በ2024 ደግሞ 4.85 ዶላር የተጣራ ትርፍ አግኝቷል።

በአንጻሩ የኬንያው KPLC በሥራ ላይ ካዋለው ከእያንዳንዱ የ100 ዶላር ዋጋ ካለው ከማንኛውም እዳ ነጻ የሆነው የራሱ የተጣራ ኃብት ፤ በ2025 22.38 ዶላር ሲያተርፍ በ2024 ደግሞ 34.45 ዶላር አትርፏል።

በእዚኽም የኬንያው KPLC በ2025 እና በ2024 ከንብረት አንጻር የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከ7 እጥፍ በላይ ትርፋማነት እንደ አለው ይታያል።

## 5.3 ጠቅላላ ገቢ ከሥራ ማስኬጃ ወጪ አንጻር (Operating Cost per Total Income)

ይኸ መመዘኛ ፤ ቋሚ ኢንቨስትመንት ከእሚባሉት ፤ ለምሳሌ ፡- ግድብ ወይንም ሕንጻ ግንባታ ወጪዎች ውጭ ፤ ዓመታዊ ገቢን ለመፍጠር ከወጡ ፤ ለምሳሌ ፡- የመለስተኛ ዕቃ ግዢዎች ፣ የሠራተኛ ደሞዝ ፣ የነዳጅ ፣ የጥገና ፣ የእርጅና (Depreciation) (Essentially it is the sum of Direct Costs + Operational Expenses and Depreciation Costs in the case of EEP) ፣ ወዘተ ዓይነት ወጪዎች አንጻር ከትርፍ በፊት ምን ያኸል ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ መሰብሰብ ተችሏል የእሚለውን የእሚለካ ነው።

ይኸም የተቋማትን የወጪ አወጣጥ ብቃት (Operational Efficiency) ከገንዘብ አንጻር ይመዝናል።

በእዚም መሠረት ፤ በ2025 እና በ2024 ባቀረቡት ኦዲት የተደረገ ሪፖርታቸው መሠረት ፡-

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከኬንያው ኬንጀን ፥
- የኢትዮጵያው ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከኬፒሊሲ ፥

ጋር ሲነጻጸሩ የእሚከተሉትን ዓይነት ውጤት አላቸው።

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል | | ኬንጀን (KENGEN) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| Operating Cost/Total Income | (+) 27.84% | (+) 60.11% | (+) 79.83 % | (+) 84.05% |

ይኸም ማለት ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በ2025 100 ዶላር ገቢ ለመፍጠር የ27.84 ዶላር የሥራ ማስኬጃ ወጪ ያወጣ ሲሆን ፤ በ2024 ደግሞ የ100 ዶላር ገቢ ለመፍጠር 60.11 የሥራ ማስኬጃ ወጪ አውጥቷል።

በአንጻሩ የኬንያዊ ኬንጀን የ100 ዶላር ገቢ ለመፍጠር በ2025 የ79.83 ዶላር ሥራ ማስኬጃ ወጪ ያወጣ ሲሆን ፤ በ2024 ደግሞ የ100 ዶላር ገቢ ለመፍጠር የ84.05 ዶላር የሥራ ማስኬጃ ወጪ አውጥቷል።

እንግዲኽ በእዚኽ መመዘኛ የለካናቸው እንደሆን ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤ በአንጻራዊ ርካሽ ደሞዝ ፣ የመሬት አቅራቦት ፣ እና ሌሎች የአገልግሎት ወጪዎች ወዘተ ምክንያት በአንጻራዊነት ከኬንያው ኬንጀን በ2025 ከእጥፍ ባነሰ የሥራ ማስኬጃ ወጪ ተመሳሳይ ገቢ መፍጠር ሲችል ፤ በ2024 ደግሞ ከኬንጀን 33% ገደማ ቅናሽ ባለው የሥራ ማስኬጃ ወጪ ከኬንጀን ጋር ተመሳሳይ የሆነ ገቢ መፍጠር ችሎ እናየዋለን።

ይኸ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን ፤ የገቢ ፈጠራ ጥሩ ብቃት ሊያሳይ ሲችል ፤ ይበልጥ ሲመረመር ግን ፡-

1. ምን አልባት ፡- ለሠራተኛ አነስተኛ ደሞዝ በመክፈል እና ብዙ በማሠራት ፥ የተለያዩ መንግሥታዊ ድጎማዎችን በመጠቀም ጭምር እንጂ በውጤታማ የሥራ ማስኬጃ ወጭ አስተዳደር ላይሆን ይችላል።
2. ከእዚያ ሲቀጥል ፤ ይኸን የመሠለ በዝቅተኛ የሥራ ማስኬጃ ወጪ ተወዳዳሪ ገቢ መሠብሰብ የቻለ ተቋም ፤ እንዴት በእየ ዓመቱ ፤ ለምሳሌ ፡- በ2025 የኢትዮጵያ 122 ብር በ2024 ደግሞ 10 ቢልዮን ብር ሊከስር ይችላል የእሚለውን ጥያቄ ስንመልስ የእሚመጣው ነው። እርሱም ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዋነኛ የኪሳራው ምንጭ ፤ የኃይል ማመንጫዎችን ለመገንባት የወሰዳቸው ብድሮች ፤ አብዛኛው የዶላር ወይንም የውጭ ምንዛሪ ብድሮች ፤ ከምንዛሪ አቅም መዳከም ጋር ተዳምረው በእሚያደርሱበት ጫና መሆኑ ነው። ይኸም ፡- የክስረቱን ዋነኛ ምንጭ ፤ ባግባቡ የእማይጠቀምበትን ኃይል በከፍተኛ ብር ተበድሮ በመሥራቱ መሆኑ ፤ ተቋሙ የእሚከስረውን ኪሣራ የእሚከስረው ፤ ድኃ በመደጎሙ የእሚለውን መከራከሪያ በማፍረስ የተቋሙ ትክክለኛ የኪሳራ ምንጭ ፤ የተበላሸ የኢንቨስትመንት ስልት መሆኑን ያሳያል።

በመሆኑም ፡- ጥንካሬ የእሚመስለው ፤ የሥራ ማስኬጃ ወጪ አፈጻጸም ብቃት ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን ብቃት ሳይሆን ፤ ውስጣዊ የተሸሸገ ችግር ማሳያ ያደርገዋል።

ይኸንን ተመሳሳይ መለኪያ በመጠቀም ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን ከኬፒአልሲ ጋር ስናጻጽር ደግሞ የእሚከተለውን ውጤት እናገኛለን ፡-

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት | | ኬፒኤልሲ (KPLC) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| Operating Cost/Total Income | (+) 86.95% | (+) 101.89% | (+) 87.34 % | (+) 84.68% |

ከሰንጠረዡ ልትመለከቱ እንደ እምትችሉት ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ፤ የሥራ ማስኬጃ ወጪ አስተዳደር ፤ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የተገላቢጦሽ በመሆን ፤ በ2025 የ100 ዶላር ገቢ ለመፍጠር 86.95 ዶላር ወጪ ያወጣ ሲሆን ፤ በ2024 ደግሞ ይባስ ብሎ ፤ የ100 ዶላር ገቢ ለመፍጠር ብሎ 101.89 ዶላር ወይንም የሥራ ማስኬጃ ወጪ ከፈጠረው ገቢ በልጧል።

በአንጻሩ ኬፒኤልሲ ደግሞ ፤ ምንም እንኳን ይኸን መሠል የሥራ ማስኬጃ ወጪ በጣም ግሩም የእሚባል ዓይነት ባይሆንም ፤ በአጻራዊነት ከኬንጀን ወይንም ከኃይል አምራቹ ጋር ተመሳሳይ አፈጻጸም በማሳየት ፤ በ2025 የ100 ዶላር ገቢ ለመፍጠር የ87.34 ዶላር የሥራ ማስኬጃ ወጪ ሲያወጣ ፤ በ2024 ደግሞ የ100 ዶላር ገቢ ለመፍጠር የ84.68% የሥራ ማስኬጃ ወጪ አውጥቷል።

እዚኽ ጋር ፤ ዋና ጥያቄ የእሚሆነው ፤ ለምሳሌ ፡- በ2024 ከገቢው የእሚበልጥ የሥራ ማስኬጃ ወጪ ያወጣው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዴት በእዚያ ዓመት የ3.7 ቢልዮን ብር ትርፍ አተረፈ የእሚለው ነው።

እላይ በክፍል 4.1 ላይ እንደ ተቀመጠው ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በ2024 ትርፋማነት ያስመዘገበው ፤ በትክክልም ትርፋማ ስለ ነበር ሳይሆን ፤ በእሚከተለው የIFRS ሪፖርት ማድረጊያ መመሪያ መሠረት ፤ በጣም በትንሽ ብድር የተሰጠውን ብድር ፤ ይኽን ብድር ከገበያ ብበደረው ኖሮ የ4.7 ቢልዮን ብር የወለድ ክፍያ ይኖርብኝ ነበር ፤ አኹን ግን ብድሩን በመጣያ የወለድ መጠን በማግኘቴ ፤ ያን ሊከፈል ይችል የነበረ የወለድ መጠን ገቢ ብዬ መመዝገብ አለብኝ ብሎ ፤ በርካሽ ብድር ምክንያት ሳይከፍል የቀረውን ወለድ ፤ እንደ ገብ ቆጥሮ ገቢ ብሎ በማስታወቁ አንዱ ሲሆን።

ሌላ ደግሞ ከ 1 ቢልዮን ብር ትንሽ የእሚበልጥ የአሮጌ ዕቃ ሽያጮች ስለ አደረገ ነው።

የ2025ቱ ትርፍ ግን ፤ በዋናነት ኤሌክትሪክ የመሸጫ ዋጋ እና ኤሌክትሪክ ማስገቢያ ዋጋዎችን በ1/3 ገደማ በመጨመር የመጣ ይመስላል።

የኪሳራ ውርጅብኝ በእሚለው በክፍል 4.1 ላይ እንደ ተቀመጠው ግን ፤ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ ከፈረንጆቹ 2018 እስከ 2025 ባሉት 8 ዓመታት በአንዱ ማለትም በ2018 ብቻ ነው የከሰርኩት ቢልም ፤ የርዳታ ብድርን ወለድ ከገበያ ቢበደረው የሚከፍለውን ብር እንደ ገቢ በመቁጠር እና ለቆራሌው እቃ በመሸጥ ባይሆን ኖሮ ፤ ከሶሥቱ ዓመታት ፤ ማለትም ፡- ከ2025፣ 2023 እና 2022 በስተቀር በኪሳራ ነበር የእሚሆነው።

በጥቅላላውም ፡- በእዚኽ ከሥራ ማስኬጃ ወጪ አንጻር የገቢ መጠን ከእሚመመዝንበት መለኪያ አንጻር ካየነው ፤ ተቋማቱ ጥንካሬያቸውን ሳይሆን እምናየው ፤ ጠንካራ እንኳን ሲመስሉ ፤ ጥንካሬው የብዙ ሌሎች ስውር ጉዳቶች መሸፈኛ እንጂ ዕውነተኛ ጥንካሬ እንደ አልሆነ ነው።

ይኽም ፡- በሐገራችን ከእምንከተለው ግትር አቋም አንጻር ፤ ስር የሰደደ መዋቅራዊ በሽታ እንደ አለብን እና በግዜ ፤ እውነቱን ወደ ጸሐይ አውጥተን ፤ ኪሳራውን ኪሳራ ፣ ድካሙን ድካም ፣ ጥፋቱን ጥፋት ብለን ለቀጣይ የይስሙላ ሳይሆን እውነተኛ የእርምት እርምጃ ፤ ግልጸኝነት እና ተጠያቂነት ባለው የገበያ ስረዓት ካልተመራን ፤ ከሐገር ክዳት ያልተናነሰ ጥፋት በማጥፋት ፤ ሐገር እያደከምን እና እየጎዳን ነው እሚሆነው።

## 5.4 ንብረት በሠራተኛ ( Assets Per Employee)

በዘመናዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ የአንድ ሠራተኛን ምርታማነት የእሚያሳድገው ፤ የሠራተኛው ፡- ሞያዊ ብቃት ፣ ትጋት እና ጥረት ብቻ ሳይሆን ፤ ሥራውን ለመከወን የእሚቀርብለት መሣሪያ በመሆኑ ፤ በእየ ሥራ መስኩ ተቋማት ባላቸው የሠራተኛ ብዛት እና በሥራ ላይ ባዋሉት ንብረት መካከል ያለው ተዛምዶ ፤ የሠራተኛ አጠቃቀም እና የሠራተኛ ምርታማነትን ለመለካት እንደ ማሳይ ይወሰዳል።

ይኸን ካልን ዘንዳ ፤ የኢትዮጵያ ኤሊክትሪክ ኃይልን ከኬንያው ኬንጀን እንደ እዚኹም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን ከኬንያው ኬፒኤልሲ ጋር ንብረት በሠራተኛ መለኪያ መሠረት በ2025 እና በ2024 እናነጻጽር።

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል | | ኬንጀን (KENGEN) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| Asset Per Employee | 10,760,892,898.10 | 9,026,402,467.25 | 20,848,376,412.37 | 19,534,503,180.91 |

ከሰንጠረዡ ልትመለከቱ እንደ እምትችሉት ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሠራተኞች በአማካይ ከኬንጀን በግማሽ ያነሰ ንብረት በሥራቸው አለ።

ይኸ በአንድ በኩል ፤ የኬንያ ሠራተኞች ሥራቸውን ለመሥራት እና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ ፤ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሠራተኞች ኹለት እጥፍ ዘመናዊ መሣሪያ ይጠቀማሉ ሊያስብል ሲችል ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ቅጥርን እንደ ማሕበራዊ ዋስትና በማቅረብ ፤ በአግባቡ ሥራውን ለማከናወን ከእሚያስፈልጉት በላይ በርካታ ሠራተኞችን ይቀጥራል ማለት ሊሆን ይችላል።

እንዴትም ቢታይ ግን ፤ የኢትዮጵያ ኤሊክትሪክ ኃይል **<u>በሠራተኛ ያለው ንብረት</u>** (Asset Per Employee) ተወዳዳሪ የእሚያስብለው እንደ አልሆነ ነው።

ወደ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ኬፒኤልሲ ስንመጣ ደግሞ ነገሩ ይበልጥ ይገንና ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ ምግብ ለሥራ የእሚል የሴፍቲኔት ዓይነት ተቋም እንጂ ዘመናዊ የሐገር አውታር የሆነ አንድ ትልቅ ኮርፖሬሽን እስከ አይመስል ድረስ ፤ በጣም የተጋነነ የሠራተኛ ቁጥር ኖሮት ነው የእምናገኘው።

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት | | ኬፒኤልሲ (KPLC) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| Asset Per Employee | 730,076,795.78 | 437,657,902.43 | 3,676,426,866.38 | 3,548,218,380.90 |

በሠንጠረዡ ላይ የእሚታየውን ቁጥር ፤ የKPLCን በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በእየ ዓመቱ በማካፈል ልታዩ እንደ እምትችሉት ፤ በ2025 የኬፒኤልሲ ሠራተኞች ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ይልቅ በሠራተኛ 5 እጥፍ ንብረት በሥራ ላይ እንደ አላቸው እና በ2024 ደግሞ እጥፈቱ ከፍ በማለት 8 እጥፍ ይደርሳል።

በተለይ ከኢትዮ ቴሌኮም እና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ልምድ ጋር አዛምደን ይኸን ስናየው ፤ ኮርፖሬሽኖቹ በጥቂት ኢንቨስትመንት ሠራተኞችን ብዙ እያሠሩ ሳይሆን ፤ ተቋማቱ የካድሬ መቀጠሪያ በመሆን ፤ የማሕበራዊ ዋስትና ሥራ እየሠሩ እንጂ የተቋቋሙለትን ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል እና አገልግሎት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማቅረብ ሥራ እየሠሩ እንደ አልሆነ ግልጽ ይሆናል።

ምንም እንኳን ደጋግሜ እንደ አልኹት ከኢትዮጵያ 2014 በኋላ ፤ በተለይ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ ተቋማዊ መረጃ የመደበቅ በሽታ ስለ ተጸናወተው ፤ የ2017 ግልጽ የደንበኞች እና የሠራተኞቹን ቁጥር በቀጥታ ማግኘት ባይቻልም ፤ በ2014 ባወጣው ፋክትስ ኢን ብሪፍ በእሚለው መጽሔቱ ላይ ፤ ጠቅላላ የቅድመ ክፍያ እና የድህረ ክፍያ ደንበኞቼ ቁጥር 4,324,859 ነው ስለ እሚል እና ከእዚያ በፊት የነበረውን ዓመታዊ የደንበኛ ቁጥር ዕድገት መሠረት አድርገን ከ2014 እስከ 2017 1 ሚልዮን ደንበኛ ጨምሯል ብንል ጠቅላላ የደንበኞቹ ቁጥር 5, 324, 859 ስለ እሚሆን እና በተመሳሳይ ስሌት በእዚያው መጽሔት ላይ ጠቅላላ የሠራተኞቼ ቁጥር (ቋሚ እና የኮንትራት ጨምሮ) 26, 180 ናቸው ስለ እሚል እና ከ2014 ዓም በኋላ ከ 1 ሺ ሠራተኛ በላይ ሊጨምር አይችልም በእሚል በ2014 ዓም የጠቅላላ ሠራተኛ ቁጥሩን 27, 000 አድርገን በእዚያ ወቅት ከነበረው ከኬፒኤልሲ 10 ሺ ሠራተኛ ጋር ስናነጻጽረው ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልም ሆነ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ የቅጥር ሴፍቲኔት እንጂ የሐገር ምሶሶ የሆነ ኮርፖሬሽንነት ባሕሪ እንደ ሌላቸው ግልጽ ይሆናል።

ምክንያቱም ፦ ከእዚኽ በታች ፤ በ2025 እና በ2024 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ኬፒኤልሲ ያላቸውን የሠራተኛ ቁጥር እና የደንበኛ ቁጥር ተመልከቱ ፦

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት | | ኬፒኤልሲ (KPLC) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| የሠራተኛ ቁጥር | 27,000 | 26,667 | 10,582 | 10,092 |
| የደንበኛ ቁጥር | 5,324,859 | 4,991,526 | 10,100,000.00 | 9,643,865.00 |

ከማነጻጸሪያ ሰንጠረዡ ልትመለከቱ እንደ እምትችሉት ፤ ኬፒኤልሲ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከግማሽ በላይ ያነሰ ሠራተኛ ኖሮት በአንጻሩ ደግሞ ከእዚኽ ከግማሽ በላይ በሆነው የሠራተኛ ቁጥር የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን ከእጥፍ በላይ የሆኑ ደንበኞችን ያገለግላል።

የእራሳችን አንድ ሠራተኛ ስንት ደንበኛ ያስተናግዳል በእሚል ፤ የደንበኞችን ቁጥር በሠራተኛ ቁጥር ብናካፍል ፦ በደንበኛ የእሚል መለኪያ ብንፈጥር እና ብናነጻጽር ፦

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት | | ኬፒኤልሲ (KPLC) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| ሠራተኛ ለደንበኛ | 197.217 | 187.18 | 954.45 | 955.59 |

ማለትም ፦ ለምሳሌ ፦ በ2025 አንድ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሠራተኛ በአማካይ 197 ደንበኞች ሲያስተናግድ ወይንም ሲያገለግል በአንጻሩ የኬንያው ኬፒኤልሲ ሠራተኛ በአማካይ የእርሱን 5 እጥፍ 954 ደንበኞች ያገለግላል።

በሌላ መልኩ እናስቀምጠው ካልን ደግሞ ፤ የኬንያውን ኬፒኤልሲ ዓይነት የሠራተኛ አጠቃቀም ቢኖረው ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አሁን በ27,000 ሠራተኞች የእሚሠራውን ሥራ በ5,500 ሠራተኞች ሊሠራው የእሚችል እና ከ21,000 በላይ የእሚሆኑት ሠራተኞች ትርፍ ሠራተኞች እንጂ አምራች ሠራተኞች አይደሉም ማለትን ያስከትላል።

ታዲያ ይኽ ተቋም ነው የኢትዮጵያ ሕዝብን የተሸከመው ወይንስ በስሙ የእሚቆመረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ፤ ይኽንን እና መሠል በልማታዊነት ስም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃው ላይ የተሸከማቸው ?

መልሱ ግልጽ ይመስለኛል።

## 5.5 ትርፍ በሠራተኛ (Profit Per Employee)

ይኽንኛው መለኪያ ፤ በቀላሉ ጠቅላላውን የተቋማቱን የተጣራ ትርፍ ለሠራተኛቸው ቁጥር በማካፈል ፤ በአማካይ እያንዳንዱ ሠራተኛ ምን ያኽል ትርፍ አመጣ የእሚለውን ለመገመት የእሚያስችል መለኪያ ነው።

በእዚኽም መሠረት ፤ በቀጣይ ፡-

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን ከኬንጀን
- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን ደግሞ ከኬፒኤልሲ

ጋር በእዚኽ መመዘኛ ፤ ማለትም ትርፍ በሠራተኛ በማነጻጸር ፤ ተቋማቱ ሠራተኞቻቸውን በምን ያኽል ደረጃ በትርፋማነት እየተጠቀሙባቸው እንደ ሆነ ለማየት እንሞክራለን።

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል | | ኬንጀን (KENGEN) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| Profit Per Employee | (-) 15,914,080.92 | (-) 1,288,282.33 | 18,468,270.52 | 18,815,347.51 |

ቀደም ብለን እንደ አልነው ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤ ከ2018 እስከ 2025 ባሉት 8 ዓመታት ትንሽ ሲከስር 10 ቢልዮን ብር ሲከፋ ደግሞ 122 ቢልዮን ብር ድረስ የእሚከሥር በመሆኑ ፤ በሠራተኛ የእሚመዘገብ ትርፍ ሳይሆን ኪሳራ ነው ያለው።

በመሆኑም ፡- በ2025 በሠራተኛ 15.9 ሚልዮን ብር ሲከስር በ2024 ደግሞ በሠራተኛ 1.29 ሚሊዮን ብር ከሥሯል።

በአንጻሩ ኬንጀን በ2025 በሠራተኛ 18.5% ሚልዮን የኬንያ ሽልንግ ሲያተርፍ ፤ በ2024 ደግሞ በሠራተኛ 18.8 ሚልዮን የኬንያ ሽልንግ አትርፏል።

እንደ እሚታየው ልዩነታቸው ለንጽጽርም እሚበቃ ባይሆንም ፤ ጉድ ሳይሰማ ግምገማ አያልቅም ነውና ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለኬንያው ገበያ ኤሌክትሪክ ኤክስፖርት ያደርጋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን እና የኬንያውን ኬፒኤልሲ ትርፋማነት በሠራተኛ መሠረት ስናነጻጽር ደግሞ ፡-

| | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት | | ኬፒኤልሲ (KPLC) | |
|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2024 | 2025 | 2024 |
| Profit Per Employee | 150,129.81 | 137,918.64 | 2,312,088.92 | 2,980,615.34 |

አኹንም በድጋሚ በሠንጠረዡ እንደ እሚታየው ፤ የእርዳታ ድርጅቶች የሰጡኝን ብድር ፤ ከገበያ ብብደረው ኖሮ ብዙ ወለድ እከፍል ነበርና ፤ አኹን በነሱ ቸርነት ያተረፍኩትን የወለድ ክፍያ ነገር ግን ሠርቼ ያላመጣኹትን ትርፍ ፤ ትርፍ ብዬ ሪፖርት ማድረግ አለብኝ ብሎም ቢሆን ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፤ እንደ አቅሙ ፤ በሠራተኛ በ2025 150 ሺ ብር እና 2024 ደግሞ 138 ሺ ብር ገደማ አትርፏል።

በአንጻሩ ፤ የኬንያው ኬፒኤልሲ ደግሞ በ2025 በሠራተኛ 2.3 ሚልዮን ሽልንግ ሲያተርፍ ፤ በ2024 ደግሞ በሠራተኛ 2.9 ሚልዮን ሽልንግ አትርፏል።

ኹለቱን በማካፈል ማየት እንደ እሚቻለው ፤ በ2025 የኬንያው ኬፒኤልሲ በሠራተኛ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ይልቅ 15 እጥፍ ትርፋማነት ሲኖረው ፤ በ2024 ደግሞ በሠራተኛ ከ21 እጥፍ በላይ ትርፋማነት እንደ አለው ይታያል።

በመሆኑም ፡- በኢትዮጵያ ታሪክ ፤ እንደ ማሕበራዊ ፍትሕ እና ሶሻሊዝም አስተሳሰብ ተከታይ በሆኑ ሰዎች ፤ በኢትዮጵያ ላይ ከተፈጸመው በደል በላይ ሌላ በደል የተፈጸመ አይመስልም።

# 6 ማጠቃለያ

ክብር ኢትዮጵያዊያን ፤ እኔ ይኽን ተከታታይ የምርመራ ጽሑፍ ስጀምር ፤ የሐገራችን የፖለቲካ ተዋንያን ደካማ የጽንሰ ኃሳብ ሙግት የማድረግ አቅም ስለ አላቸው ፤ ለኢትዮጵያ ከልማታዊነት (በተለይ ኢትዮጵያዊያን ልማታዊነት ከእሚሉት) መርኽ ይልቅ የነጻ ገበያ አሠራር በተገበው የፖለቲካ መዋቅር ከታቀፈ የተሻለ ሥራ ይሠራል የእሚለውን ለማሳየት ፤ የሐገራችን ልማታዊ ድርጅቶች ፤ በልማታዊነት አስተሳሰብ እየተመሩ በእራሳቸው ፣ በሐገር እና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሱትን ጉዳት ፤ በእሚታወቅ የሒሳብ ምርመራ ስልት ለማሳየት እና በአንጻሩ ደግሞ እነ እዚኽ ተቋማት በገበያ ቢመሩ ኖሮ ፤ ሊያስገኙ ይችሉ የነበረውን ጥቅም በማሳየት ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ነጻነት ዴሞክራሲ እና ነጻ ገበያ ፤ የይስሙላ ሳይሆን የልብ ሽግግር እንድናደርግ ለማሳሳብ ወይንም ለማሳየ ነበር።

ነገር ግን በእዚኽ ኺደት ውስጥ እኔም እራሴ ብዙ እየተማርኩ እና ግንዛቤዬም በመረጃ እየተደገፈ ሲኼድ ፤ ይኽ የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ፤ እንደ ሐገር ይኽንን ማሳሰቢያ ሰምተን ፤ በግዜ አካኼዳችንን ካላስተካከልን ፤ ዝንጋታችን ከሐገር ክዳት የእማይተናነስ እና ውጤቱም ከሐገራዊ ስብራት እና ውርድት ውጭ ሌላ ምንም ላይሆን እንደ እሚችል እየታየኝ ፤ የአለንበትን አስፈሪ ኹኔታ ይበልጥ አጉልቼ እንደ አይ አድርጎኛል።

እናም ትልቁ መጽሐፍ እንደ እሚለው ፤ ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ አለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉኃል ፤ ኢትዮጵያዊው ሆይ ለራስህ ስትል ፤ ይኼን የከብት ፖለቲካህን አቁም እና ለራስህ ስትል ስማና ፤ ወደ ዴሞክራሲ እና ነጻ ገበያ ና ፤ እምቢ ብትል ግን ፤ ድንጋይ ነው ብለው ፦ አረብ ሐገር ፣ አፍሪካ ሐገር ፣ አውሮፓ እና አሜርካ ይጥሉኃል እንጂ ባለሐገር ሆነኽ አትኖራም !